
በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የማህበራዊ ጉዳይ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75
ካናዳ $3.00

# ላንዳፍታ




እየተበጣጠሰች በመሄድ ላይ ያለችው ኢትዮጵያ የጥንት ካርታዋ

በዚህ እትም

- ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)
- ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ (ገብርዬ)
- ጦርነቱን በተመለከተ ሰፋ ያለ ዜና
- “አ ይ ሰ ማ ም !” (ከጦራ ጦጦራ)
- “ኢትዮጵያና ችግሮቿ”
- ኑሮ በአሜሪካ
- ልብ ወለድ

?ካቲት/መጋቢት
፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
፯ኛ ዓመት
ቁጥር ፫

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine in Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
FEBRUARY/MARCH 1999
Vol. 7 No.3

# L & M GLOBAL SERVICES, INC.

450 N. Indian Creek Dr., Clarkston, GA 30021
Phone: 404-296-3088 - Fax: 404-296-7413

## ታክስ በማዘጋጀት ልምድ ባላቸው፤

- የግልና የንግድ
- ፈጣን የታክስ አገልግሎት
- ፌዴራልና ስቴት
- አሜንድድ ሪተርን

ጥያቄ ካልዎት ለአከን ያነጋግሩ።

ለአከ ማለደ — LEAKE MALEDE

AUTHORIZED IRS e-file PROVIDER

*Member of National Society of Tax Professionals*

## RTS ACCOUNTING & INCOME TAX SERVICE

Professional Tax Preparation

- Indiviadual & Business
- Electronic Tax Filing
- Federal & State Return
- Amended Return

## Other Services:

- ⇒ **Prepare monthly Sales Tax Report**
- ⇒ **Prepare Business Loan Package**
- ⇒ **Book Keeping Service**

Choose how fast you want your Refund:

- Electronic Refund
- Direct deposit
- I.R.S. Check

# ASAP COPIES

**The Mission of ASAP COPY Center** Quality service as cost effectively as possible.

**Turn Around Time:** The Copy Center can turn around most jobs in 24 to 48 hours based on 1. The time the order received 2. Other work in progress 3. The size of the job, special stock requirements amound of bindery requirements.

**The ASAP COPY offers:** Copying of all your jobs, large & small. 20# white 8 1/2x11 1 plain or 3 hole drilled paper. Variety of colored paper and cover stock letter head. Transparencies. Stapling. Collating.

**Consulting service** on how to produce the most professional look at the most reasonable price.

- √ FLYERS
- √ BUSINESS CARDS

- √ Typesetting
- √ High-Speed Duplicating
- √ Fax service
- √ Self-Serve Copies
- √ Passport Photo
- √ Immigration Photo
- √ Resume
- √ Flyers

*MoneyGram*
*Money sent worldwide*
*Authorized MoneyGram Agent*

*We are located at Campus Plaza Mall across from Dekalb Book Store*

# With Gratitude!

**ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ለቤተሰብ ለዘመድና ለወዳጅ ወደ አዲስ አበባ ለመላክ ሲያስፈልግዎ በ2 ሰዓት ውስጥ አዲስ አበባ በሚያደርሰው**

**ፈጣንና አስተማማኝ በሆነው ድርጅታችን ይጠቀሙ።**

በግ (ከነቆዳው)........................$39.99
ኩንታል ጤፍ........................ $69.99
ዶሮ........................$ 5.99
ውስኪ (ጆኒ ዎከር) ........................$29.99
ሻምፓኝ........................$19.99
የተለያዩ ፍራፍሬዎች ለሕመምተኛ ለማቀበል (በ45 ደቂቃ)................$19.99
ለእዝን እንጀራ ከሁለት ድስት ወጥ ጋር (በ45 ደቂቃ)................$59.99
ኬክ........................$15.99
የማር ጠጅ........................$ 9.99
አበባ ቡኬ........................$10.99
ኪሎ ቡና እንዲሁም ኪሎ ስኳር........................$14.99
ጠበል ለሚፈልጉ ሰዎች በመኪና ማጓጓዝ........................$እንደርቀቱ

## ለሠርግ ስጦታ

የተሟሉ የሻይ ሲኒ ከኬክ ሳህን ጋር........................$59.99
የተሟሉ የወይን ጠጅ (WINE) ብርጭቆዎች........................$59.99
የተሟሉ የጭማቂ ብርጭቆዎች........................$59.99
የተሟሉ የሻምፓኝ ብርጭቆዎች........................$49.99
የተሟሉ የምግብ ሳህኖች ከብርጭቆዎች ጋር........................$129.99
ሳምሰንግ 20 ኢንች ባለቀለም ቴሌቪዥን ........................$519.00
ሰንጋ በሬ........................$589.99
ሰርገኞች ባህርዳር ለማዝናናት በአውሮፕላን እስከ 9 ሰው................$889.99
ላንጋኖ ለንፋስ ቅየራ እስከ 9 ሰው —አዋሽ ላይ ነፃ ለስላሳ ብስኩትና ሻይ ....$169.99
ሶደሬ ለማናፈስ እስከ 9 ሰው— ሞጆ ላይ ነፃ ለስላሳ ብስኩትና ሻይ ..........$119.99
ለአራስ ጥሪ........................$59.99
ከ2 እስከ 10 ዓመት ዕድሜ ለሆናቸው ልጆች የልደት ስጦታ........................$69.99

ከዚህ በላይ በዝርዝር ካቀረብናቸው ሌላ የሚያስፈልግዎት ዕቃ ካለ ብዙ ዝርዝር ውስጥ ያልገቡ ዕቃዎች ስላሉን በስልክም ሆ በፋክስ ቢጠይቁን ለመርዳት ዝግጁ መሆናችንን እየገለጽን፣

**አዲስ አበባ ቤተሰባችሁ በር ድረስ ስለምናደርስ ለስልክ ገንዘብ ከማባከን፤ በባህላዊ ሥነሥርዓት ቤተሰባችሁንና ዘመዶቻችሁን አስደስቱ።**

የዚህ ሺያጭ ትርፍ ሙሉ በሙሉ ኢትዮጵያ ለሚከፈተው ቤተ መጽሐፍት ይውላል።
እናመሰግናለን!!


አድራሻችን 13831 MENLO AVE GARDINA, CA 90247

**ስልክ (310) 532—4177**

**የጽሑፍ መልዕክት ቁጥር (FAX ) 310—532–4619**

# ማ ው ጫ     CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

6 ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ (ገብርዬ)

8 ደብዳቤዎቻችሁ

12 ዜና

18 አይሰማም (ከጦራ ጦራ)

23 ትኩረት
- ኢትዮጵያና ችግሮቿ (አልታዬ ወርቅነህ)

25 ለውይይት
- "ለምሁርማ አርዮስም ምሁር ነበር!" (አማረ አፈለ – ሉስ አንጀለስ)

29 ልብ ወለድ – "ስጋት"

32 ትዝ ከሚለን . . .

34 ኑሮ በአሜሪካ
- ኑሮ በዘዴ (ከበደ ኃይሌ)
- የሴቷ ወይንስ የወንዱ (ገሊላ አያሌው)

37 ቋንቋችን
- የሥነ ቃል ሐብታችን
- ታሪክና ምሳሌ
- የግጥም ጉባኤ

43 ቢስቁም ባይስቁም

44 ዜና ቤተ ክርስቲያናት

46 ስንጠረዥ


በአሁኑ ወቅት በጦር ሜዳ እየተዋደቀ ያለው ወገናችን ለታላቅ ድል እንዲበቃ ጸሎታችን አይለየውም። ለእውነት የቆመ ኃይል ምንግዜም አሸናፊ ነውና "ድል ለአንተ ይሁን!!" እያለች የላንዳፍታ መጽሔት ምኞትዋን ትገልፃለች!!

ለሰላም
ለፍቅር
ለአንድነት
መደማመጥ
መቻቻል!


ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1999

ላንዳፍታ

የካቲት/መጋቢት ፲፱፻፺፩

፯ኛ ዓመት ቁጥር ፪

LANDAFTA

FEB/ARCH1998



አዘጋጅና አሳታሚ

መኮንን ገሠሠ

**Publisher/Editor**

*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editor:**

*Genet Wolde*

**Contributors:**

*Workayehu (pen name)*
*Gebrie (Pen Name)*
*Saefu Bishaw*
*Rev. Mekbib Atnaw*
*Kebede Bogale*
*Tora Totora (pen name)*

**Editorial Advisors**

*Lisanu Simret*
*Dr. Getachew Metaferia*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Dawit Deres*

**Distribution**

Atlanta, GA
California Mart
Express Food Mart
H & B Shop
Merkato Market
Sweet Auburn Grocery
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Wondwossen Yimer
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Denver, CO
Emebet Worku
Houston
Queen of Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Coffee Damera
London
St.Gabriel Ethiopian Delicatseen
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire News Stand
Santa Clara, CA
Nathan Graphics
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Lideta Market (Arlington)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu


# ከአዘጋጁ

እንደምን ከረማችሁ። እኛ ደህና ነን። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ያለውን የጦርነት ሁኔታ በተመለከተ ዜናዎችን እናጠናቅራለን በሚልና ጽሑፎችም በጊዜው ስላልደረሱን ይህ እትም ዘግይቶብናል። በየጊዜው ምክንያት አታጡም እንደምትሉን እናውቃለን። ለወደፊቱ በተቻለ መጠን በወቅቱ ለማድረስ አስፈላጊውን ሁሉ ጥረት እናደርጋለን።

የተፈራው አይቀሬ ሆኖ ይኸው አገራችን እንደገና በሌላ ዙር የጦርነት አውድማ እየሆነች ነው። የገነጠልኩት መሬት አይበቃኝም በማለት ተጨማሪ መሬትና ሌላም ሌላም ፍለጋ ጦሩን ሰብቆ የመጣውን የሻቢያ ጦር ለመመከት ወገናችን ዘርና ጎሣ ሳይለይ አንድ ላይ ወደ ጦር ሜዳው ተሟል። በዕብሪት የተነሣውንም ወራሪ በመቅጣት ትልቅ ትምህርት እንደሚሠጠው ሳይታለም የተፈታ ነው። ጥንት አባቶቻችን በጦርና በጎራዴ ብቻ የአገራችንን ሕልውና ጠብቀው ኢትዮጵያን ከቅኝ ግዛትነት አድነዋት ለእኛ አስረክበውናል። ይህ በአንድነት ላይ የተመሠረተ ሕዝባዊ ወኔ አሁንም በተግባር እየተተረጎመ ነው። ኢትዮጵያን ለመድፈር መሞከር ይህን ታሪካዊ እውነታ ባለማጤን የተሞከረ የዕብሪትና የጥጋብ እርምጃ በመሆኑ ወገናችን አስፈላጊውን ትምህርት እንደሚሰጥ እንተማመናለን። ምንም ዛሬ በአገራችን በኢህአዴግ አማካይነት በተግባር ለመተርጎም የተነደፈው የጎሣ ፖሊሲ ሕዝብን የሚከፋፍል ቢሆንም በዚህ ቀውጢ ጊዜ የታየው ወገን ያልለየ ሕዝባዊ ተሳትፎ የፖሊሲውን ኪሣራነት የሚያሳይ ሆኗል። ኢህአዴግም ከዚህ ሁኔታ ትምህርት እንደሚያገኝ አንጠራጠርም። በዚህም የብሔራዊ ዕርቅን አጀንዳ በአስቸኳይ እንደሚያቀርብ አንጠራጠርም።

በዛሬው እትማችን የዜናው ክፍል በአብዛኛው ጦርነቱን የተመለከተ ሲሆን ይህ መጽሔት ማተሚያ ቤት እስገባበት ድረስ ያለውን ሁኔታ ከተለያዩ የዜና ወኪሎች ያገኘነውን አጠናክረን ለማቅረብ ሞክረናል። ከዚህ በተረፈ አንዳንድ ጽሑፎች ጦርነቱ ከመነሳቱ በፊት የተዘጋጁ በመሆናቸው ምናልባት ከጦርነቱ መነሣት ጋር ልዩነት ቢያሳዩ እንደ ወቅቱ ሁኔታ እንድትመለከቱት እናሳስባለን።

ውድ አንባቢያን፤ የመጽሔታችንን ዕድገት በተመለከተ በስልክም ሆነ በደብዳቤ የምትሠጡንን አስተያየት በተግባር ለመተርጎም ሙከራ እያደረግን ነን። ወደፊትም አስተያየቶቻችሁ እንዳይለዩን አደራ እንላለን።


የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል

LANDAFTA

P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359

Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447

E-MAIL- landafta@aol.com

HOME PAGE:

http://www.ethiopic.com/landafta.htm



*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት

## ከወርቃየሁ (ሸገር)

ውድ ገብርዬ!

ለጤናህ እጅጉን እንደምን አለህ? እኔ/እኛ ቸርነቱ የማያልቅበት አምላክ ይመስገን በጣሙን ደህና ነን። ገብርዬ ለመሆኑ እንዴት ነህ? አዲሱ የፈረንጆች ዓመትስ እንዴት እያደረ ጋችሁ ነው? እያ ክሊንተንስ እንዴት እየሆኑ ነው ጃል! እናንተ የአገሪቱን ፕሬዚዳንት ህግ ፊት ካላቀረብኩ ሞቼ እገኛለሁ በሚል የዲሞክራሲ አገር ተቀምጣችሁ ምን አለባችሁ? መቼም እያ ክሊንተን ይህን ዲሞክራሲ የሚባለውን ነገር ባመጣባቸው ጣጣ መቼም ሳይረግሙት አልቀረም። የሆና ሆና እሳቸውም የዋዛ አይን አውጣ አይደሉም። አገሬን በደንብ እስካስተዳደርኩ ድረስ በእኔና በቤተሰቤ ጣጣ እናንተን ምን ዶላችሁ አይደል የሚሉት? የኛዎቹ አሉ አይደል እንኳን እነሱን ፍርድ ቤት ለማቅረብ ቀርቶ በአገራችን ጉዳይ እንኳ ምን አገባችሁ? እኛው ብቻ ነን የምናውቅላችሁ የሚሉን። ምን ታደርገዋለህ "ጊዜ የሰጠው ቅል ድንጋይ ይሰብራል" አለ የአገሬ ሰው።

ውድ ገብርዬ!

በአዲስ አበባ ቀን ከለሊት ሳይለይ ሲጨፈርባት ይታደራል። ለጦርነቱ መርጃ ገንዘብ መሰብሰቢያ እየተባለም የሙዚቃ ድግስ በየቀበሌው በየቦታው ይደረጋል። ኢሳይያስ ደግሞ "አዲስ አበባን በአንድ ቀን ነው የማጠፋት እያለ ይፎክራል ይዝታል።" ያም ሆኖ አስረሽ ምቺው አልቀነሰም። የዓለም የዜና አውታሮች ሁኔታውን እየተከታተሉ ቀን በቀን የሚዘግቡትን የጦርነት ወሬ ስታስቡና አዲስ አበባ ስትገባ ሁኔታው ሁሉ ይለይብሃል። በከተማችን የሚታየው ፈንጠዝያ ድሮ ጣልያን እኛን በወረረችበት ጊዜ በየመጠጥ ቤቱ እንደሚደነፋት አይነት ሆኗል። በየቦታው የሙዚቃ ድግሱ ሌላ ነው። – "ሉዐላዊነታችን መደፈሩ ተረስቷል? ወይስ ሉዐላዊነት ሲደፈር ሰው መጨፈር መዝፈን አለበት? ያኔ ስለ ህወሀት ስንሰማ ህወሀት ጦርነት ሊጀምር ሰሞን ወይም መመልመል ሲፈልግ ከበሮውን ይዞ የትግል ዘፈን እየተጫወቱ ሜዳ ይወጣል፤ ከዛም ጦር ይመለምላል ይባል ነበር። ዛሬ ግን ጦር ሜዳ ያለው ወታደር የሄደበትን ዓላማ ጭራሽኑ ትቶ በየጊዜው በሚሄዱለት የተለያዩ የአገሪቱ የሙዚቃ ባንዶች አማካኝነት መጨፈሩን ተያይዞታል። ይህን አስመልክቶ አንድ ጓደኛዬ ያለኝን ልንገርህ ባለፈው የገና በዓል ተገናኘንና "እስቲ ዛሬ እንኳ ወደ ፒያሳ ወጣ ብለን ጨፍረን እንግባ" ብለው "ትቀልዳለህ! ጭፈራ ያለው ባድሜና ሽራሮ እዚህ ምን ጭፈራ አለ?" ብሎኝ ጥሎኝ ሄደ። እንዳለውም አመሻሽቼ ቤቴ ገብቼ ቴሌቪዥን ብከፍት የሚታየው ባድሜና ሽራሮ ያለው ወታደር ሲጨፍር፣ ሲደንስ፣ ሾቤ ሲረግጥ ነው። እስቲ በፈጠረህ ሰው መሬቱን አስረክቦና በየዕለቱ የከባድ መሳሪያ ድምፅ እያንባረቀበት የተደሰተ ይመስል ይጨፍራል? እኛ አሁን እንኳን ጭፈራ ቀርርቶውም አያምርብንም። የሚያምርብን የተያዘውን መሬት በምንም ይሁን በምን ወደ ኢትዮጵያ ቀላቅሉ ከዛ እንኳን መጨፈር ... "እግዜር ጭፈራ ሲያምረው ... ያጠግባል" ይባላል፤ ይህቺ ጥጋብ ግን የደህንነት አትመስለኝም።

ገብርዬ! አንዳንዴ ሻዕቢያ ማለት ምንና ማን እንደሆነ እስከምንጠራጠር ድረስ የመንግስት ዜና አውታሮች ሊያደናግሩን ይሞክራሉ። ይህን ጦርነት የኤርትራ ህዝብ አይፈልገውም እንደውም ጠሩም ጭምር ይሉናል። ታዲያ መድፉን የሚያንባርቅብን ኢሳያስ አጉታችን ብቻውን ነው ማለት ነው? በተለይ "ከአስመራ አምልጠው መጡ" የሚባሉት ሰዎች የሚሰጡት አስተያየትም እርስ በእርሱ የሚቃረን ነው። በአንድ በኩል የኤርትራ ፖሊሶች ደብድበውን አሰቃይተውን ... ይሉናል። ወዲያው ደግሞ ሻዕቢያን ማንም አይደግፈውም፣ ጦርነቱንም አይፈልጉትም ይሉናል። እና ለማለት የፈለግሁት ዕውነታውን በመሸሽ ፀባችን ከኤርትራ መንግስት ጋር ብቻ ነው የሚባለው አባባል የኤርትራውያንን የድንጋይ ልብ ለማለስለስ ከሆነ ሞኝነት ይመስለኛል። ገብርዬ! ኤርትራውያን ምንም ይሁን ምን አመለካከታቸው አንድ አይነት ነው፤ ምሁሩ ኤርትራዊ ከጫካ በቀሉ የሻዕቢያ ፋና፤ የፋብሪካ ወዛደሩ ከቤት እመቤቷ፤ አለም በቃኝ ያለው መነኩሴ ከቡና ቤቷ ኮማሪ፤ ለማኙ ከናጠጠ ነጋዴው፤ በውጭ አገር የሚኖረው ኤርትራዊ አገር ውስጥ ካለው ኤርትራዊ የሚለያዩት በአኗኗራቸው እንደሆነ እንጂ ከኤርትራዊ ልባቸው የሚመነጨው ጠብ አጫሪነት፣ ራሳቸውን ከፍ ከፍ አድርጉ የማየቱ ጥንውትም ሆነ የኢትዮጵያና የኢትዮጵያውያን ጥላቻቸው አንድም መራራቅ የለውም። የሁሉም አንድ ወጥ ነው። ይንቁናል፣ ይጠሉናልም። ዛሬ ኤርትራውያኑ ለእኛ (ትግሬዎችን አይጨምርም) ያሰቡ ይመስል የችግሩ መንስኤ ከኤርትራ ሳይሆን ከትግራይ እንደመነጨ፣ ችግሩ የወያኔ ሀርነት የመስፋፋት ፖሊሲ የወለደው ነው እያሉ ሊነግሩን ሞክረዋል። እኛ ይህንና እንዲህ ያለውን የመስፋፋት ህልም እንደነበረ የሰማነው ዛሬ ሳይሆን ከአመታት ቀደም ብሎ ነው። እኛ ስንሰማ ግን የነገሩ ጥንሰሳ ጌሾ ወቀጣውና ብቅል ሰበራው ላይ የሻዕቢያ ሰዎች ግንባር ቀደም ተዋንያን እንደነበሩም ጭምር ነው የሰማነው። ይሄው ውጥን ምን ሰይጣን እንደገባበት ባይገባንም እነሆ ዛሬ ደግሞ ነገሩ ጨዋታ ፈረሰ ዳቦ ተቆረሰ ተብሎለታል። አቶ ኢሳይያስም ሆኑ ዶክተር ነን ባዮቻቸው፣ ባለህብቶዎቻቸውም ጭምር በገሀድ እያሳዩን ያሉት ከራሳቸው በቀር እኛ አንዳችም የራሳችን እምነት፣ አላማና ግብ እንዲያም ሲል እውቀት እንደሌለን ነው። አቶ ኢሳይያስ የኢትዮጵያን አንድነት የታደጉና ከመከፋፈል ያዳንዋት እሳቸው እንደሆኑ አሳምረው ውለታ ቢስነታችንን ነገሩን። – አቶ ገ/ተንሳይ ተድላም ኢትዮጵያውንን በሹካ መብላት ያስተማሩ እሳቸው ብቻ መሆናቸውን 'እኒህ ባላገሮች' የሚል ዘይቤ ይዘው የስድብ ውርጅብኝ አወረዱብን። ሌሎቹም እንደዛው። ካለፈ በኋላ መቆጨት እንዳይሆንብኝ እንጂ ኤርትራና ኤርትራውያን ከኢትዮጵያ አይገነጠሉም ብለን የፎከርንባቸው አመታት፣ ለእነሱ ፍቅር፣ ለእነሱ

ወገናዊነት ስንል የደከምነው ድካም፣ የፈሰሰው ደም፣ የተከሰከሰው አጥንት የወጣውን ወጪ ሁሉ ዛሬ ከንቱ እንደሆነ ሳስበው በጣም እቆጫለሁ።

ገብርዬ!

ዛሬ እኛ ከራሳችን አልፈን ያሰለጠናቸውን የሰው አገር ወታደሮችና መኮንኖች ማስመረቅ ይዘናል። ለራሳችን ሠራዊት ገንዘብ የለንም እያልን ህዝብ መዋጮ እየተጠየቀ በሌላ በኩል በአዋሽ አርባ የሩዋንዳ ወታደሮችን አሰልጥነን አስመርቀን ሸኘን። ጥይቶች አይደለን? ነገር ግን የራሳችንን መሬት ለ8 ወራት አስረክበን በትዕግስት እንጠብቃለን። ለምን? ይሄ ሁሉስ ልመና ለምንድነው? ምን የተደበቀስ ነገር አለ? ኤርትራ ይህን ቦታ በኃይል ከተቆጣጠረ 8 ወራት ያለፉት ሲሆን ይህ ወደ 400 እስኩየር ሜትር ስፋት ያለውን በወርቅ ማዕድን የበለፀገ ቦታ እንደ ትንሽ መሬት ታይቶ የሚታለፍ ባለመሆኑና የወያኔ ትዕግስተኝነት ከምን ችግር ወይም ተፅዕና የመጣ እንደሆነ በአንክሮ መገምገም አለበት። “መንግስታችን” ሰላም ፈላጊ መሆኑን የሚጠላ አልነበረም። ነገር ግን ሰላም ፈላጊ ለመሆንም እኮ ምክንያትና ጊዜም አለ። የራሱን መሬት አስነጥቆ ይህን ያህል ጊዜ በዝምታ መቀመጥ በኢትዮጵያ መሪዎች ታሪክ የሌለ ነው። አንድ የትግራይ ሴት ከዛሬ 3 ወር በፊት “ቦታው ላይ ልጅ ተረግዞ እስኪወለድ ነወይ የሚጠበቀው?” ብለው ድርጊቱን በቁጭት አውግዘው ነበር። እንደተባለው የተረገዘ ካለ ሊወለድ ተቃርቧል። የእኛ መንግስት ግን በዕለት ዜና ሪፖርቱ መብታችንን፣ ድንበራችንን፣ ሉዐላዊነታችንን ማስከበሩ ቀርቶ መርዶ ነጋሪ በመሆን በየዕለቱ ሻዕቢያ በህዝባችን ላይ የሚያደርሰውን የከባድ መሳሪያ ድብደባ፣ ያደረሰውን ስደት፣ መከራና የሰብዓዊነት ክብር መደፈር የመሳሰሉትን ያረዳናል፤ እንግሊዝ ሻዕቢያን ተቃወመች፣ ጣልያን እንዲህ አለች፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የእርቅ ሃሳብ አቀረበ፤ የአሜሪካው ፕሮፌሰር የሻዕቢያን ድርጊት አወገዙ፣ ... የተባሉት ዲፕሎማት ስለእርቁ ድርድር ለመወያየት አዲስ አበባ ገቡ፣ አሥመራ ሄዱ ... የሚል የሰለቸና ፋይዳ የሌለው ወሬ ከማውራት በስተቀር የሚለን ነገር የለም። ከወራት በፊት “በኃይልም ቢሆን ሉዐላዊነታችንን እናስጠብቃለን” ተብሎ በመሪዎቻችን እንደበት የተነገረው እቡነ ዘበሰማያት ገቢራዊ አለመሆኑ “ምን ይጠብቃሉ?” ወደሚለው መሰረታዊ ጥያቄ አምርቷል። “ክረምቱ ይውጣ ተባለ ክረምቱ ወጣ፣ የአአድ ሽምግልና ውጤት ካልመጣ በጦርነቱ እንገፋለን ተባለ ከአንዱም ሁለቴ ምንም ፋይዳ እንደሌለው ታየ – እነሱ በበኩላቸው እየጠበቅናችሁ ነው እናስተናግዳችኋለን ብለው እስከሚያሾፉብን ድረስ ግን ትዕግስት አለን እኛ። እንደገናም ስንጠብቃችሁ ካልመጣችሁ እኛ ጀምረነዋል ብለው ሲወጉንም በከባድ መሳሪያ ሲደበድቡንም ትዕግስት አለን እኛ። ያ “ተራራውን ያንቀጠቀጠ ትውልድ” ተብሎ በሁለት ገቢር የተፃፈለት ትውልድ ገና 10 ዓመት እንኳ ሳይሞላው ወኔውን ዛሬ ምን ሰለበው? ነው ወይስ ተራራውን ያንቀጠቀጠው ሻዕቢያ ነበር? ይሄ የሁሉም ሰው ጥያቄ ነው።

ዛሬ በወያኔ አመራር አካላት ዘንድ ያለው ችግር ምንድነው? የሚለው መጠይቅ በህዝብ አንደበት እየተብላላ ይገኛል። በስልጣን አካባቢ ግልፅ ያለመሆን ስሜት መስተዋሉ በህዝብ ብሔራዊ ስሜት ላይ የፈጠረው አንድምታ መኖሩ አይካድም። የኢትዮጵያ ህዝብ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን የመሪዎቻችን ትዕግስት ከምን ሊመነጭ እንደቻለና ከህዝብ ለሚነሳው የተለያየ ጥያቄ በቂ ምላሽ የሚያስገኝ ትንተና አለመስጠቱ ሌላው አጠያያቂ ሆኗል። ለምን ዝም አሉ? የምትለውን ነጥብ ይዞ የተነሳ ማንኛውም ተጠራጣሪ ሌሎች ብዙ ነገሮችን እያነሳ የባሰ ሊጠይቅና የባሰውን ሊጠራጥር ይችላል። አገሪቱን ለተመጽዋችነት ያበቃው ኢህአዴግ በጥያቄ ምልክት ውስጥ ያለው የአገሪቱ ኢኮኖሚ፣ ማህበራዊ ችግሮችና የሉአላዊነት ሁኔታ በተራ ፕሮፖጋንዳ፣ በነአቶ መለስ ዜናዊ የሰለቸ ሽንገላና በኢኮኖሚስቶች የቸከ ትንተና የማይለወጥ በመሆኑ፣ ከቃል ይልቅ ተግባር ሊለውጥ እንደሚችል መገንዘብ ያለባቸው ይመስለኛል።

ገብርዬ! ማንኛውንም አገር ወዳድ ለማሳሰብ የምወደው እነ ወያኔ ስልጣናቸው ለማደላደል ሲሉ የማያደርጉትን እናደርጋለን፣ ያልሆኑትን ነን በማለት ህዝብን በማደናገር የተካኑ ስለሆኑ በአሁኑ ጊዜ ከሻዕቢያ ጋር ያላቸውን ሽኩቻ ህዝቡ በጥንቃቄ ሊገመግመው ይገባል። የወቅቱን የድንበር ግጭት የስልጣን ዕድሜያቸውን ማራዘሚያ፣ ለገንዘብ ማሰባሰቢያና የተቃዋሚ ኃይሎችንም ከሚያካሂዱት ፀረ–ወያኔ ትግል ‘አገር ተወረረች’ በማለት ማዘናጊያ አድርገው ለጠባብ አላማቸው እንዳይጠቀሙበት በጥንቃቄ እያንዳንዱን እርምጃቸውን መመርመር ይገባል። የአገራችን ብሔራዊ ጥቅም ለዘለቄታው በአስተማማኝነት ሊከበር የሚችለው ዛሬ በጥቅም የተጋጩት ሻዕቢያና ወያኔ ሁለተኛ በህዝባችን ላይ ተባብረው እንዳይነሱባት እንደተነጣጠሉ እንዲቀሩና የስልጣን ዕድሜያቸውን በአጭሩ በመቅጨት ለህዝብ ተጠያቂነት ባለው አስተዳደር በነዚህ በህግ ልዕልና በማያምኑ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች የሆኑ መንታ ቡድኖች መቃብር ላይ መመስረት ሲቻል ነው። ከዚህ ትግል ጐን ህዝቡ የወያኔ መንግስት የደቀነበትን የጐሳ የፖለቲካ ጋሬጣ አንስቶ አመቺ የሆነ ሁኔታ በመፍጠር በወያኔ ላይ የተጠናከረ ግፊት ማድረግ ያስፈልጋል። መሪዎች በድብቅ ሲዶልቱ ህዝቡ በሀገሩ ጉዳይ አምባገነኖች የሚዶልቱትን መመርመርና መተንበይ ብሄራዊ ግዴታው ነው። ባለፉት 8 ወራት የተከናወኑት ድርጊቶች እነዚህንና ሌሎችንም ጥርጣሬዎች የመፋቅ ኃይል እንደሌላቸው ታይቷል።

ገብርዬ!

የወያኔ መንግስት በየጊዜው ድርድር ድርድር እያለ ከሚያሰማው ተባራሪ ወሬ ሌላ ለድርድሩ በቀረቡ ሁኔታዎች ላይ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚያውቀው ነገር የለም። የድርድሩ ጉዳይ ምን እንደሆነ ዝርዝሩም ምንን እንደሚያካትት የተገለፀ ነገር የለም። ስለኢትዮጵያ ህዝብ ጉዳይ በኢትዮጵያና በጠላቶቿ ላይ ለሚደረግ ማንኛውም ድርድር ምስጢረኞቹ እነ አንቶኒ ሊክ ናቸው፣ እነ መለስ ዜናዊ ናቸው። ህዝቡ ተራ ተመልካች ነው። ህዝብ የመጠራት መብት ያለው በመዋጮ ጊዜ ለማጨብጨብና መዋጮ ሲያስፈልግ ብቻ ነው። እርግጠኛ ነኝ የኢትዮጵያና የኤርትራ ድንበር የት የቱ ጋ እንደሆነ ብዙ ኢትዮጵያዊ አያውቀውም። ህወሐት በየጊዜው እየቀደደ ከሚሰፋው ድንበር ሌላ ህዝብ የራሴ ድንበር ነው የሚለው ነገር የለውም። – ነገ ተነገ ወዲያ እነመለስ “ተደራድረናል – እንዱን ለኤርትራ ሰጥተን እንደኛውን ወስደናል” ቢሉ የህዝቡ ድርሻ ማጨብጨብ ሊሆን ይችላልና ኢህአዴግ የህዝብ መድረኮች ሊያዘጋጅና ስለድርድሩም ሆነ ስለጦርነቱ ሁኔታ ህዝቡን ማወያየትና

ማነጋገር ይገባዋል ባይ ነኝ።

ወዳጄ ገብርዬ!

ዛሬ፣ 7 ዓመት ሙሉ በኢትዮጵያ ህዝብ ለደረሰው በደል ሁሉ ተጠያቂው ሻዕቢያ ሆኗል(አድርገውታል)። የቤት ኪራይ እንዲጨመር ያደረገብን ሻዕቢያ፣ መሬት በሊዝ እንዲሆን ያደረገብን ሻዕቢያ፣ የጉምሩክ ቀረጥ እንዲጨምር ያደረገብን ሻዕቢያ፣ የአገር ውስጥ ገቢ ቀረጥ እንዲደረግብን ያደረገ ሻዕቢያ፣... የኢህአዴግ ኤልኒኖ ሻዕቢያ ሆኖ ሁሉንም ነገር በእነሱ እያሳበቡ ነው። ዛሬ 'ትምክህተኛ' የሚለውም ቃል 'በሻዕቢያ' ተተክቷል። ትምክህተኛው፣ ነፍጠኛው ነፍጡን እንዲያነሳ የሚፈለግበት ጊዜ ነውና ቋንቋው እንደጊዜው ተቀይሯል። "ያልፈሳንበት ዳገት የለም አለች አህያ" ሁሉንም ግን እኛ እናውቀዋለን። እውነት ሻዕቢያ ከሆነ እንዲህ ያደረገን ኢህአዴግ መንግስታችን ያለአግባብ በህዝቡ ላይ የተጫኑብንን ጫናዎች በሙሉ ያንሳልንና፤ የዛኔ እውነትም ...

ውድ ገብርዬ!

ደርግ በሩሲያ መሳሪያዎች (የዚህ ዕዳ ገና ከጫንቅላታችን አልወረደም) አስራ አምስትና አስራ ስድስት አመታት ተጠቅሞባቸዋል። በእነዚህ አመታት ውስጥ የወደቁት ከ3 አይበልጡም። ያለፈውን የ6 አመት ብክነት ልተወውና ከአሁኑ ከኢትዮጵያና ከኤርትራ ግጭት በኋላ ብቻ ከ6 በላይ ጀቶች ከጥቅም ውጪ ሆነዋል። በቅርቡ ወደ አንድ ሚሊዮን ዶላር አውጥተን የጦር መሳሪያና አውሮፕላን ተገዝቷል ያው በተለመደው ብድር እንጂ በነፃ እንደማናገኘው ርግጠኛ ነኝ። ታዲያ ይህን በብድር ያመጣነውን እንደልማዳችን ከተራራ ጋር እያጋጨን ከጥቅም ውጪ የምናደርገው ከሆነ ኖሮም ላንኮራበት ተዋግተን ላናሸንፍበት ከሆነ ትርፋችን በዕዳ ጫና መጉበጥ፤ ስራችን ታጥቦ ጭቃ ነው የሚሆነው። ገብርዬ! የትኛው ጦርነት ተካሂዶ ሁለተኛው ጦርነት ላይ እንደደረስን ባይታወቅም የአንደኛው ዙር ሲቪል የህክምና ዘማቾች ግዳጃቸውን ጨርሰው ሰሞኑን ወደየምድብ ቦታቸው እየተመለሱ እንደሆነ ተነግሮናል። እንዲሁም አንደኛው ዙር የዕርዳታ ማሰባሰብም ፕሮግራም አብቅቶ ሁለተኛው ዙር የእርዳታ አሰባሰብ ሰሞኑን ተጀምሮ ቅስቀሳውም ሆነ መዋጮው ተጧጡፎ ይገኛል። ገንዘቡ ለምንና ለማን እንደዋለ የሚታወቅ ነገር የለም።

ወዳጄ ገብርዬ! አገር ለመምራት እኮ ብልህነትንና የህዝቦችን የልብ ትርታ ማድመጥ ይጠይቃል። በአንድ ወቅት አፄ ምኒሊክ ግብር እንዲጨመር ካዘዙ በኋላ ከረምረም ብለው "ህዝቡ ምን አለ? አረኛስ ምን ይላል?" ብለው ይጠይቃሉ። "ህዝቡ በጣም ተቆጥቷል፣ አረኛም የሚገልጸው ይህንኑ ነው" በማለት በጊዜው የመረጃ ስልት የሰሙትን አማካሪዎቻቸው ይገልጡላቸዋል። አፄ ምኒሊክም "ተዉት የአገሬ ህዝብ ከተቆጣ ቂም አልያዘም ማለት ነው ይላሉ"። እንደገና በዓመቱ በተመሳሳይ ግብር እንዲጨመር ካደረጉ በኋላ ከረምረም ብለው "ህዝቡ ምን አለ? አረኛስ ምን እያለ ያዜማል?" በማለት ሲጠይቁ፤ "ህዝቡ ዝም ነው ያለው ቁጣውን ትቷል፣ አረኛውም ስለተጨመረው ግብር አያነሳም" በማለት አማካሪዎቻቸው ይነግሯቸዋል። አፄ ምኒሊክም "የአገሬ ህዝብ የተቆጣው አሁን ነው። ዝምታው ቁጣ ነው" በማለት ሁለት ጊዜ የተጨመረውን ግብር እንዲነሳ አዘዙ ተብሎ ይነገራል። ዛሬ የኢትዮጵያ ህዝብ በዝምታውና በትዕግስቱ ያገኘው ድል ቢኖር፤ ተረስቶ የነበረውን የጥንት አባቶቹን ጀግኖችና አርበኞች ስም በየዕለቱ እንዲጠራ ማድረጉና "ጨርቅ" ተብሎ የነበረውን የኢትዮጵያ ባንዲራ እንደገና በየቦታው ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ ማድረግ መቻሉ ነው። ገብርዬ! ባይገርምህ ዛሬ የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቲቪ ለ7 ዓመታት የረሳናቸውን ቀረርቶና ሽለላዎች፣ ኢትዮጵያችንን የሚያወድሱ ዘፈኖች ማስደመጥ ጀምሯል። ይህ የጊዜው ድላችን ነው፤ ሌላ ሌላውን ደግሞ ወደፊት እናየዋለን።

በቸር ይግጠመን ወርቃየሁ ነኝ – ከሸገር

# ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ

## ከገብርዬ

ባላገር ወርቃየሁ!

እንዴት ሰነበትክ። አንተስ በሀገር ነህና ብትደኸይም ስቃዩ ቢበዛብህም የሀገር ፍቅር ስሜትህ ከምታየውና ከምትኖርበት ሁኔታ የተነሳ አይቀንስም። እንዲያውም ለሺህ ዓመታት እንደሚንተገተግ ጠበል እየፈላ የበረዳቸውን ያሞቃል፣ መድኃኒትም በመሆን የመዳን ተስፋን ያጐናፅፋል። ባላገሩ ጋንዲ እንዲያው በቁመና ባላውቅህም ስሜቱ እንዳንተ ነበር። ባንድ ወቅት ቅርበኞቹና ጓዶቹ እንጂና እንኳ ከእንግሊዙ ምስለኔ (Viceroy) ጋር በመሆን ነገር ይሰሩበት ነበር። እንዲያው እንደምገምተው የአውሮጳውን ልብስ ጥለህ እንደባላገሩ ሱሪና ነጠላ ለብሰህ የዕለት ስራህን ብትሰራ እንዴት ደስ ባለኝ።

ከእኛ ብዙ አትጠብቁ። የአመፅና የማንቂያ ሥራ ተጀምሮ ትክክለኛ ዴሞክራሲ የሚገነባው እዚያው ባለው ህዝባችን ነው። ጠበቃውና ባላገሩ ጋንዲ ለንደን ወይም ኬፕታውን ተቀምጦ በሩቅ ቁጥጥር የፖለቲካ ትግል ማካሄድ አቅቶት አይደለም ህንድ ተመልሶ ምልዐተ–ህዝቡን ያስተባበረው። ለዚህም ትግል ባላገሩና ህዝብ አፍቃሪው ምሁር ከጉኑ ተሰልፎ ነበር የዓለምን ህዝብ ልብ የማረከው። አየህ ሺህ የፖለቲካ ድርጅት ፍልፍል ከመፈልፈል አንድ እንደ ጋንዲ ያለ ጀግና ማፍራቱ ይበጃል። ህዝቡ በርሱ ዙሪያ ይሰባሰባል። ክርስቲያኑም እስላሙም። ብዙ ደጋፊ ስለሚኖረው አንዱ ተማርኩ ባይ ኃይል አሰባስቦ በጭንጋፎ አይጥለውም። ከህዝቡም ውስጥ ስለበቀለ ህዝብን ከችግር ለማውጣት አይፈላሰፍም፤ እንደህዝቡ እየኖረ ህዝብን ያስተምራል። እንደባላገሩ ጋንዲ ማለት ነው። ባለፉት 40 ዓመታት የኢትዮጵያን ምሁር ክፍል ስንመረምር ጠባዩን በሦስት ደረጃ ከፍለን ማየት እንችላለን። 1ኛው ወገን ለጉጂ የመንግሥት ፖሊሲዎች ተሸካሚና አገልጋይ የሆነ እኔ ከሞትኩ ሰርዶ አይብቀል የሚል ጥቅም አስጠባቂ ክፍል ነው። ይህም በእኛና ሶሚየት ህብረት የታየው ዓይነት ዕቡይ መደብ (Nomenclatura) የሚባለው ነው። ይህም ዕቡይ መደብ እንደየሀገራቱ ልዩነት የራሱ የሆነ ልዩ

ጠባይ ይዞ ይገኛል። ለምሳሌ በሞቡቱ ዛየር ጊዜ በነአይኤምኤፍ (IMF) እና የዓለም ባንክ ብድርና መስተዋፅዖ የደለበው ሲያሰኘው በጉሳ ከፈለገም በቤተሰብ ተደራጅቶ የነበረው እኩይ መደብ (Cleptocracy) የተባለው ነበር። ዕቡይና እኩይ ምሁራን በቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት በሁለቱ ኃያላን መንግሥታት ገመድ እየተጉተተ በራሱ ቅጥፈት የሚሰቃይ፣ እነደሟች በቅሎ ሳሩን ለመብላት ገመዱን ላለማሳጠር ሌት ተቀን የሚተጋ ገመዱ ካጠረበትና ቀን ከጨለመበት የሚረሸንና በሐፍረትና በሙስና ከሥልጣኑ ተንከባሎ በተፈለገው ጊዜ ሲባረር ጥፋተኛ ነኝ በማለት በጌቶቹ ማይክሮፎን ፊት ራሱን የሚወቅስ ክፍል ነው። ይህ ክፍል ውጭ እንኳ ቢሰደድ የሚሰራው ለራሱ ዝናና ጥቅም ነው። በተቻለ መጠን የህዝብን ፍላጐት በተመቸው ጊዜ ሁሉ እንዳመትበዓል ዶሮ ጠምዝዞ ለእርሱ ፖሊሲ ጭዳ ያደርገዋል።

2ኛው ደግሞ ሙያውን እየቸረቸረ "ሥጋና ቅቤ ከሌለህ የባቄላ አሹቅም ፕሮቲን ስላለው በእርሱ መተካት ትችላለህ" ብሎ እንደሚያስተምረው የምግብ ሊቅ የድህነት ዘለዓለማዊነትን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚሰብክ የህዝብን የከፋ ሁኔታ ለመቀየር የማይታገል ሆዳም ምሁር ነው። * እዚህ ላይ ከባቄላም ፕሮቲን ወይም አልሚ ምግብ ይገኛል። በምዕራቡ ዓለም ሰዎች ሲደልቡ ሥጋና ቅቤን ትተው ወደ እህልና ቅጠላ ቅጠል ምግብ ያዘወትራሉ። በመሰረቱ የባቄላ አሹቅና የኑግ ዘይት መመገብ ነውርም ሆነ ስህተት የለውም። ስህተቱ የሚመጣው የኑግ ዘይት ዘለዓለማዊነት ሲሰበክ ነው። ለምሳሌ የወያኔ ካድሬዎችና ደጋፊዎች በዓመት በዓልና በሌላው ቀን ሥጋና ቅቤ ሳያጥራቸው እየደለቡ ከሄዱ የሌላውን የአዲስ አበባ ህዝብ አንተ ቅቤ ስለተወደደ ኑግ ብቻ ብላ፣ ኑግ ለጤንነት ጥሩ ነው ብሎ መስበኩ ፍትሐዊ አይደለም። የህዝብ ምሑር ኑግም ብላ ብሎ እያስተማረ ፍትህ እንዲመጣ ህዝብን ማስተማርና ማታገል ይገባዋል።

3ኛው የምሑር ክፍል የነቃ መደብ (concious or vocal or troublemaker) የሚባለው ለፍትህና ለህዝብ የሚከራከር፣ የሚረሸን፣ ስይል የሚፈፀምበት፣ የሚታሰር፣ የሚያደራጅ የሞራል አባት ነው። በሦስተኛው ዓለም የዚህ የምሑር ክፍል እጅግ የዋህ፣ ዓለማዊ ግብና ምኞት ያለው (idealist)፣ በፖለቲካ ቀመር (political calculation) የገረረ ስላልሆነ በሌሎች ወንድም/እህት የምሑራን ክፍል አስተባባሪነት ቶሎውኑ ይመታል። ዴሞክራሲ ባላንሰበበት የሦስተኛ ዓለም የተነሳው ይህ ሐቀኛ የምሁር ክፍል ብዙውን ጊዜ የጠላትን የኃይል አሰላለፍ ስለማይረዳ የትግል ስህተት በመፈፀም የእሳት እራት ሆኖ ይወድማል።

4ኛው የምሑር ክፍል ከሁሉም ጠቃሚውን ትምህርት የቀሰመ ብዙውን ጊዜ ለምሳሌ በአሜሪካና በሳውዝ አፍሪቃ እንደታየው በእምነትና በባህል አካባቢ ተሰባስቦ የሚቀሰቀስ፣ ለውጥ የሚያመጣና የሚያታግል ነው። (ምሳሌ፦ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ ሊቀ ጳጳስ ዴዝመንድ ቱቱ፣ ማልኮለም ኤክስ፣ ... ወዘተ)። የረሀብ አድመኛንና ሰልፈኛን በጥይት በሚቆላ ሀገር ህዝብ ከዳር እስከዳር ካልተንቀሳቀሰ የተቃውሞ እርምጃን መውሰድ አደገኛ ነው። በወያኔ ላይ ዶክተር አስራት ያደረጉት የረሐብ የተቃውሞ ትግል በየጊዜው በኃይል በጉሉኮስ መርፌ እንደከሸፈ ሰምተናል።

ወዳጄ ወርቃየሁ፦ ከዚህ በታች ያለውን ለምሳሌ የቀረበውን የሳይኮሎጂ ስዕል መርምረው። ረጋ ስራሹና ችኩሉ ምሁር ባንድ ወጥ አመለካከት ዋንጫውን ብቻ ነው የሚያየው፤ ሌላው ወገን ደግሞ ሁለት ፊት ሊያይ ይችላል። ይህንን ምሳሌ ያነሳሁልህ የተመራማሪን ምሁር ሁሉን መርማሪ ጠባይ ለማሳየት ነው እንጂ ይህች ትንሽና ተራ ስዕል ሁሉን ነገር ታሳያለች ከሚል አይደለም፤ ጉበዝ ታዳጊ የ5ኛ ክፍል ተማሪም ሊገመግማት ይችላል።

የኔ ውድ፣

ከፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ በኦርቶዶክስ ኃይማኖት ዙሪያ የተሰባሰቡት ምዕመናን ለኢትዮጵያ አንድነትና ትግል አዎንታዊ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ ብዬ እገምታለሁ። የኢትዮጵያ የእስልምና ኃይማኖትም እንደዚሁ። እየሀ ያኔ የነፃነት ስነመለኮትን (Liberation Theology) ሳነሳ የትግላችንን ድክመት በመመርመርና የቱ ድልድይ ለግባችን ዐቢይ አስተዋጽዖ እንደሚያደርግ ለሌሎች ለማሳየት ነበር።

ዛሬ በላቲን አሜሪካ ሀገሮች የግፉዐኑን ትግል የሚያቀጣጥሉት ከሮማው ፓፓ የወጡ ታጋይ ቀሳውስት ናቸው። የእነዚህም እምነት በሐዲስ ኪዳኑ የእየሱስ መልዕክት ላይ የተመሰረተ ነው። ግፍ፣ ውሸት፣ ባርነት፣ መለያየትና ሌሎችም እነዚህን ሁኔታዎች በመሰረታዊ ሁኔታ የሚያስፋፉ የኃጢያት መዋቅሮች ባሉበት (structural sins) ቦታ ሁሉ እየሱስ ዛሬ ቢመጣ ይታገላል መዋቅሩንም ይሰባብረዋል። የዚህ መዋቅር መንስዔ የውጭ የካፒታሊስቶች ብድርና ድርጐ ነው። የዓለም ባንክና አይኤምኤፍ በመዋቅራዊ ማስተካከል (Structural Adjustment) ስም ልዩ ልዩ ህዝብን የሚጐዱ ፖሊሲዎችን በአሻንጉሊት መንግሥታት ኃይል ያስፈጽማሉ። እነዚህ የማብቃቂያ እርምጃዎች (austerity measures) የሚከተሉትን ሁኔታዎች ይፈጥራሉ። ሠራተኞች በግፍ ይባረራሉ፣ የብሶት አድማን ለመቆጣጠር በመንግሥት ፖሊሶች ግድያ፣ አፈናና ስይል በህዝቦች ላይ ይፈፀማል። እናቶች ልጆቻቸውን ለመመገብ ሴተኛ አዳሪ ይሆናሉ፣ የመጠጥ ኮማሪነት ይበዛል፣ ታክስ ይጨምርና የብድሩ አራጣ መከፈል ይጀምራል – ዋናውማ በርካታ አመታትን ይጠይቃል። በዚህ ብድርና ገንዘብ የሚደልቡት ቅድም የጠቀስኳቸው ዓይነት የምሁር ክፍሎች፣ በጉሳና በቤተሰብ የተቃቀፉ የዘር ካድሬዎች፣ የመንግሥት ባለሥልጣናትና የወታደሩ ክፍል ናቸው። በኢትዮጵያም ሁኔታው ከዚህ የተለየ አይመስለኝም።

ወዳጄ ወርቃየሁ፣

ቤተክርስቲያንን ለመምታት ማንኛውም አምባገነን ሥርዓት ይከብደዋል። ቤተክርስቲያን ግፍንና መከፋፈልን ለማስወገድ ልክ እንደማርቲን ሉተር ኪንግና እንደነዴዝመንድ ቱቱ በህሊና ትግል የወያኔን መንግሥት ማጋለጥ መቻል አለባት። ለዚህ ከፍተኛ መስዋዕትነት የተዋሀዶ ክርስቲያን ምዕመናን የእየሱስን ዕጣ ለመቀበል ዝግጁ መሆን አለባቸው። የላቲን አሜሪካ ያሁኑ ተመክሮ ባጭሩ ልግለጥልህ። የክርስትያን ምዕመናን መሠረታዊ ማኅበራት (Basic Christian Communities) አላቸው። አንዳንዶቹ እንደሁኔታው ግልጥ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ህቡዕ ናቸው። በአጠቃላይ ኅብረተሰበዊ ችግሮች ላይ ከአምልኮ ሥርዓት በኋላ ይወያያሉ። መፍትሔ ይፈልጋሉ። ለሰብዓዊ መብት በደብዳቤና በሰልፍም ይታገላሉ። ቤተክርስትያናችንም ፍትህን በማስተማርና ለፍትህና ለሀገር አንድነት በማታገል ሳውዝ አፍሪቃ

እንደተደረገው ያለንን የጉሳ መዋቅራዊ ኃጢአት መስበር ትችላለች። ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ይህ አዲስ ነገር አይደለም። የአደዋና የማይጨው ትንግርቷ ትልቅ ምክስርነት ነው።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

በዚህ ባለፈው ክሪስማስ ለኢትዮጵያውያን ለነቤቢና ቼቼ የክሪስማስ ስጦታ የሰጡ በርካታ "ሥልጡናችን" በዓይኔ አይቻለሁ። እዚያም ይህ ሁኔታ ሳይጀመር አይቀርም። እዚህ አንድ አባት እንዳስተማሩን የድኃውን የኢየሱስ ትምህርት ጥለን የሀብታሙን የዶላር ኢየሱስ እያመለክን ነው። ሌላው ቀርቶ የህፃኑ ኢየሱስ በሳር የተጉዘጉዘ የፕላስቲክና የእንጨት ማኖሪያ ክፍት ሳጥን ማሳያ እስከ $50 ዶላር በሚደርስ ገንዘብ ገዝታ ቤቷ የክሪስማስ ዛፍ (አርተፊሽያል ነው) ያኖረችውን ጉረቤቴን የዘበኛ ጋረደውን ልጅ አውቃታለሁ። ያኔ በ1974 ሡንጋ ተራ ነበሩ፣ ጡረታ ወጥተው። ዛሬ በህይወት ይኑሩ አይኑሩ አላውቅም። እንግዲህ ሀገር የሌለን ባላገሩን ስንሰድብ ይደንቀኛል። እስቲ አንድ ቀን ሁለት ሆነን ስንከራከር አንዱ ምሑር ራሱን በመውቀስ ከነገረኝ ውስጥ መርጬ በግጥም መልክ ላቅርብልህ፤ የግጥሙ ርዕስ "የፓላሚኖ ምሑር ፀፀት" ይላል። እኔ ገብርዬ ዘመቻ የማደርገው ሆዳምና ዕኩይ ምሑር ላይ እንጂ ሀገር ወዳድና ለኢትዮጵያ ህዝብ ጊዜውን፣ ሐብቱንና ህይወቱን የሚሰጠው ላይ አይደለም። እነሆ ትንሿን ግጥም።

## የፓላሚኖ ምሑር ፀፀት
## (ባላገር ባለድግሪ)

አገር ሳይኖረኝ ተበትኜ ፥
በስደት ንዴት ተግኜ፤
እንደቺቺሊ ቦሎኛ ፥ ባንኮኒ ላይ የምተኛ
ነገሬ ሁሉ ቶረኛ ፥ ለተነሳው ሁሉ ቀበኛ
ወይኔ እኔ ምቀኛ – የፍርደ–ገምድል ዳኛ።
ጣፊያ መሰል ድግር ይዤ ፥ ተኮፍሼ ተጉዝጉዤ፤
ለምን ይሆን እኔ ፈሪው ፥ ባላገሩን የምንቀው
እንደኔ ባይማር እንኳ –
እርሱም እኮ አገር አለው!
ማህተቡን ያልበጠሰ ፥
ቁምነገሩ ያበው ነው።

መረን ተለቆ ያልጠፋ ፥
እንደባላገር ጋንዲ ተሰፋ
ወኔን ሁሉ የሚያፋፋ፤
ተነፋነፍ አጥልቆ ፥ በጀ ጠባብ አምሮ ደምቆ፣
ጋቢ መሳይ የደረበ ፥ ላንድነቱ የቆረበ
ታሪኩን ያነበበ።
እርሱ ነው እንጂ ታታሪ ፥ ወግ አክባሪ አስከባሪ
እንደምኒሊክ ተፈሪ ፥ የዲፕሎማሲ ተጠሪ።

ዶጋመድ ያልሆነበት ፥ መከሩ ያልተነረተ
በፈረንጅ ደማሚት ውቃት ፥ ሰብሉ ያልተመረተ
እርሱ ነው እንጂ ባላገሩ ፥
በፈረንጅ ቃል ያልቃተተ
ባለድግር ታራ ፥ የሥልጣኔ ፈጣሪ
እርሱ እንጂ ባለድግሪ ፥ ሚስቱም ሁሉ መካሪ
እንደጣይቱ የቤት መሪ ፥
ያች አልማዝ – ያች ድሪ።

ቸር ይግጠመን
(ገብርዬ)

# ደብዳቤዎቻችሁ

ለተከበራችሁ ውድ ላንዳፍታዎች እንደምን አላችሁ። በህዳር ወር በወጣው የኢትዮጵያን ሬጅስተር መጽሔት ላይ "በህግ አምላክ ጳጳሳት" በሚል የተጻፈ ጽሁፍ ሁላችንም አንበናል። ለዚህም በጽሁፉ የተጠቀሰው በዴንቨር ኮሎራዶ የሚገኘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ሲሆን ለዚህ ቤተክርስቲያንም አባቶቻችን ዴንቨር በመጡበት ጊዜና አሁንም የያዝነው ዓመት 1998 ዓ.ም እስኪ ልያቅ ድረስ የቤተክርስቲያኑ የሰበካ ጉባኤ (የቦርድ) ዋና ጸሀፊ ሆኜ የማገለግል በመሆኔ በቤተክርስቲያናችን ላይ የተሰነዘረውን አግባብ የለሽ ክስ መልስ ለኢትዮጵያን ሬጅስተር ልኬ በታህሳስ ወር እትማቸው ሳያወጡት በመቅረታቸው የመጽሄታቸው አንባብያን ከሁሉም አቅጣጫ የሚሰነዘሩትን አስተያየቶች እንዲያውቁ መጽሄቱ መብታቸውን ስለገፈፈ ለኢትዮጵያን ሬጅስተር የላከኋቸውን ሁለት ደብዳቤዎች በመጽሄታችሁ ታወጡልኝ ዘንድ በትህትና እጠይቃለሁ።

ብርሃኑ ዓለም
የዴንቨር ኮሎራዶ የኢት. ኦርቶዶክስ
ተዋህዶ ቅድስት ማርያም ቤ/ያን የሰበካ
ጉባኤ ዋና ጸሀፊ

## ለኢትዮጵያ ሬጂስተር

### ሳልተነፍስ እንዳላልፍ ብዬ እንጂ እናንተስ ታዳላላችሁ!!

ለኢትዮጵያ ሬጂስተር — የታህሳስ ወር እትማችሁ የሚደርስ አስተያየት "በህግ አምላክ ጳጳሳት" ብላችሁ ለጻፋችሁት መልስ መስጠቴን ታውቁታላችሁ። አንባብያን እንዳያውቁት በመፈለጋችሁም አስተያየቴን ከማውጣት ተቆጥባችኋል። ልያችሁ ብዬ እንጅ እንደማታወጡት እርግጠኛ ነበርሁ። ሆኖም ግን በየወሩ በሚወጣው መጽሄታችሁ ገጽ አንድ ላይ "We advise contributors not to send us articles that have been submitted to other magazines" ብላችሁ ስለምትማጸኑ ያን ለማክበር ስል የናንተን የታህስስ ወር ዕትም ለመጠበቅ ተገደደሁ።

ይህን በስደት ምድር ላይ ፈጣሪውን በመለመን ላይ ያለን ክርስቲያን ህዝብ መሰባሰቢያ አገኘ ብላችሁ ለመከፋፈል የሰነዘራችሁበትን በትር ለመከላከል በተጨባጩ የማውቀውን አስተያየቴን በመሰንዘሬ አስተያየቴን ግፈናችሁ አንባብያን ትክክለኛ ፍርድ እንዳይሰጡና ስለጉዳዩ ሙሉ እውቀት እንዳይኖራቸው ለማድረግ ሞክራችኋል። ይህ ደግሞ የማታ ማታ መጽሄታችሁንም ሆነ ግለሰቦችን ይጐዳል። ምክንያቱም እውነት ልትዘገይ ብትችልም መውጣቷ አትቀርምና ነው።

በህዳር ወርም ሆነ በታህሳስ ወር "For Your File" በሚለው መድረካችሁ ላይ ባላየውም እኔው ለመረጃ ያህል ላቅርብላችሁና አንባብያን ይፍረዱት። ጉዳዩም ስለመጽሄታችሁ ዋና አዘጋጅ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ የሂውስተኑ ስብሰባ ውሳኔዎች ነጥብ 8ኛ (ሀ) እንዲህ ብሎ ነበር፦

"የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባል ከሆነችበት ጊዜ ጀምሮ፥ ፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌ ቤተክርስቲያኗን ከሚወክሉት ጋር በዓመታዊ ጉባኤዎችም በየኮሚቴው ስብሰባ በመገኘት፣ እንዲሁም ጀኔቫ ካለው ከማኅበሩ ዋና ጽህፈት ቤት ጋር የቅርብ ግንኙነት በመፍጠር ያደረጉትን አስተዋጽኦ በማስታወስ፣ በአምስተኛው ጉባዔ በተወሰነው መሰረት አሁንም ብፁዕ አቡነ ይሥሐቅን በመርዳት ግንኙነት ጀምረው እንዲያጠናክሩ ጉባዔው አደራ ጥሎባቸዋል። ለዚህም የሚሆነውን ቦርዱ እንዲያመቻች አሳስቧል።" ታዲያ እኒህ አዘጋጅ ይህን ያህል ኃላፊነት ካላቸው እንዴት አያዳሉ? ከዚህ የበለጠስ አይን ያወጣ ጉጠኝነት የት ታይቶ ይታወቃልና ነው የአብይን ወደ እምየ ልክክ ያደረጋችሁት።

ፕሮፌሰር ግን ታዘብሁዎት "በህግ አምላክ የሚሉ ምዕመናን ..." ብለው ከመጻፍ በህግ አምላክ የምል ፕሮፌሰር ብለው ቢጽፉ ያምርብዎት ነበር። ይህን ካልሁ በኋላ የተገላቢጦሽ እንዳይሆን ነገሩ!! በሚል የላክሁላችሁ ደብዳቤ ከዚህ ደብዳቤ ጋር ተያይዞ በሌላ ቦታ ለዚህ ወር ባይደርስም ታሪክ ነውና ይወጣል። እናንተ ግን አንድ ነገር ልታውቁ ይገባል የዛሬውን ቤታችሁን ትታችሁ ለነገው ብታስቡ የእግዚአብሔርን ደጅ ታገኛላችሁና የተጣላን ለማስታረቅ፣ የተራራቀን ለማቀራረብ እንጅ አንድ የሆነን ለማለያየት፣ የተቀራረበን ለማራራቅ መጽሔታችሁን አትጠቀሙበት።

## ለኢትዮጵያ ሬጂስተር

---

## የተገላቢጦሽ እንዳይሆን ነገሩ!!

በህዳር እትማችሁ "በህግ አምላክ . . ." በሚለው ርዕስ ላይ መጽሔታችሁን ለትዝብት የጣለና ኃላፊነት የጐደለው መረጃ የለሽ ክስ በዴንቨር ኮሎራዶ የሚገኘውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያንን ያለአግባብ በመክሰሳችሁ ለከሳችሁ ቤተክርስትያኑም ሆነ የሰበካ ጉባኤውን ሳልወክል ራሴን ወክየ አስተያየት ለመስጠት ተገድጃለሁ።

በሰሜን አሜሪካ ስለሚገኙት ጳጳሳትና ብፁዕ አቡነ መርቆሪዎስ የሰጣችሁትን አስተያየት እኔ መልስ የመስጠት መብትም ሆነ ኃላፊነት የለኝምና ያንን ለአባቶቻችን እተዋለሁ። አንድ ነገር ግን መናገር እሻለሁ። የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የራሷ መመሪያ ያላትና ሽሪውም ሿሚውም የሆኑት የሃይማኖታችን መሪው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስ በአጠገባችን ስላሉ ይህ የደረደራችሁት ክስ ወደ እርሳቸው ቢሄድ የተሻለ መልስ ያገኝ ነበር እላለሁ። ይህን ካልሁ በኋላ ግን የማቀውንና በኃላፊነትም የሰራሁበትን ክሳችሁን ልመልስ ይፈቀድልኝ።

በምታወግዟቸው አባ ጳውሎስ ተከታዮች ከቤተክርስቲያን ተባረን ፍርድ ቤት ለፍርድ ቤት ስንጉላላ የመጽሄታችሁን አንድ መስመር የማበረታቻ ቃል ሳናገኝ አሁን ከደረሰበት የደረሰው ቤተክርስቲያናችን ዛሬ ጳጳሳቱን በዘረፈ ጸሁፋችሁ እኛንም እንዲህ ብላችሁ ታጠቃልሉናላችሁ "እንዲያውም በዚያው ዕለት ተከታዮቻቸውን ይዘው ዴንቨር (ኮሎራዶ) ሌላ ስብሰባ አድርገው እንደነበር ከዚያ የመጣ ዘገባ ያመለክታል።" መስመር የኔ።

አንባብያን ይፍረዱና ጉዳዩ እንደዚህ ነው። የዴንቨር ግሸን ማርያም በዓለ ንግሥ ሁልጊዜ የሚከበረው መስከረም 21 ቀን ሲሆን ያለውን ጊዜ ለመጠቀም የመስቀልን በዓልና የግሸን ማርያምን በዓለ ንግሥ ቅዳሜንና እሁድን አከታትለን እንደምናከብር በሙሉ ጳጳሳቱ የሚያውቁ ሲሆን ጳጳሳቱና ለበዓላችን ይመጣሉ ተብሎ የተጠሩት ካህናት ከአንድ ወር በፊት በደብዳቤ በኋላም በስልክ ተጠርተዋል። በዓላችንን ለማክበር አምስት ቀን ሲቀረን ሂውስተን ቴክሳስ ስብሰባ እንደሚደረግ የሚገልጽ ደብዳቤ ከጽህፈት ቤቱ ሲደርሰን ይህ ስብሰባ እኛና ለበዓላችን የሚመጡትን እንግዶቻችን እንዳንገኝ የተደረገ ጥረት ነው የሚል እምነት አድሮብኝ ነበር። በመጽሄታችሁ የጻፋችሁትን ካነበብሁ በኋላም የሚከተሉትን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ተገደድሁ።

1. ለምን በእኛ አመትበዓል ወቅት ሌላ ስብሰባ ለማድረግ ማህበሩ ፈለገ? አያውቅም እንዳትሉኝ ቶሮንቶ ላይ የቤተክርስትያናችን ካህን ሁሉንም በቶሮንቶ የተገኙ አባቶችና ካህናት ጠርተዋል።
2. እንዴት አርገን የራሳችንን ዓመት በዓል አስቀምጠን ወደ ሂውስተን ሰው መላክ እንችላለን? ያውም የቤተክርስቲያኗን አንድ ካህን?
3. እንዴትስ ለእኛ አመት በዓል የመጡ የሶስት ቤተክርስቲያን ካህናት በስብሰባው ላይ መገኘት ይችላሉ?
4. ለምንስ ስብሰባ ከታሰበ ሁሉም ሊገኝ ወደሚችልበት ወደ ዴንቨር አልታሰበም ነበር?

ይህን ካልሁ በኋላ አባቶቻችን ዴንቨር በሰነበቱበት ሰሞን ሰው እንዳልተለያቸውና ምንም አይነት ስብሰባ ያላካሄዱ መሆኑን ማረጋገጥ እወዳለሁ። "ከሆነ . . ." ብሎ በጉጠኝነት የመደበን ይህ መጽሄታችሁ የቤተክርስቲያናችን ምዕመናን ጉጠኝነትን በመታገላቸው ቤተክርስቲያናችንን የሁሉም ኢትዮጵያውያን ቤት አድርገዋታልና የተሰነዘረው ክስ ያለቦታውና ለማይመለከተው ወገን በመሆኑ ለወደፊቱ ብትታረሙበት የአንድነት ወገኖችን አታስከፉም እላለሁ።

የኢትዮጵያችን አምላክ ይቅር ይበለን

ብርሃኑ ዓለም – የሰበካ ጉባኤው ዋና ጸሀፊ

ደብዳቤዎቻችሁ

# ባለተራ መስቀል ቀንበር መንፈሱ፣ ቀያፋም በዲያብሎስ ፈረሱ።

ከማሩ ወልደንጉድጓድ

ለሐቅ ሳይሆን ለግል ዝነኛነት ለቆምከው ከፋፋይ፤ በፈጠርከው መዋቅር ይህች ደብዳቤህ ደርሳህ እንደምታነባት አልጠራጠርም። የደብዳቤዬን መጀመሪያ ልብ ብለህ አጢነህ ከሆነ አንቱ አላልኩህም፤ በዕድሜ የሚበልጡንን እንድናከብር ኮትኩቶ ያሳደገን መልካም ኢትዮጵያዊ ባህላችን ቢማፀነኝ እንኳ አንተም የኃይማኖት አባቶቼን ስላላከበርክልኝ አንተን የማከብርበት ልቦና የለኝም። እንዳትቀየመኝ፣ አሳቱን እኔ አልጀመርኩትም።

ባትረዳው ነው እንጂ በሀገር ወዳድነት አቋም የተነሳ ከዚህ በፊት ተንኮልህን ሳናውቅ የደገፍንህ፣ የምናበረታታህና አይዞህ የምንልህ ያው በስደት ላይ በአሜሪካ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ነበርን። እኛን መከፋፈል ከጀመርክ ወዲህ ግን ትምህርት ሳትወስድ የቀረህ አይመስለኝም።

ከዚህ በፊት ከባዕድ ስም ጋር ተጣብቃ በብዕር ስም ፓትሪያርኩን የሰደበችውን ኮኪ አቤሰሎምን በማበረታታት በኋላም ከአንድና ሁለት የማይበልጡ ፀረ-አንድነት ቁሶች በመጠቀም ጳጳሳቱ ላይ ያደረግሽው ቅስቀሳና አሉባልታ የአደባባይ ሚስጢር ነው። ይህም ብዙ ኢትዮጵያውያንን እንዳስቆጣ የምትገነዘብ ይመስለኛል። ቅኝ ግዛትን (የውጭ ወረራን)፣ አዲስ መጤ ሚስዮናውያንና የወያኔን የከፋፍለህ ግዛው መርሆ የታገለችውን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ያውም በስደት ላይ በፈተናና በመከራ ላይ የምትገኘውን መከፋፈል በአጠቃላይ በአሁኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ላይ ትልቅ አሻጥር መስራት ነው። ችግር አለ፣ በስደት ላይ ባለችው ቤተክርስትያናችን መሻሻል የሚገባቸው ነገሮች አሉ ብትል እንኳ ይህንን ጉዳይ ጳጳሳቱን በመቅረብና በመወያየት ካልተቻለም ከበርካታ ካህናትና ምዕመናን ጋር በመነጋገር ወንድማዊና ኢትዮጵያዊ መፍትሔ መፈለጉ ቅን ሐሳብ ነበር።

ያንተ መንገድ ግን ስሜታዊ ጽሁፍ በመፃፍ አንባብያንና ምዕመናኑን ማወናበድ ሆነ። አሁንም ከቀጠልክበትና ሰውን አወናብደህ ከጉንህ ብታሰልፍ እንኳ አንተን በብዕር ከመታገል ወደኋላ አንልም።

በዕምነት ላይ የሚደረግ ስብስብን ወያኔም ሆነ የምዕራቡ የስለላ ድርጅት የቱን ያህል እንደሚፈሩት የምታውቀው ይመስለኛል። ጳጳሳቱን በመነጣጠል ምዕመናኑን ለመከፋፈልና እንደተቃዋሚ ኃይሎች ለማዳከም የወያኔ የስለላ መረብ አሉባልታን በማሽተትና የሌለ "ጉጠኝነትን" ደጋግሞ በመርጨት የቱን ያህል እንደሚራወጥ በዚሁ በላንዳፍታ መፅሔት ከሁለትና ከሦስት ዓመት በፊት የወጡትን ጽሁፎች አላነበብክም አልልም። ምናልባት ሌሎች ሰዎችም አነጋግረውህ ይሆናል።

ልዩነት ቢኖር እንኳ ሁሉንም አቻችለህ በምሁርነትህና በሽማግሌነትህ ማሰባሰብ ሲገባህ አፍራሽ ነገርን ለግል ዝናህ መጠቀምህና በተራቀቀ ተንኮል ሁሉን ወቃሽና የእውነት አባት በመምሰል ወያኔዎችም እንዲያመሰግኑህ መሞከርህ የኢትዮጵያን ፖለቲካ የማያውቁትን ያጭበረብር እንጂ ምዕመናኑን አያታልልም።

ለትግላችን በማይረዳ መንገድና ካለጊዜው አላስፈላጊ ስሜታዊ፣ አደናጋሪና አሉባልታዊ ጽሁፎችን በየጊዜው በመደንጉር የበርካታ ምዕመናንና ካህናትን ስሜት በመንካትህ ተፀፅተህ ይህን ማረሙ ተገቢ ነበር።

አንተ "የለሁበትም ዓይኔን ግንባር ያድርገው" የምትልለት የምሑር ክፍል ነው ከዛሬ 40 ዓመት ጀምሮ ፊደል የቆጠረው (እኛንም ጨምሮ) ባህላችንና ኃይማኖታችን ላይ በማመፅ አንዴ ከአሜሪካ፣ አንዴ ከሩሲያ፣ አንዴ ከአረብ፣ አንዴ ከባይዛንታይን ቀለም ተውሶ ሃገሪቱን ምድረ በዳ ያደረጋት። ለዚህ ሁላችንም ንስሐና ተሐድሶ ማድረግ አለብን፤ ኢትዮጵያዊነትንና ሐገር ወዳድነትን እንደገና መገንባት ይኖርብናል።

እንዲያው እኛ ትንሽ ያንተን ያህል ባናደርግም የዘመኑን ፊደል የቆጠርነው ነን ለዚህ መልስ የምንሰጥህ፤ ጳጳሳቱ እንኳ ካንተ ጋር እንካ ሰላንቲያ አልገጠሙም፤ "በበረዶ፣ በበጋ፣ ዝናብም በመከር እንዳይገባ እንዲሁ ለሰነፍ ክብር አይገባውም። እንደሚተላለፍ ድንቢጥ ወዲያና ወዲህም እንደሚበር ጨረባ፥ እንዲሁ ከንቱ እርግማን በማንም ላይ አይደርስም። አለንጋ ለፈረስ፥ ልጓም ለአህያ፥ በትርም ለሰነፍ ጀርባ ነው። አንተ ደግሞ እርሱን እንዳትመስል ለሰነፍ እንደስንፍናው አትመልስለት።" የሚለውን መጽሐፈ ምሳሌ ተግሳፅ በመከተል ስድብህን ቦታ አልሰጡትም። መጽሐፈ ምሳሌ ም. 26(2)፣ ቁ 1–4)።

በርግጥም "ኃጥኡን የሚያፀድቅና፣ በፃድቁ ላይ የሚፈርድ ሁለቱ በእግዚአብሔር ዘንድ አፀያፊዎች ናቸው" (ምሳሌ ም.16 ቁ.15)። በካህናት ላይ መፍረድ ዛሬ አልተጀመረም። የሞሶሎኒ አሽከሮችና ታዛዦች የአቡነ ጴጥሮስን ስም ከማጥፋት አልፈው ረሽኗቸዋል። የደርግም አሽከሮች አቡነ ቴዎፍሎስን ከመኮነን አልፈው አስመትተዋቸዋል። ስለዚህ እንኳ ብዙ የምታውቀው ስላለ አንተው እውነታውን የምትናገርበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም፤እኛም የምናውቀው አለና! ጳጳሳትና ካህናት ከባድ የሰይጣን ፈተና እንደሚጠብቃቸው ተረድተው ነው ቃለ መሐላ የተቀበሉት። የኢየሱስ የመስቀል ቀንበር ስቃይ በስም ማጥፋት፣ በግዞትና በስደት ይከሰታል። የተቀበሉት ስጋወደሙና ቃልኪዳኑ ይበልጥ ያጠናክራቸዋል እንጂ የታጠቁትን የእምነት ሰንሰለት አያስፈታቸውም፤ በስደት የሚገኙ ምዕመናን ከእርሱ ጋር ናቸው። በምድር ላይ እስካለን ድረስ የዲያብሎስ ፈተናም ይቀጥላል፣ የመስቀል ቀንበሩም ተሸካሚዎቹን እየከበደ እየደፋና እያውተረተረ ያሰቃያቸዋል፣ መራራ ሆምጣጤም ይቀምሳሉ፣ እንደጉለጉታው ኢየሱስ አባታቸው ዙፋን ፊት እስከሚደርሱ ድረስ።

## እባካችሁ ደግ ደጉን!!

ውድ ላንዳፍታና ላንዳፍታዎች እንኳን ለፈረንጆች አዲስ ዓመት በሰላም አሸጋገረን። አዲሱ ዓመት የስላም የፍቅር የነፃነትና የህይወት መሰረት ሆኖልን ካለብን የኋላ ቀርነት አንድ ርምጃ ወደፊት የምንራመድበት ዓመት እንዲሆንልን ሁላችንም በያለንበት ደግ ደጉን እንመኝ እላለሁ።

ላንዳፍታዎች ባይሆን ጽሁፌን ለማሻሻል እሞክራለሁ እንጂ እንግዲህ በአማርኛ ዩኒቨርስቲ አልሄድኩም ብዬ በነአቶ መኮታው ስድብ ጽሁፌን አላቆምምና የዛሬ ደብዳቤዬ የሚያተኩረው እኛው እርስ በራሳችን እየተጠላለፍን እንድንወድቅ የሚያደርጉንን ነገሮች ለማመልከት ነው። ለምሳሌ፦

■ አንድ ቢዝነስ ለመክፈት ልምድ ያለውን ሰው ለማማከር ሲኬድ ገና ከጅምሩ ሀበሻን አምነህ ቢዝነስ

ደብዳቤዎቻችሁ

አትክፈት፡ እኔ ራሴ ልዘጋው ትንሽ ነው የቀረኝ ብለው ሞራል ይገላሉ። ይህ ሌላው ዜጋ እንዳያድግ ከመፈለግ ስሜት የመጣ እንጂ አለበለዚያ ጥቅሙንም ጉዳቱንም ካስረዱ በኋላ ውሳኔውን ለባለጉዳዩ መስጠቱ ይገባ ነበር።

■ እርሜን ገና ዛሬ ሀበሻ ሬስቶራንት ልበላ ብሄድ ስንት ሰዓት ሙሉ አስጠበቁኝ፣ በዚህ ላይ አስተናጋጆቹ ሰው በደንብ አያነጋግሩ ኩራታቸው ... ይባላል። ግን የትኛውም ሬስቶራንት (የሀበሻ ያልሆነ) ቢሄዱ እርስዎ ካዘዙ በኋላ ነውና የሚዘጋጀው ጊዜ እንደሚወስድ ወይም እንደሚዘገይ ልብዎ ያውቃል ግን በቃ የራስን ነገር ማናናቅ ልምድ ሆኖብን እንደልብም መናገር ይቻላልና ተመናጭቆ ይወጣል። በእውነት በሬስቶራንቱ ችግር ካዩ ሥራ አስኪያጁን አስጠርቶ በግልፅ ችግሩን መናገሩ ይሻላል እንጂ ውጪ ወጥቶ ሐሜት መፍጠሩና የንግድ ቤቱን ስም ማጥፋቱ አግባብ አይደለም።

■ አዳዲስ ሙዚቃዎች ሲወጡ ኦሪጅናል ካሴት እንዳይሸጥ ሙዚቃውን በካሴት እያባዙ ለሰው መስጠት። ይሄ ዘፋኙን ባይጉዳውም ሙዚቃ ቤቱን በእጅጉ ይጉዳዋል፤ የሙዚቃውንም ጥራት ይቀንሳል። ደግሞም እነዚህ ሙዚቃ ቤቶች ደንበኞቻቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ ሆነን ሳለ እኛው እንደዚህ ካደረግናቸው እንግዲህ ማን ይግዛቸው?

■ ነጋዴዎችም የንግድ ድርጅቶቻችሁን ለማስተዋወቅ ኢትዮጵያውያን መጽሔቶችን በመጠቀም እርስ በርሳችሁ እየተረዳዳችሁ እናንተም ንግዳችሁን አስፋፉ እነሱም መጽሔቱን ለአንባቢ ያድርሱ።

እና በአጠቃላይ ለማለት የፈለግሁት ከትውልድ የወረስነው አንዳንድ ኋላ ቀር ባህሎች ቢኖሩብንም ከአዲሱ አካባቢ አዲስ ነገር ለመቅሰም መሞከር ዋናው ሲሆን፤ ሁሌ ሰዎችን ከመተቸት ይልቅ ተቀራርቦ በመስራት እድገት ይገኛልና የበለጠ ለማወቅና ለማግኘት እርስ በርሳችን በኮሚኒቲያችን እንረዳዳ እላለሁ።

ኑር ሁሴን አደም – ዳላስ ቴክሳስ፡

## የ3 ሺህ ዘመን መተማንን!

አለምፒክስንና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ እግር ኳስን ወደ አትላንታ በመሳብ ያስተናገደው መግነጢስ (ማግኔት) በዓመታዊው የጥቁር ኪነ-ጥበብ ክበረ-በዓል ምክንያት የአቶ ኃይሌ ገሪማን የፊልም ድርጅት "ማህፉድ"ንም ዘንድሮ መሳቡ አልቀረም።

"ምርት፣ 3 ሺህ ዓመት" (Harvest 3000) የተሰኘውን ተንቀሳቃሽ ምስል ለማግኘት በሐዋላ ካዘዝኩኝ ሦስት ዓመታት ያስቆጠረ ቢሆንም በአላላክ ዘዴና በእኔ የመረከቢያ አድራሻ መካከል ችግር ተፈጥሮ ባለመረከቤ ችላ ብየው ነበር። ነገር ግን በጥቁር በዓል ላይ በፒድሞንት መናፈሻ ውስጥ ማህፉድ ዳሱን ጥሎ ሲያስተናግድ አገኘሁት። *"ምን ልርዳህ?"* የሚለው ጥያቄ ከአስተናጋጇ ሲቀርብልኝ *"የ3 ሺህ ዘመን ምርቴ አልደረሰኝም"* ወደሚል ዝርዝር ሁኔታ ውስጥ ገባሁኝ። በዚህ አጋጣሚ ወ/ሮ ሶሎሜ ለሥራ በቦታው ስለነበሩ ሁኔታውን ገለፅኩላቸው። ብዙ ሐተታ አልነበረም፤ ጭቅጭቅም አልተፈጠረም። መልካም ለሠራ ልጅ ቆሎ ታፍሶ እንደሚሰጠው ያህል ከጠረጴዛው ላይ ለገበያ ከተደረደሩት ተንቀሳቃሽ ምስሎች መካከል *"ምርትን"* በላስቲክ ከረጢት ውስጥ ከትተው ስላስፈው ችግር ይቅርታ በመጠየቅ ሰጥተው ሸኙኝ።

በማግስቱም የማዘግየ ማረጋገጫያዬን ይዤ ብቀርብም ወ/ሮ ሶሎሜ ከቃሌ አመኔታ ሌላ ሌላ ማረጋገጫ ሳይጠበቁብኝ በትሕትና መለሱኝን ከሦስት ዓመታት በኋላም የሦስት ሺህ ዓመት ምርትን በአመኔታ መስጠቱ ልቤን ስላረካው ለወ/ሮ ሶሎሜ ገሪማና ለማህፉድ ድርጅት ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። – ብይሉ ላዳነች ብሻው

## መቼ ይሆን እኛም ...

(ከገነት ጉርሙ — አትላንታ)

ይህንን ፅሁፍ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች እንድፅፍ ያስገደደኝ ከጥቂት ሳምንታት በፊት ቸ–ሰፐእነ ያስተላለፈው በconnecticut ግዛት ሲካሄድ የነበረ ስብሰባ ነው። የስብሰባው መነጋገሪያ አጀንዳ የፕሬዚዳንት ክሊንተን ለኢምፒችመንት መቅረብ ወይም አለመቅረብ ነበር። ስብሰባውን የጠሩት በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት ከተቸገሩት ጥቂት ሪፐብሊካን የህዝብ እንደራሴዎች መካከል አንደኛው የሆኑት ክርስቶፈር ሼይስ ነበሩ። ዓላማቸውም ይህንን አንገብጋቢ ጉዳይ ከመረጣቸው ህዝብ ጋር ለመነጋገርና የወከላቸው ህዝብ ምን ዓይነት ውሳኔ ለምክር ቤቱ ይዘው እንዲቀርቡ እንደሚፈልግ ከህዝቡ አፍ ለመስማት ነበር።

ይህ በኒውዮርክ ከተማ ውስጥ የተካሄደው ውይይት ቁጥራቸው ከአንድ ሺህ በላይ የሚሆን የኒውዮርክና አካባቢው ከተሞች ነዋሪዎች የተሳተፉበት ሞቅ ያለ ውይይት ነበር። ከ14 ዓመት የስምንተኛ ክፍል ተማሪ ጀምሮ እስከአዛውንቶች፣ በትምህርት የላቁ ፕሮፌሰሮች፣ ዶክተሮች እንዲሁም የከተማው ከንቲባና የመንግሥት ባለሥልጣኖች በስብሰባው ላይ ተገኝተው ነበር። የስብሰባው ተሳታፊዎች ሁሉም በየበኩላቸው አስተያየታቸውን ሰጡ።

የኢምፒችመንት ተቃዋሚ

ች ሰው ሆኖ የማያጠፋ የለምና የሁላችንም ጓዳ ቢፈተሽ ጉድ ይወጣልና ፕሬዚዳንታችን ምንም እንኳን መርጠነው በአሜሪካን ምድር ከፍተኛውን ኃላፊነት ብንሰጠውም ከሁሉም መጀመሪያ እሱም እንደኛው ሰው ነውና ይቅር እንበለው በማለት፤ ከሃይማኖት መፃህፍት ጥቅሶችን አነበቡ ከታላላቅ የኃይማኖት መሪዎች ሥራዎችም በመጥቀስ ይቅር ባይነትና አስተዋይነት እግዚአብሔር የሚወደው ነገር መሆኑን ተናገሩ። በዕድሜያቸው የገፉ አዛውንቶች ደግሞ አሜሪካ የዓለም ህዝብ መሳለቂያ ሆነች አሁንስ ይበቃናል አሉ። የተቀሩት ፕሬዚዳንቱ ሥልጣን እንዲለቅ የሚያበቃ ወንጀል አልፈፀመም ይህ ጉዳይ እዚህ ደረጃ ሊደርስ የቻለው በሪፐብሊካኖች ሴራ አቀንቃኝነት ነው ስለዚህም ከፖለቲካ ኩዴታ ለይተን አናየውም አሉ። እንደራሴያቸውንንም ይህንኑ ሐሳባቸውን ለምክር ቤቱ እንዲያቀርቡላቸው ተማፀኑ። የኢምፒችመንት ደጋፊዎችም በበኩላቸው ምንም ሆነ ምንም ኋይት ሀውሱን አስደፍሯል። እውነቱን ለመናገር በመፅሐፍ ቅዱስ ምሎ በተደጋጋሚ ዋሽቷልና ከሥልጣን መባረር አለበት ብለው ፈረዱ። ዕድሜያቸው 14ና 16 ዓመት የሆኑ ወጣት ተሳታፊዎችም ሲናገሩ በቤትም ሆነ በት/ቤት በፅሑፍ የሰፈረና በተለምዶም የሚከበር ህግና ደንብ እንዳለና ከዚህ ዝንፍ ብለው ቢገኙ ግን በወላጆቻቸውም ሆነ በመምህሮቻቸው እንደማይታለፉና ተገቢውን ቅጣት እንደሚቀበሉ ገልፀው በተለይም ሀገር መሪነትን የሚያክል ሥልጣንና ኃላፊነት የተጣለባቸው ፕሬዚዳንት ክሊንተን የፕሬዚዳንቱ ቢሮ ስሙ እንዲጉድፍ በማድረጋቸውና አልፎ ተርፎም ለአሜሪካን ህዝብ በመዋሸታቸው ተገቢው ቅጣት እንዲወሰንባቸው ማለትም ከሥልጣን እንዲለቀቁ ጠይቀዋል።

ምንም እንኳ በልጆች አንደበት ቢነገርም ቁም ነገሩ የማያሻማ

ቀጥተኛ ነው። አንድ ሰው ጥፋት ካጠፋ እነሰም በዛ ለጥፋቱ

(ወደ ገፅ 33 ይዞራል)

ደብዳቢዎቻችሁ

# ከዜና ማኅደር እንዲህ ሆነ!

ውድ አንባብያን፣ የዜና ማህደር አቀራረባችንን በተመለከተ አንዳንድ ያደረግነው ለውጥ አለ። ያለነው ወጭ አገር በመሆኑና ድርጊቶች በሚከናወኑበት አካባቢዎች ባለመኖራችን የምናቀርባቸው ዜናዎች ከሌሎች የዜና ምንጮችና ጋዜጦች እያጠናቀርን መሆኑን እንገልፃለን። በሌላ በኩል ደግሞ መጽሔታችን የምትዘጋጀው በየሁለት ወሩ በመሆኑ በአብዛኛው የምናተኩርባቸው ዜናዎች መጽሔቷ በምትወጣበት አካባቢ ያሉትን እንደሆነ ለመግለጽ እንወዳለን። ስለአቀራረባችን የተሻለ አስተያየት ልትሰጡን የምትፈልጉ እባካችሁ አነጋግሩን።

**ጦርነቱን በተመለከተ የቀረቡት ዜናዎች መጽሄቱ ለእትመት እስከገባበት እስከ ቅዳሜ የካቲት 7 1991 ጠዋት ድረስ ያለውን ብቻ ነው።**

## ከፍተኛ ውጊያ ተካሄደ፤ ኢትዮጵያ 7 ሽህ የሻቢያ ጦር ከጥቅም ውጭ ማድረጓ ተገለፀ፤

ጥር 29/1991 የሻዕቢያ አየር ኃይል አዲግራትን ከደበደበ በኋላ በሰነዘረው ማጥቃት ሳቢያ በተነሳው ጦርነት የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ባደረገው የመከላከልና የመልሶ ማጥቃት ውጊያ ከፍተኛ ድል መቀዳጀቱን የመንግሥት ቃል አቀባይ ጽ/ቤት የካቲት 6 ቀን ማምሻውን አስታወቀ። የመንግሥት ቃል አቀባይ ጽ/ቤት ባወጣው መግለጫ ሰባት ሺህ የሻዕቢያ ወታደሮች የሞትና የመቁሰል አደጋ እንደደረሰባቸውና 6 ታንኮች፣ 3 ቢኤም እንዲሁም 21 ሮኬት ማስወንጨፊያ መሣሪያዎች ተደምስሰዋል ብሏል። ጥር 29/1991 በባድመና በጾረና በተደረገ በዚህ ውጊያ ከሻዕቢያ 3 ሺህ 81ኛ ኮር 1ኛ ክ/ጦርና የአንድ መቶ ሰላሳ አንደኛ ኮር ሶስተኛ ክ/ጦር ሰራዊት ውስጥ ከአራት ሺህ በላይ ሙትና ቁስለኛ ሲሆን ሁለት ታንኮች ሶስት ቢ.ኤም ማስወንጨፊያ ሌሎች ከባድ የጦር መሳሪያዎች የኢትዮጰያ ሠራዊት ማጋየቱን የገለፀው የመንግሥት ቃል አቀባይ ጽ/ቤት የካቲት 1/1991 ደግሞ በጾረና ግንባር በተካሄደ ውጊያ የሁለት ሺ አንደና ኮር 2ኛ ክ/ጦርና የሶስተና ክ/ጦር አንድ ብርጌድ የሻዕቢያ መካከል ከ3 ሺህ በላይ ሙትና ቁስለኛ መሆናቸውን ገልጿል። ከዚህ በተጨማሪም በዚሁ ግንባር የኢትዮጰያ መከላከያ ሠራዊት 4 ታንኮችን ማውደሙን የተለያዩ የትጥቅ ማከማቻ መጋዘኖችን ማጋየቱን ይኸው የመንግሥት መግለጫ አስረድቷል።

የመንግስት ቃል አቀባይ ጽ/ቤት ባወጣው በዚህ መግለጫ ይህን ድል የመጀመሪያው የመከላከልና የመልሶ ማጥቃት ምዕራፍ ሲል ገልጾታል። የሻዕቢያ መንግሥት ሠራዊት ጥር 29 ቀን 1991 ዓ.ም ንጋት ላይ ከተከዜ እስከ መረብ ድረስ ባለው የባድመ ግንባር መጠነ ሰፊ የማጥቃት በኢትዮጰያ ወታደራዊ ይዞታ ላይ መክፈቱን የኢትዮጰያ መንግሥት ቃል አቀባይ አስታወቀ። የኤርትራ ሰራዊት በባድመ ግንባር ማጥቃት የከፈተበት ዓላማ የኢትዮጰያ መከላከያ ሠራዊት የያዛቸውን ምሽጎች ለመቆጣጠርና በግንባሩ ተሰልፎ የሚገኘውን ሠራዊት ለመደምሰስ መሆኑን የመንግሥት ቃል አቀባይ አስታውቋል። ቀደምሲል በተሰጠው መግለጫ መሠረት የኢትዮጰያ መከላከያ ሰራዊት ምሽጎቹን ላለማስደፈር ለማጥቃት የተሰማራውን የኤርትራ ሰራዊት ከፍተኛ አደጋ እንደጣለበት ተብራርቷል።

የኤርትራ መንግሥት በባድመ/ሽራሮ እና ዛላንበሳ ግንባር በኢትዮጰያ መከላከያ ሠራዊት ላይ ጠንካራ የማጥቃት ሙከራ አድርጎ ነበር። በተገኘው ዜና ጥር 29/91 ንጋት ላይ እንደ ባድመ በዛላንበሳ ግንባር ሻዕቢያ የሙሉ ወታደራዊ የከባድ መሳሪያ ጥቃት በማድረግ ለ45 ደቂቃ ያደረገው የማጥቃት ሙከራ ከሽፏል። በባድመ ግንባር ደግሞ ንጋት ላይ ሲከላከል የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ቀትር ላይ ወደ ማጥቃት ተሸጋግሮ በባድመ ግንባር የነበረውንና የሻዕቢያ ጠንካራ ምሽግ የሆነውን ገዛገብረስላሴን አስለቅቋል። ምንም ከሻቢያ በኩል የቀረበው መግለጫ ተቃራኒውን ቢሆንም በዚህ ፍልሚያ የሻዕቢያ ሠራዊት ከፍተኛ ሽንፈት እንደደረሰበት የኢትዮጵያ ቃለ አቀባይ አመልክቷል።

«በባድመ ግንባር የኢትዮጰያ አየር ኃይል ከፍተኛ ጥቃት አድርሷል። የመጀመሪያው ጄት ካጠቃ ከ20 ደቂቃ በኋላ ሌላ ጄት ይመጣል። የኤርትራ ኃይሎች ከጀቶቹ የሚሰነዘረውን ጥቃት ለመቋቋም የአየር መቃወሚያ መሣሪያዎችን ቢተኩሱም ጀቶቹን ፈፅሞ ለመጣልና ለመምታት አልቻሉም» ስትል የቢቢሲ ሬድዮ ዘጋቢ ካተሪና ጄንክሲን ከስፍራው ዘግባለች ብሏል አንድ ኢትዮጵያ የሚታተም ጋዜጣ ።

ይህች የኢትዮ–ኤርትራ ግጭት በተከሰተበት ወቅት ከአስመራ ሆና በፍፁም ወገናዊነት ስሜት ለሻዕቢያ በሚያደላ መልኩ በምታቀርበው ዘገባ ከፍተኛ ተቃውሞ የቀረበባት ጋዜጠኛ የኢትዮጰያ አየር ኃይል በሻዕቢያ ምሽጌችና ከምሽጉ ማዶ በማለፍ ያለከልካይ የሻዕቢያ ይዞታዎችን ሲቀጠቅጥ መዋሉን ለማመን ከመገደዷም ባሻገር ሳትደብቀው ለአለም ህዝብ ይፋ አድርጋለች ይላል የጋዜጣው ሐተታ። የኢትዮጰያ ተዋጊ ጄቶች ከባድመ አልፈው ወደ ውስጥ 30 ኪ/ሜትር ዘልቀው ጥቃት መሰንዘራቸውንም በዘገባዋ አመልክታለች። የኤርትራ ቁስለኞች በብዛት በመኪና እየተጫኑ በመሄድ ላይ መሆናቸውንም ከዚህችው በስፍራው ከነበረችው ጋዜጠኛ ዘገባ መረዳት ተችሏል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ የኢትዮጰያ መከላከያ ሠራዊት ሰኞ የካቲት 1 ቀን በቁጥጥር ስር ያዋላቸውን ኩኑኒ እና ቁኒኒ የተባሉ ቦታዎችን በተመለከተ ስለመያዝ አለመያዛቸው ማረጋገጫ እንዲሰጡ የተጠየቁት የኤርትራ ከፍተኛ ባለሥልጣን ሳቅ በማብዛትና ዙሪያ ጥምጥም እየሄዱ ቃላት በመዘብዘብ ቁርጥ ያለ ምላሽ መስጠት ተስኗቸው ነበር። በኋላም ጋዜጠኛው ጥያቄው ቦታዎቹ ተይዘዋል አልተያዙም? በሚል ሲያፋጥጣቸው ውሸት ነው የሚል ምላሽ ሰጥተዋል።

እኚህ የፕሬዝዳንት ኢሳያስ ቃል አቀባይ የሆኑት የማነ ገ/አብ በተመሳሳይ ከቢቢሲ ሬድዮ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ «ገዛገብረስላሴ» የሚባል ቦታ የለም በማለት ሸምጥጠው ከካዱ በኋላ መንግሥታቸው «ገዛ ገብረስላሴ» የሚባል ቦታ መኖሩን በማመን ዓለም አቀፍ ጋዜጠኞችን ወደ ስፍራው ጋብዟል። ይሁን እንጂ ለጋዜጠኞች ያሳየው ቦታ «ገዛገረስላሴ» የሚባለው ቦታ አለመሆኑም የኢትዮጰያ

መንግሥት ቃል አቀባይ ጽ/ቤት ካወጣው መግለጫ መረዳት ተችሏል ሲል ጋዜጣው አትቷ ል።
የኢትዮጵያ ጦር በኤርትራ ኃይል ላይ በጄቶችና በሄሊኮፕተሮች የታገዘ ጥቃት መሰንዘሩን የቢቢሲ ሬዲዮ ዘጋቢዎች ከማረጋገጣቸው ባሻገር የጀርመን ዜና ወኪል ይህንኑ የኢትዮጵያ አየር ኃይልን ጥቃት በማረጋገጥ ኢትዮጵያ ሁለት ስልታዊ ቦታዎችን ይዛለች ሲል ማረጋገጫ መስጠቱ አገር ቤት በታተሙ ጋዜጣዎች ተገልጿል።

የሻዕቢያ መንግሥት ባሰማው ክስ እሁድ የኢትዮጵያ ወታደሮች አዲኳላን በመምታት ስምንት ዜጐቼን ገድላለች፣ በዘጠኙ ላይ የመቁሰል አደጋ አደጋ አድርሳለች ማለቱን ጠቁሞ የኢትዮጵያ መንግሥት በበኩሉ በአዲግራት ከተማ ላይ ሻዕቢያ በከባድ መሣሪያ ለ30 ደቂቃ በፈፀመው ድብደባ ሰባት ሰዎች ክፉኛ ሲቆስሉ ሶስት ቤቶች ከነንብረቶቻቸው እንዳለ መውደማቸውን ዜናው አያይዞ ገልጿል።

የኢትዮጵያ ሠራዊት ከአዲኳላ 5 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የሚገኘው የኤርትራን መንግሥት የራዳር ጣቢያ በከባድ መሣሪያ ባደረገው ድብደባ ቀጥሎ በመዋል የራዳሩን ጣቢያ እንዳለ ማውደሙን የጀርመን ድምጽ መግለፁ ታውቋል።
አዲኳላ ከአስመራ በስተደቡብ በኩል 95 ኪ.ሜ ርቀት ላይ የምትገኝ ከተማ መሆኗን ዜናው በመጥቀስ በከባድ መሣሪያ ድብደባ የወደመው የአውሮፕላን መቆጣጠሪያ ጣቢያ ሰዎች በማይኖሩበት አካባቢ ከአስመራ 100 ኪ.ሜ ላይ እንደነበረም ዋቢ በማስቀመጥ አስረድቷ ል። በራዳሩ አካባቢ የነበሩ የሻዕቢያ ወታደሮች ላይ የኢትዮጵያ ሠራዊት በወሰደው እርምጃ ከፍተኛ ጉዳት መድረሱን ዜናው አመልክቷ ል።
ጦርነቱ በባድመ ሽራሮ ግንባር በጾረና በኩል መካሄዱን ያስታወቀው የጀርመን ድምጽ የኢትዮጵያ ሠራዊት ቁልፍ ቁልፍ ቦታዎችን እየተቆጣጠረ መሆኑን ያስረዳል። በጦርነቱ የሻዕቢያ ራዳር ከየትኛው አቅጣጫ ተመቶ እንደወደመ ባይገለጽም ወታደራዊ ጠበብቶች ራዳሩን ለመምታት ምቹ የሆነው ቦታ በራማ ግንባር በኩል እንደሆነም ሰፊ ግምታቸውን አስፍረዋል ብሏል።
የሻዕቢያን ከፍተኛ ምሽግ የሆነውን የገዛገብረስላሴን ምሽግ የኢትዮጵያ ሠራዊት መቆጣጠሩ ሲታወቅ ለማስለቀቅ በተደረገው ውጊያ ሻዕቢያ ሽንፈት የደረሰበት ከመሆኑም ባሻገር በከፍተኛ ኃይሉ ላይ እልቂት እንደደረሰበት አመልክቷ ል ይላል ይኸው ዜና። ጾረና ለቀጣይ እርምጃው ከወታደራዊ ስትራቴጂ አኳያ አመቺ ቦታ መሆኑንም ጠበብቶች ይናገራሉ። ጾረና ከአስመራ 125 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደምትገኝ ይታወቃል። የኢትዮጵያ መንግሥት ውጊያውን እስከየት ድረስ እንደሚያዘልቀው ባይታወቅም ሻዕቢያን የማያዳግም ትምህርት እንሰጠዋለን እያሉ መናገራቸውን አስታውሷል።
የኤርትራ መንግሥት ውጭ ጉዳይ ሚ/ር በበኩሉ የኢትዮጵያ ሠራዊት በአሊቴና፣ ጾረናና ባድመ ግንባር ሌላ ጥቃት ሰንዝራብኛለች በማለት ክስ ማሰማቱ ታውቋል። በአሊቴናና መረብ ሰቲት ግንባር ጦርነት መቀጠሉን ሻዕቢያ ገልጾ የኢትዮጵያ እግረኛ ሰራዊት በጄትና የጦር ሄሊኮፕተሮች እየተደገፈ መጠነ ሰፊ ጥቃት ሰንዝሮብኛል ብሏል።
በተያያዘ ዜና በባድመና ጾረና ግንባር የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት በሚካናይዝድ ኃይልና በጄት እየተደገፈ በወሰደው የማጥቃት እርምጃ የሻዕቢያ ሁለት ከፍተኛ ወታደራዊ ይዞታዎች መደምሰሱን ለማወቅ ተችሏል።
በጾረና ግንባር በኩል የኢትዮጵያ ሠራዊት በተዋጊ ጄቶች በመደገፍ ባደረገው መልሶ ማጥቃት ከአዲኳላ ሌላ ለመንደፍራና ደቀመሃሪ ቅርበት ያለውንና ከፍተኛ የሻዕቢያ ወታደራዊ ቤዝ በመደብደብ ድል መጨበጡ ይነገራል። ሰራዊቱ በባድመ ግንባር ከሻዕቢያ ያስለቀቀውን ገዛገብረስላሴን የተባለውን ከፍተኛ ምሽግ ለማስለቀቅ አለኝ ብሎ የሚመካበትን ኃይል ሻዕቢያ ቢያሰልፍ የኢትዮጵያ ሰራዊት በወሰደው አኩሪ እርምጃ ምሽጉን አስከብሮ ከመቆጣጠሩም ባሻገር የጠላትን ኃይል እንዲበታተን ማድረጉን የደረሰን ዜና አመልክቷ ል። በዕለቱ በተደረገው ውጊያ ከጠላት በኩል ለቁጥር የሚያታክት ጦር እንደተደመሰሰ ዜናው አያይዞ በመግለጽ ከወገን በኩል መጠነኛ ጉዳት እንደደረሰም ሳይሸሽግ አስረድቷ ል።

## ዘግይቶ የደረሰን

እሁድ የካቲት 7 ቀን ከንጋቱ በአሰብመስመር በር ግንባር በከባድ መሣሪያ ውግያ መካሄዱን የኢትዮጵያ መንግሥት ገለፀ። የሻቢያ ወራሪ ጦር በቡሬ ግንባር የከፈተውን ጥቃት በመመከት የእትዮጵያ አየር ኃይል በወሰደው የመልሶ ማጥቃት ውግያ በሻቢያ ጦር ላይ ከባድ ጉዳት ማድረሱ ሲገለፅ 2 የጠላት ታንኮችና የሻቢያ ጦር የሚጠምበት የውሃ ማጠራቀሚይ መደምስን መግለጫው አክሏል። እንደ መግለጫው አባባል ከኢትዮጵያ በኩል አንድ ኤሊኮፕተር ተመትቶ ሲወድቅ ሌሎች ጄቶችና ኤሊኮፕተሮች ግዳጃቸውን ፈጽመው በደህና መመለሳቸውን ለመረዳት ተችሏል።

# “ኢትዮጵያ ግዛቷን ለማስመለስ ያላት ብቃት አያጠራጥርም”

የው/ጉ/ሚ/ ሥዩም መስፍን

“ኢትዮጵያ ያላት ብቸኛው ፖለቲካዊና ወታደራዊ ግብ በወረራ የተያዘባትን ግዛቷን በማስመለስ ሉዓላዊነቷን ማስከበር እንደሆነ” የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መስፍን አስገንዝበዋል። የኢትዮጵያ የውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር አቶ ስዩም መስፍን በኢትዮ–ኤርትራ ግጭቶች ዙሪያ በሰጡት ጋዜጣዊ መግለጫ ኢትዮጵያ ለሠላም ሲባል ሙሉ ትብብር እያደረገች መቆየቷንና አሁንም ለዚህ ዝግጁ መሆኑዋን ገልፀው ሉዓላዊነቷ እየተደፈረ የህዝቦቿ ክብር እየተዋረደ ልትቀጥል አትችልም ሲሉ ገልጠዋል። “ለ3ኛ ሸምጋይ አካሎች ያሳየነው ትዕግሥትና ዝግጁነት በስህተት ተተርጉሞ ሁሉንም ዓይነት በደል ሊቀበል የሚችል ወፍራም ቆዳ እንዳለን ተደርጎ ሊታይ አይገባም” ሲሉ አስገንዝበዋል። በመቀጠልም “ኢትዮጵያ ተወራና ተደፍራ እያለች ህዝቧ ግፍ እየተፈፀመበትና ያለ እረፍት እየተተነኮሰች በነበረችበት ሁኔታ ኢትዮጵያ ያሳየችውን ትዕግስት ሁሉም ያስተዋለው ነው” ብለዋል። አያይዘውም” የሰላም ሃሳቦች እና የሁሉንም ስንቀበል ኤርትራ አንዱንም

ሳትቀበልና በመጨረሻም የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሰላም ሃሳብ ላይ ደርሰን ኤርትራ እቀበላለሁ ወይም አልቀበልም ሳትል ላልተወሰነ ጊዜ በዚሁ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የውሳኔ ሃሳብ ላይ ልትተኛ ማሰቧ ምን ያህል ለጦርነት እንደተነሳሳች ያረጋግጣል" ሲሉ አቶ ስዩም ለጋዜጠኞች ገልጠዋል። በአየር ላለመጠቃቃት የነበረውን ውል ኤርትራ ቀድማ ማፍረሷና በመጨረሻም በባድመ ሽራሮ ግንባር ሰፊ ማጥቃት በመጀመር ኢትዮጵያ አስገድዳ ወደ ጦርነት እንዳስገባቻት ውጪ ጉዳይ ሚኒስትሩ ገልፀዋል። አያይዘውም አቶ ስዩም ሲናገሩ የኤርትራ ባለሥልጣኖች ለዓለም አቀፍ ህጎችም ይሁን ለቀረቡት የማስታረቂያ ሃሣቦች ያሣዩት ደንታ ቢስነት በግልጽ የታዩ ሂደቶች ሆነው አልፈዋል ሲሉ ገልፀዋል።
የኤርትራ ባለሥልጣናት ኃላፊነት በጎደላቸው ተግባሮቻቸው የፈጠሩትና የጫሩት ጦርነት እሳት ማስቀሪያው ብቸኛው መንገድ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ያቀረበው ዕቅድ መሆኑን የተገነዘበ የዓለም አቀፍ ማህበረሰብ እምቢተኛው ወገን ላይ በቂ ጫና ባለማሣረፉ ኤርትራ በግትርነቷ እንድትገፋ ቀዳዳ ከፍቶላታል ሲሉ አቶ ስዩም አስገንዝበዋል።
አያይዘውም ኢትዮጵያ በወረራ የተወሰደባትን ግዛቷን ከማስመለስ ውጪ የኤርትራን መንግሥት ለመገልበጥ ሃሳብ እንደሌላትና ይህ የኤርትራ ህዝብ ጉዳይ እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ ሲመልሱ አብራርተዋል።
ኢትዮጵያ በቀራት አማራጭም ቢሆን መሬቷን ለማስመለስ ብቃት እንዳላት መጠራጠር አያስፈልግም ያሉት ውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ስዩም መግለጫውን በሰጡበት ዕለት አሁንም ጦርነቱ እንደሚቀጥል የመንግሥት ቃል አቀባይ አረጋግጧል።

## የተመድ የፀጥታው ምክር ቤት ውሳኔ አሳለፈ

በኢትዮጵያና በኤርትራ መሀከል የሚደረገው ውጊያ በአስቸኳይ እንዲቆም የጠየቀው የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት የጦር መሣሪያ ማዕቀብ እንዲደረግ ውሳኔ አስተላለፈ። በኢትዮጵያና ኤርትራ መሐከል ጦርነት መጀመሩ ያሳዘነው መሆኑን የተባበሩት መንግሥታ ድርጅት የፀጥታው ም/ቤት ባወጣው መግለጫ ገልጧል። ውጊያው በሲቪል ህዝብ ላይ የሚያደርሰው መዘዝ ያሳሰበው መሆኑን ካውንስሉ ገልጾ ውጊያው የሚቆምበትን መንገድ አባሎቹ በመፈለግ ላይ መሆናቸው ታውቋል። ምክር ቤቱ ከዚህ በፊት ባሣለፈው ውሳኔ መሠረት ውጊያው በአስቸኳይ እንዲቆም ጠይቆ የነበረ ሲሆን ጥያቄው በሁለቱም ወገኖች በኩል ተቀባይነት አላገኘም። የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናን አአድና ሌሎችም ድርጅቶች ውጊያው እንዲቆም መጠየቃቸው ይታወቃል።

## የዓለም ኅብረተሰብ ውጊያው እንዲቆም እየጠየቀ ነው

ካለፈው ቅዳሜ ጧት ጀምሮ በመካሄድ ላይ ያለው ጦርነት የሚያስከትለው ለውደቀት ለሁለቱም ወገኖች ስለማይበጅ ውጊያው ቆሞ ወደ ሠላማዊ ንግግር መግባት እንዳለበት የሚጠይቁ አስተያየቶች ከየአቅጣጫው እየተሰነዘሩ ናቸው።
የአሜሪካ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ወ/ሮ ማድሊን ኦል ብራይት የሁለቱን ሀገሮች ግጭት አስመልክተው ለአሜሪካ ድምፅ ራዲዮ በሰጡት መግለጫ ላይ፤ ጦርነቱ እንዳይቀስቀስ ሀገራቸው የተቻላትን ሁሉ መድከሟን ከተናገሩ በኋላ፤ በአፍሪካ ሁለቱ ተስፋ የሚጣልባቸው መሪዎች ውጊያውን ትተው በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ቢያተኩሩ ይሻላቸዋል ብለዋል።
የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ፀሐፊ ኮፊ አናንም በበኩላቸው ሀገሮቹ በትጥቅ ትግል ችግሮቻቸውን የመፍታቱን አማራጭ ትተው ወደ መነጋገር እንደገና እንዲመለሱ ጥሪ አቅርበዋል። የቡርኪናፋሶው ፕሬዝዳንትና የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም በተመሣሣይ ሁኔታ ውጊያውን ተቃውመው ለሁለቱም መንግሥታት በአስቸኳይ ተኩስ እንዲያቆሙ ያላቸውን ፍላጎት ገልጠዋል። የሚቀጥለው የአፍሪካ አንድነት የመሪዎች ስብሰባ የምታስተናግደው አልጄሪያም በጦርነቱ ምንም ትርፍ ሊገኝ እንደማይችል ገልጣ፤ አሁን እየተካሄደ ያለው እልቂት ቶሎ መገታት እንዳለበት ጥሪ አቅርባለች፤ ከአውሮፓ ሀገሮችም የጀርመኑ ውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዮርካ ፊሸር ሁለቱም መንግሥታት የወሰዱትን እርምጃ ተቃውመው ለሠላማዊ ጥረት ጥሪ ከማቅረባቸውም ሌላ የኢጣሊያ መንግሥት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ረዳት ኃላፊም ተመሣሣይ ተማፅኖ አቅርበዋል። ሰሞኑን ጅቡቲ ውስጥ ሲካሄድ የነበረው የኢጋድ አባል ሀገሮች የሚኒስትሮች ስብሰባም በማብቂያው ላይ ባሳለፈው ውሳኔ ጦርነቱ ቆሞ በሰላማዊ መፍትሔው መገፋት ወደሚችልበት መንገድ አባል ሀገሮች ግፊት እንዲያደርጉ ጠይቋል። በዚህ ስብሰባ ላይ ኢትዮጵያ በም/የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሯ የተወከለች ሲሆን በኤርትራ በኩል የእርሻ ሚኒስትሩ ተካፋይ እንደነበሩ ከዜና ዘገባዎች ለማወቅ ተችሏል። ሁለቱ ሀገሮች ወደ ጦርነት እንዳይገቡ በርካታ ጥረቶች መደረጉ የሚታወቅ ነው። እየደረሰ ካለው እልቂት አንፃር ግን የዓለም ማኅበረሰብና መንግሥታት ለጉዳዩ የሰጡት ትኩረት ቀዝቃዛ ሆኖ ታይቷል።

## ሻዕቢያ በምስጢር ያዘጋጀው ጦር መሣሪያ በቤልጂየም ታገተ

ሻዕቢያ ለሲቪል ኢንዱስትሪ ግንባታ የሚውሉ ታፔላዎች የተለጠፈባቸውና በውስጡ ግን የተለያዩ ጦር መሳሪያዎችና የመሳሪያዎች መለዋወጫ የያዘ እሽግ ሳጥኖች ወደ አገሩ ለማስገባት ሲሞክር በበልጄየም የደኅንነ ኃይላት ቁጥጥር ስር መዋላቸው የቤልጅየም ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አስታወቀ።
የቤልጅየም ውጭ ጉዳይ ቃል አቀባይ ለጋዜጠኞች በሰጡት መግለጫ የተያዙት ኮንቴይነሮች በውስጣቸው

ከባድ የጦር መሳሪያ የማኑ ተሸከርካሪዎች እና የዘመናዊ ታንኮች መለዋወጫ የሚሆኑ ሞተሮች ናቸው።
40 U.N.I ሞክ የጭነት መኪናዎች በውስጣቸው የጦር መሳሪያ እንደተጫነባቸው በኮንቴይነሮቹ ታሽገው ወደ ኤርትራ ሊጓዙ እንደነበር ያመለከተው ዘገባ ራሺያ ስሪት ለሆኑ T.54 እና T.55 ታንኮች መቀያየሪያ የሚያገለግሉ ሞተሮች በ51 የብረት ሳጥኖች ታሽገው ሊጓዙ እንደነበር በቤልጂየም የጦር ኤክስፐርቶች መረጋገጡን አስረድቷል። የጦር መሳሪያዎቹና ሞተሮቹ ስሙ ካልተጠቀሰ ከአንድ የእንግሊዝ ኩባንያ መጫናቸውን የሚገልፀው ይኸው የዜና ምንጭ መሳሪያው ከሮተርዳም ተነስቶ የአንትዎርፕ ወደብን በማቋረጥ ወደ ኤርትራ እንዲደርስ ታቅዶ እንደነበር አስረድቷል። ለጦር መሳሪያው መያዝ የቤልጂየም መንግስት በጦር መሣሪያ ዝውውር ላይ ያለው ጠንካራ ሚግና ጥብቅ ቁጥጥር አስተዋፅኦ ማድረጉን የሀገሪቱን የውጪ ጉዳይ ቃል አቀባይ ማስታወቁ ተገልጧል።

## <u>51 የሻዕቢያ ወታደሮች ከነዩኒፎርማቸው (ጂዛን) ሳዑዲ ዓረቢያ ገቡ</u>

51 የኤርትራ መንግሥት ወታደሮች ከተሰለፉበት የአሰብ ግንባር ከድተው በሞተር ጀልባ ተጉዘው ከነወታደራዊ ዩኒፎርማቸው ጂዛን (ሳዑዲ ዓረቢያ) ባሳለፈነው ሳምንት መግባታቸው ተሰማ።
እነኚህ ከአሰብ ግንባር በሞተር ጀልባ ተጉዘው ሳዑዲ ዓረቢያ ውስጥ የገቡ ወታደሮች የምድር ጦር ወይንም የባህር ኃይል አባላት ስለመሆናቸው በግልፅ ባይታወቅም የከዱታቸው መንስዔ የሻዕቢያ አምባገነን ሥርዓት በአጎራባች ሃገሮች ላይ በከፈተው ጦርነት ተዋናይ በመሆን መስዋዕትነት መክፈል በመጥላት እንደሆነ ታውቋል።
በኢትዮ ኤርትራ በቀይ ባህር በኢትዮ ሱዳን ድንበር በተናጠል ሁለት ወይም ሦስት ወታደሮች በትናንሽ ጀልባ በየብስ ላይም በእግር እየተጓዙ እጃቸውን ለተቃራኒ ሃገር ለተሰለፈ ኃይል መስጠት ዘወትር የሚደጋገም ትርዒት ቢሆንም ብዛት ያላቸው ወታደሮች በቡድን ሆነው ከነዩኒፎርማቸው ወደ ጎረቤት ሃገር በዚህ ዓይነት ሲኮበልሉ ይኼ የመጀመሪያው ነው።
ጂዛን ከድተው ስለገቡት 51 ወታደሮቹ ከኤርትራ መንግሥት የቀረበ ጥያቄ እስካሁን ባይኖርም ከዕለት ወደ ዕለት በኢትዮ ኤርትራ ድንበርም እይከዱ እጃቸውን የሚሰጡ ወታደሮች መበራከት የኤርትራ መንግሥት በግዳጅ እየተመለመሉ ወደ ጦር ግንባር በተላኩ ዜጎች ሰራዊቱ የተገነባ ስለመሆኑ ጠቋሚ ምልክት መሆኑን ወታደራዊ ታዛቢዎች ይገልፃሉ።
<u>ከሪፖርተር የካቲት 1 ቀን 1991</u>

## የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመሩን ወደ ናይሮቢ አዛወረ

በተፈጠረው ወቅታዊ ሁኔታ የተነሳ የኢትዮጵያ አየር መንገድ የበረራ መስመሩን በናይሮቢ በኩል ማድረጉን የኢትዮጵያ ሬድዮ በጥር 29 /1991 ስርጭቱ አስታውቋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በረራዎቹ በሙሉ በናይሮቢ በኩል ሲያልፉ ሁሉም መንገደኞች ወደሚፈልጉበት አቅጣጫ ያለብዙ መጉላላት እንዲደርሱ ከፍተኛ ጥረት እንደሚደረግ ማመልከቱን የሬድዮው ዘገባ ያስረዳል። ከአዲስ አበባ ለሚነሱና ወደ አዲስ አበባ ለሚመጡ መንገደኞች ግን በአዲስ አበባና በናይሮቢ መካከል በረራዎች እንደሚኖሩም አየር መንገዱ አስታውቋል። ከሰሜን ኢትዮጵያና ከድሬዳዋ በስተቀርም ወደሌሎች የአገር ውስጥ ጣቢያዎች የሚደረገው በረራ እንደሚቀጥልም ጭምር ገልጿል።

## ፈረንሣይ በጅቡቲ ላይ ለሚሰነዘረው ጥቃት እበቀላለሁ አለች

በፈረንሳይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አማካሪ በሆኑት ጆርጅ ሴሪ የተመራው ወታደራዊና ሲቪል ባለሥልጣናት ያሉበት የልዑካን ቡድን የሻዕቢያ መንግሥት በጅቡቲ ላይ እንዳችም ወታደራዊ ርምጃ የሚወስድ ከሆነ የፈረንሳይ መንግሥት የአፀፋዊ ወታደራዊ ምላሽ እንደሚያደርግ ለኢትዮጵያና ለአስመራ ባለሥልጣናት በላከው ደብዳቤ ማስጠንቀቁን ኢንዲያን ኦሽን የተሰኘው ጋዜጣ ዘግቧል። የኤርትራና የኢትዮጵያ የድንበር ግጭት ወደ አጠቃላይ ጦርነት እያመራ መሆኑ ያሳሰበው የፈረንሳይ መንግሥት ሻዕቢያ የጅቡቲ መንግሥት ከኢትዮጵያ ጐን ቆሟል በሚል የበቀል ርምጃ ለመውሰድ መዘጋጀቱ እንዳስቆጣው ገልጦ የሻዕቢያን መንግሥት አስጠንቅቋል። ይኼውም ማስጠንቀቂያም ለኢትዮጵያ መንግሥት እንደደረሰ ጋዜጣው ጨምሮ አስታውቋል።
የፈረንሳይ የልዑካን ቡድን ወደ አሥመራና አዲስ አበባ ያመሩት ሁለት ተልዕኮ ይዘው እንደነበር የዘገበው ኢንዲያን ኦሽን አንደኛው ተልዕኮ ሁለቱም አገሮች የኦኡድን የማስማሚያ ሃሳብ እንዲቀበሉ ማድረግ ሲሆን ሁለተኛው ተልዕኮ ደግሞ ሁለቱ ሃገሮች በሚያደርጉት ጦርነት ሳቢያ ጅቡቲ በአንዳቸውም የጦር ኃይል ጉዳት እንዳይደርስባት ለማስጠንቀቅ መሆኑን ጋዜጣው በዘገባው አስፍሯል።
ይህ ሳይሆን ቀርቶ ይላል ኢንዲያን ኦሽን በጅቡቲ ላይ ከየተኛውም ወገን ለሚደርስበት ጉዳት የፈረንሳይ መንግሥት የመልሶ ማጥቃት ርምጃ ለመውሰድ የሚያስችሉ አካባቢዎች አስቀድሞ የተጠኑ መሆናቸውን ልዑካኖቹ ማስታወቃቸውን ገልጧል።
የፈረንሳዩ ወታደራዊ ጄኔራል እንደተናገሩት ከሆነ የሻዕቢያ ሠራዊት በጅቡቲ ድንበር አካባቢ የኢትዮጵያን ለማጥቃት የአካባቢው መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ሊያስቸግሩት ይችላሉ። ምናልባት የኢትዮጵያን የየብስና መገናኛ መስመሮችን በመቁረጥ ኢትዮጵያ በጅቡቲ ወደብ በምታስገባቸው ንብረቶች ላይ አደጋ የማድረስና የባቡር መሥመሮችን የማፈራረስ እቅድ እንዳለው ገልጠው ፈረንሳይ ይህን መሰሉን እንቅስቃሴ በንቃት እንደምትከታተለው መግለጣቸውን ከጋዜጣው ዘገባ ለመረዳት ተችሏል።
የፈረንሳይ መንግስት በአካባቢው 8000 ያህል ሲቪልና የጦር ኃይል የሆኑ ዜጎች እንዳሉት ዘገባው ጠቅሶ ለአካባቢው ሰላም መጠበቅ ሲባል ከፍተኛ ኃይሏን ለማስፈራሪያነት እንዳሰፈረችም ገልጧል። በተጨማሪም ከፍተኛ የሆኑ የጦር መርከቦችን በቀይ ባህር በኩል

አስገብታ ጠረፋማ አካባቢዎችና በዓለም አቀፉ የውሃ መስመር ላይ ተከታታይ ወታደራዊ ቅኝት እያደረገች መሆኗንም ጋዜጣው ጨምሮ ገልጧል።
ይኼው የፈረንሳይ ከፍተኛ ልዑክ የኢትዮጵይና የኤርትራ ባለሥልጣናት በጅቡቲ ጉዳይ ካነጋገረ በኋላ ሁለቱም መንግሥታት ጅቡቲን ላለመንካት ቃል ተገብቶላቸው ወደ ፓሪስ ተመልሰዋል ሲል ዜናው አስረድቷል።
ሆኖም የፈረንሳይ ልዑክ የተገባለት ቃል በተግባር መታየት እንደሚገባው አስጠንቅቆ በተሰጠው ተስፋ ጥርጣሬ እንዳደረበት ጋዜጣው ሳይጠቅስ አላለፈም።

## ዴር ሱልጣን ገዳምን ሻዕቢያ የኔ ነው አለ

ሻዕቢያ በእስራኤል አገር የሚገኘውን ጥንታዊ የኢትዮጵያ ገዳም ዴር ሱልጣን የእኔ ነው በማለት በገዳሙ ውስጥ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን መነኮሳትን በወሮበሎች በማስደብደብ አስወጥቶ ገዳሙን ለመውረስ ሙከራ ማድረጉን ከቴሌአቪሟ የደረሰን ዜና ያመለክታል። ዴር ሱልጣን ገዳም በኢትዮጵያ ይዞታ ስር ለረጅም ዘመናት የቆየ ሲሆን ግብፃውያን መነኮሳት በሃይማኖት ወንድምነት ስም ተጠግተው ኢትዮጵያውያን መነኮሳቱን በመርዝ ፈጅተው በመጨረስ ለረጅም ዘመን ተቆጣጥረውን ሲኖሩ በኢየሩሳሌም መታሰቢያ ድርጅት እና በመሪው በአቶ መኮንን ዘውዴ ብርቱ ተጋድሎ በቀረበ ታሪካዊ ማስረጃ ለኢትዮጵያ መመለሱን ታሪክ ያስረዳል።
ዴር ሱልጣን ገዳምን ከኢትዮጵያ ለመንጠቅ ኤርትራ ሙከራ ስታደርግ ይህ ሁለተኛ ጊዜ መሆኑን የጠቆመው ዘገባ በኢጣልያ ቅኝግዛት ስር በነበረችበት ዘመን ኢጣልያ ኤርትራን ተተግና የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ይዞታችንን በሮማ ካቶሊክዊት ቤተክርስቲያን ስር ለማጠቃለል የኤርትራ መነኮሳትን አነሳስታ እንደነበር ያስረዳው ዘገባ ባሁኑ ወቅት የኤርትራ መነኮሳትና ቅጥር ወሮበሎች አቅመ ደካማ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን አበው መነኮሳትን በመደብደብ ከገዳሙ ቢያባርሯቸውም የእስራኤል መንግስት ጣልቃ በመግባት ረብሻውን ካስቆመ በኋላ ቀደም ሲል እነ አቶ መኮንን ዘውዴ በጠ/ሚ/ር ጉልዳ ሜዬር የሚመራው የእስራኤል ካቢኔ ድረስ ጉዳዩን በማቅረብ ያስወሰኑትን በማፅደቅ የዴር ሱልጣን ይዞታ የኢትዮጵያ መሆኑን አረጋግጧል። ሆኖም ገዳሙ ውስጥ ለአገልግሎት የሚገቡትን በመልክ ብቻ መለየት አስቸጋሪ በመሆኑ ኢትዮጵያውያን ብቻ እንዲገቡ ለመለየት እንዲቻል ማንኛውም መነኩሴም ሆነ አገልጋይ ኢትዮጵያዊነቱን የሚገልፅ ሚጋዊ ማስረጃ ከአገሩ እንዲያመጣ የእስራኤል መንግሥት መመሪያ በማውጣቱ አገር ቤት ተላልከው ማስረጃው የደረሳቸው መነኮሳትና አገልጋዮች ባሁኑ ወቅት ገዳሙ ውስጥ መግባታቸውንና ያልደረሳቸው ግን ከገዳሙ ውጭ ሆነው እየተጠባበቁ እንደሚገኙ የቴልአቪቭ ሪፖርት በማስረዳት የእስራኤል መንግስት ሁከቱን በማብረድ የወሰደውን እርምጃ አድንቋል።

## ኦነግ የአመራር ለውጥ አደረገ

ባለፈው ዓመት በሕወሀት በሚመራው መንግሥትና በኦነግ መካከል የተሞከረው ድርድር በመክሸፉ ሳቢያ በኦሮሞ ነፃነት ግንባር ውስጥ የአመራር ለውጥ ማስከተሉን አፍሪካ ኮንፊዴንሻል ጋዜጣ ዘገበ። እንደጋዜጣው ዘገባ ከሆነ በሞቃዲሾ በተደረገው የድርድሩ ጉባኤ ላይ ዘጠኝ አባላት ያሉት የፖሊት ቢሮ መሰየሙን አትቷል። በዚህም መሠረት ገላሳ ዲልቦ የድሮ ቦታቸውን እንደያዙ የቀጠሉ ሲሆን የሚጠሩት ግን እንደድሮው ዋና ፀሐፊ ተብለው ሳይሆን ሊቀመንበር ተብለው መሆኑን ገልጿል። ከድሮው የፖሊት ቢሮ አባላት ሶስቱ አሁንም በአባልነት እንዳሉ የገለፁ ሲሆን እነሱም ዳጉሳ በካኮ፣ አባቢያ ሮባ፣ እንዳ ዳውድ ኢብሳ ናቸው። የተቀሩት አብዱል ፈታህ ሙሳ ቢዮ ሌንጮ ለታን በመተካት ምክትል ሆነዋል። ኩምሳ ገዳ፣ ሙሊስ ገዳ እና ቆፍሳ ሰባ ናቸው ብሏል። ጋዜጣው እንደሚለው ከሆነ ከምስራቅ የመጡ ሙስሊም ኦሮሞዎች በፖሊት ቢሮ ውስጥ አሁን የበላይነት አላቸው። የፖሊት ቢሮው አብዛኛው አባላት ነፃ ኦሮሚያን የሚፈልጉ ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር መነጋገሩ ዋጋ የለውም ብለው የሚያምኑ ናቸው። ከፖሊት ቢሮ የተገለሉት አብዛኞዎቹ ከምዕራብና ከመካከለኛው ኦሮሚያ ናቸው ሲልም አትቷል። እንደጋዜጣው ከሆነ የተገለሉት የፖሊት ቢሮ አባላት የሚወክሉት የከተማውን ምሁር ኦሮሞ ነው። ሆኖም አሁንም ድረስ ቢሆን ከፖሊት ቢሮው ይገለሉ እንጂ 44 አባላትን የያዘው የድርጅቱ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ናቸው ሲል አትቷል። የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ናቸው ካላቸው መካከል ሌንጮ ለታ፣ ዮሐንስ ነገዎ፣ ጠሐ አብዲ፣ ፍቃዱ ዋቅጅራ፣ ዶ/ር ታደሰ ዴባ፣ ኢብሳ ጉተማ ይገኙበታል።
በሞቃዲሾ በተደረገው ጉባኤ ለገላሳ ድል ነበር ያለው ጋዜጣ በዚያን ወቅት ገላሳን ለማውረድ የተሸረበ ሴራ እንደነበር ገልጿል። ከአሁን በኋላ ድርጅቱ ስለምርጫ ማሰብ ትቶ በትጥቅ ትግሉ እንደሚያተኩር ጋዜጣው አትቷል።

## የኦነግ አባላት ከሞቃዲሾ ተጠለፉ

ሶስት የኦሮሞ ነፃነት ግንባር አባላት ከሞቃዲሾ ተጠልፈው ለኢትዮጵያ መንግሥት መሰጠታቸውና የተጠለፉትም ከ10 በላይ በከባድ በታጠቁ ሚሊሺያዎች መሆኑን ቢቢሲ ጥር 27 1991 ባስተላለፈው ዜና አስታውቋል። የተጠለፉት የቀድሞ የኢትዮጵያ መንግሥት ወታደሮች የሆኑና አሁን ላለው መንግሥት አንሠራም ያሉ ናቸው ይላል ሆኖም የተጠለፉት ስደተኞች ሲሆኑ መጠለፋቸውን ያወገዘው የኦነግ ተወካይ ሃጂ መሐመድ አህመድ ተጠልፈው በሂራን በኩል ለኢትዮጵያ መንግሥት የተሰጡት አብዱልሃሪም ዓሊ እስማኤል ኢዘዲን እና አብዱራህማን የተባሉ ናቸው ብሏል።
ይህ በእንዲህ እንዳለ የግንቦት 1983 ዓ.ም የመንግስት ለውጥ እንደተከሰተ ሀገር ጥለው የተሰደዱትና አሁን በኡጋንዳ በስደት የሚገኙት የቀድሞው የኢትዮጵያ አየር ኃይል አብራሪ ስሞኑን ከሻዕቢያ ሬድዮ ጋር ቃለ ምልልስ አድርገዋል። በአስተማሪነትና በአብራሪነት ከ27 ዓመት በላይ ያገለገሉት ኮሎኔል ዋቅጋሪ ገመቹ

አሁን ስለተፈጠረው የወቅቱ የድንበር ግጭት በማንሳት ግጭቱ በወያኔ የመስፋፋት ስሜት የተፈጠረ ነው ብለውታል። ከዚህም ጋር በማያያዝ በመቀሌና አዲግራት በሻዕብያ አይሮፕላን የተጨፈጨፉት ንፁህን ዜጎች ሚይወት የተቀጠፈው በወያኔ መንግሥት ጥፋት ነው ብለዋል።

እኚሁ የቀድሞው አየር ኃይል ከፍተኛ መኮንን ወያኔ ስልጣኑን ከተቆናጠጠ በኋላ ወደ አየር ኃይል እንዲመለሱ መጠየቃቸውንና ይኼንንም ባለመቀበላቸው ተደላድለው ከሚኖሩበት ስደት ለሌላ ስደት መዳረጋቸውን ገልፀው፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በዚህ ጦርነት እንዳይሳተፍ ጥሪ አስተላልፈዋል።

## አባ ጳውሎስ ተቃውሞ ገጠማቸው

ኢትዮጵያንና ኤርትራን ለማስታረቅ በሚል ወደ ጀርመን የተጓዘው በአባ ጳውሎስ የሚመራው ከፍተኛ ልዑክ ጥር 16 ቀን 1991 ለትግሪኛ ተናጋሪዎች ብቻ በምስጢር ያደረገውን ጥሪ የሰሙ ተቃዋሚዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ ተገኝተው ባደረጉት ተቃውሞ ፓትርያርኩ ያቀዱትን ሥርዓተ ፀሎት ማደናቀፋቸውን ታወቀ።

አባ ጳውሎስ ትግሪኛ ተናጋሪዎችን በምስጢር ባስጠሩበት ሥርዓተ ፀሎት ላይ ደጋፊዎችና ተቃዋሚዎች የተገኙ ሲሆን፤ በተለይ ተቃዋሚዎች ቅሬታቸውንና ስሞታቸውን ከቤተክርስቲያን ውጪ ሆነው ለማሰማት ከፍተኛ የሆነው ብርድ ስላላስቻላቸው ወደ ውስጥ መግባታቸው ተገልጿል። አባ ጳውሎስ ምዕመናኑን ለመባረክና ለመስበክ መድረኩ ላይ በወጡበት ወቅት ተቃዋሚው «እርስዎ በጎሰኝነት የሚያምኑ ስለሆኑ የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ለመወከል አይችሉም። ቡራኬዎንም ስለማንፈልግ መናገር አይገባዎትም» የሚል ድምፅ ማሰማቱን ከስፍራው የዘገበው ሪፖርተራችን አስታውቋል።

በሁኔታው የተደናገጡትና በጀርመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ተወካይ የሆኑት ቄስ መርአዊ ተበጀ ፀጥታ አስከባሪዎችን ከመጥራታቸውም በተጨማሪ በደጋፊና በተቃዋሚ መካከል የገቡትን ወደ ሃያ የሚጠጉ ፖሊሶችን ተቃዋሚዎችን እንዲበትኑ ቢገፋፉም «በጀርመን ሀገር ሰላማዊ ተቃውሞ ማድረግ የተፈቀደ ስለሆነ ተቃዋሚዎች ፀብና ሁከት ካላነሱ ልናስወጣቸው አንችልም» የሚል መልስ የተሰጣቸው መሆኑ ታውቋል። በዚህም ምክንያት ጳጳሱና ተከታዮቻቸው ለሃያ ደቂቃ ያህል ሠሩ የተባለውን በደልና ግፍ አዳምጠው እንደጨረሱ በሌላ በር በፖሊስ ታጅበው ስለወጡ የታሰበው ፀሎት ሳይደረግ መቅረቱ ተገልጿል።

ስደተኛው ወደፊት ራሱን የቻለ የስደተኞች ቤተክርስቲያን ለመመስረት እንዲችል በስደት ላይ ከሚገኙት ጳጳስ ጋር ተነጋግሮ በቅርቡ አስፈላጊው እንደሚደረግ ቃል ስለገቡላቸው ችግሩ ሊወገድ እንደሚችልም ተጠቁሟል። አባ ጳውሎስ አሜሪካ አገር በስደት በነበሩበት ወቅት የትግርኛ ተናጋሪዎች ቤተክርስቲያን አቋቁመው እንደነበር ያለፈ ታሪካቸውን የሚያውቁ ሰዎች ይናገራሉ።

## ተቀጥረው በሚሠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የደረሰ በደል

ዋሽንግተን— በቤት ሠራተኝነት ተቀጥረው ወደ አሜሪካ የገቡ በርካታ ሰዎች በአሠሪዎቻቸው ከፍተኛ በደል እየተፈፀመባቸው እንደሚገኝ በአሜሪካ የሚታተመው ዕለታዊ ዋሽንግተን ፖስት ጋዜጣ አጋለጠ። በቤት አገልጋይነት ከሚሠሩት እነዚሁ ሠራተኞች አብዛኞዎቹ ሴቶች ሲሆኑ በድህነታቸው ከሚታወቁት ከአፍሪካ፣ ከእስያና ከላቲን አሜሪካ የሄዱ ናቸው። የሥራ ቦታዎችም እንደ ጋዜጣው ዘገባ በኤምባሲዎች፣ በዓለም አቀፍ፣ ተቋማትና በዋሽንግተን ከተማ በሚገኙ የተለያዩ የግል መኖሪያ ቤቶች ናቸው። በጋዜጣው ከተጠቀሱትና በደል ከደረሰባቸው መሀል የምትገኝ አንድ ኢትዮጵያዊ ኢ.ኢ.አ በ1990 ዓ.ም ወደ አሜሪካ የሄደች ናት። በሲልቨር ስፕሪንግ አፓርትመንት ለስምንት ዓመታት ተቀጥራ በሠራችበት ወቅት አሠሪዎቿ ከሌሎች ሰዎች እንዳትገናኝ በማድረግ ሳምንት ሙሉ እያሰሯት ቅሬታ ካቀረበችም እየደበደቧት እንደቆየች ከአመለጠች በኋላ ለባለሥልጣናት ጉዳዮዋን አስረድታለች። ሌላዋ ኢትዮጵያዊት ደግሞ በቱሪስት ቪዛ ወደ አሜሪካ የወሰዷት ኢትዮጵያውያን ሮክቪሉ ቤት ለስድስት ዓመታት ያለክፍያ እንድታገለግል ተደርጋለች።

ከስምንት ዓመት በፊት ምንም ዓይነት የእንግሊዘኛ ቋንቋ መናገር በማትችልበት ሁኔታ ወደ አሜሪካ ተወስዳ ለከፍተኛ ችግር የተዳረገችው የሺሃረግ ተፈራ የተባለች ወጣት ኢትዮጵያዊት ሌላዋ የችግር ሠለባ ናት። የሺሃረግ እንደምትለው በአማካይ በሳምንት ከ90 ሰዓት በላይ እየሠራች በስምንት ዓመት ውስጥ የተከፈላት በድምሩ አንድ ሺ ዶላር ብቻ ነው። ይህም ማለት በሰዓት ከሦስት ሳንቲም ያነሰ ማለት ነው።

እንደጋዜጣው ዘገባ አይና አፋሯ የሺሃረግ በጉንጯ ላይ የሚወርደውን እንባ መግታት አቅቷት የደረሰባትን ስትናገር መከራውን ልትቋቋም ባለመቻሏ ከአሳደሪዎቿ ልታመልጥ በቅታለች። የወጣቷን ችግር የተገነዘቡ አንድ ማርክኤ ሺፈር የተባሉ ጠበቃ ቀሪ ክፍያዋንና ካሳዋን ጨምሮ አሳዳሪዎቿ የዘጠኝ መቶ ሺ ዶላር ክፍያ እንዲሰጧት ችሎት ላይ ገትረዋቸዋል።

ዳዊት መኮንን የተባለውና ባለቤቱ መስከረም ወጣቷን በእንግድነት በቤታችን የተቀመጠች ነች በማለት በጠበቃቸው በኩል መልስ ቢሰጡም የሺሀረግ እንግዳም፣ ሠራተኛም ሳልሆን ባርያቸው ነበርኩ በማለት የሰጠችው መልስ የሚሰጡትን ምላሽ አሳጥቷቸዋል። ከችግረኛ ቤተሰብ የተገኘችውና ከትውልድ ሀገሯ ከወሎ የ9 ዓመት ልጅ እያለች ወደ አዲስ አበባ መጥታ የዳዊት ባለቤት ቤተሰቦች ጋር በቤት ሠራተኝነት ተቀጥራ ትሠራ ነበር። ችግሩ በዝቶባት ያለቀሰች እንደሆነ ከረሃብ ሀገር አምጥተን ይህን ውለታ ውለንልሽ እንዴት እንዲህ ትሆኛለሽ በማለት መስከረም ትቆጣት እንደነበረም ለጋዜጣው ገልፃለች። በመጨረሻም ወደ ኢትዮጵያ ሊልኳት ማሰባቸውን በመረዳቷ ልታመልጥ እንደቻለች ጨምራ ተናግራለች። ችግረኛ ቤተሰብን ለመርዳት በሚል ለዚህ መሰል ችግር የሚጋለጡ ወገኖች ቁጥር በምድረ አሜሪካ በመበራከቱ የፌዴራሉን ቢሮ እንዳሳሰበውና በቅርብ እንደሚከታተለው መገለጹን ጋዜጣው ዘግቧል።

# አ. .ይ. .ሰ. .ማ. .ም !!

## (ከጦራ ጦጦራ – ከአዲስ አባ)

ቄስና ዲያቆን፦

ከፉ ... ኛ! ተጠማምደዋል።

አንዱ፦ ያንዱን ኃጢያት አነፍንፎ እየመዘገበ ... ሌላኛው የሌላኛውን ነውር አሽትቶ እየከተበ ...ውስጥ ውስጡን ይፋተጋሉ።... የጐሪጥ ይተያያሉ። ይሿሿፋሉ። ...የጨቀርሳ ይመነጣጠራሉ።

አንድ ቀን ለቁርባን ከተዘጋጀው ሥጋ ወደሙ ዲያቆኑ ቆንጠር አድርጐ ወደ አፉ ሲጨምር አይን ለአይን ይጋጣሉ። – ከቄሱ ጋር!

ከቀናት በኋላ የደብሩ ስብሰባ ሲካሄድ "የልቤ ሞላልኝ" ብለው ተነሱ። –ቄሱ። ...እናም ወደ ድምፅ ማጉያው ሔዱ። ሔዱናም፦

"ከናንተ መሃል! ...ሥጋ ወደሙ ሰርቆ የበላ ማነው!!??" በቁጣ ጠየቁ። ...ካህናቱ ተደናገጡ። ...ይሄኔ ዲያቆን ሆዬ ብድግ አለና ድምፁን ከፍ አድርጐ፦

"አይሰማም!!"አለ።

"እዚህ ከተሰበሰባችሁት ውስጥ! ...ሥጋ ወደሙ ሰርቆ የበላ ሰው አለ። ...ራሱን ያጋልጥ! ...ማነው!?" ቄሱ በድጋሚ በንዴት አምባረቁ!

"እረ አይሰማም!!" ዲያቆኑም ከጣራ በላይ ጮኸ!...

ቄሱ ተበሳጩ። በምሬት ተንደርድረው ከመድረኩ ወረዱና ከተሰበሰበው ካህን መኃል ተደባለቁ። ...እናም ያን ዲያቆን "እንዴት ነው የማይሰማው ባክህ!? ...እስቲ አንተ እዛ ሂድና ተናገር!" አሉት። – በቁጣ።

ዲያቆኑም አፈፍ ብሎ ተነስቶ ወደ ድምፅ ማጉያው ሄደ። ጉሮሮውን ጠራረገና፦

"ከናንተ መኃል! ...የሰው ሚስት ያማገጠ ማነው!?" ድምፁን ከፍ አድርጐ ጠየቀ።

ቄሱ ከተቀመጡበት ተነሱ። ከው! ብለዋል! ...እናም ተናገሩ! – እንዲህ ብለው፦

"እውነትም! ...አይሰማም ልጄ!"

...ካለፈው ግንቦት ወር ወዲህ በየዕለቱ ...ደቂቃና ሰዓቱ ... የሚፈነዱና የሚንዷዱ ጩኸቶች በርክተዋል። – ግን አንዳቸውም አይሰሙም። የተንደረደርኩበትን "ቀዛ" ያስታወሰኝም ይኸው ጩኸት ነው። – የማይሰማው ጩኸት!

ኢህአዴግና አውራዎቹ! ...ሹመኛና አጋፋሪዎቹ ...ማጩት ካድሬዎቹ ሳይቀሩ ...ስለ ሻዕቢያ ታላቅነትና ክቡርነት! ...ብርቱና ኃያልነት! ...ፃድቅና ቅዱስነት...ሰ–ባት ዓመት ሙሉ ሲነግሩን ...ሲመስክሩና ሲያስረዱን ኖረዋል። – ድፍን ሰባት ዓመት!

ስለሻዕቢያ ደግነትና ርህሩህነት ...ምጥቀትና ግዝፈት! ...ጀግንነትና ቆራጥነት ...ሰብዓዊነትና ዲሞክራትነት ...ሻዕቢያ ራሱ ስለራሱ ከነገረን ይልቅ ኢህአዴግ የመከረን ይበዛል።

ስለ ውበቱ ...መልከመልካምነቱ ሳይቀር ደከመኝ፣ ሰለቸኝ ሳይል ኢህአዴግ አስረድቶናል። ...ወያኔ ገልፆልናል። ..."እምቢየ! ...ይሄ ሁሉ አይገባንም! ሊገባንም አይችልም!" ያልነውን ...በግፍ በትር እየዠለጠ ...እየሸነቆጠና እየቆነጠጠ ...እስካለፈው ግንቦት ድረስ ዘለቀ። – ኢህአዴግ!

ዛሬ! ...ውዳሴውና ቅዳሴው ተለውጧል። በምትኩ እርግማንና ኩነኔ ተተክቷል። – ግን አይሰማም!!

የማይሰማን፦ ነውረኛውን ዲያቆን ስለሆንን አይደለም። ኃጢያተኛውን ቄስ በመሆናችንም አይደለም። የማይሰማን ስለማይሰማን ነው።

ከግንቦት አራት ወዲህ እየተስተጋባ ያለውን ጩኸት ...እኛ ሰባት ዓመት ሙሉ ጮኸነዋል። በዚህም ደግሞ "ዋጋችን" ተከፍሎናል። – እስራት፣ ግርፋትና ...ስደት!

መሰንበት ደግ ነው! ...ዛሬ "ዋጋው" እላይ ወጥቷል! ...ያሾማል! ያሸልማል! ...ለዚህም ነው የትናንት ቀዳሽና አወዳሽ ሁላ ዛሬ አውጋዥና አንቋሻሽ የሆነው። ...እንዳውም ከማንም በላይ ዛሬ የሚጮኹት እነርሱ ናቸው። ክፋቱ ግን አይሰማም። ...ምን እያሉ እንደሆነም አይሰማ!

ትናንት ሻዕቢያን ሲያወድሱና ሲያንቆለጳጵሱ! ...ሲያስውቡና ሲቀባቡ ...ሲክቡና ሲገነቡ ...አልፎ ተርፎም ደረት ነፍተው፣ ሸንጥ ሰብቀው ...ጡንቻ አፈርጥመው ሲከራከሩለትና ሲሟገቱለት የነበሩ ሁላ ዛሬ በአንፃራዊነት እየጮኹ ነው። – የማይሰማ ጩኸት!

"ዛሬ ሻዕቢያን ለማውገዝ፣ ለመዝለፍና ለማብጠልጠል አቅምና ብቃቱ እምነትና ፅናቱ ያለን እኛ ብቻ ነንና ሌሎቻችሁ ዝም በሉ! ...ኡስስስስ...!!" በማለት የኛን አፍ ለማስያዝ የዳዳቸው የትናንት የሻዕቢያ ቀዳሽና አወዳሾች ብዙ ናቸው። ብዙም እያሉ ነው። ...ብዙ እየጮኹ! ...ግን ጥቂትም እንኳ አይሰማም።

ኢህአዴግ ...መለስ ዜናዊ ...አባይ ፀሐዬ ...ዶ/ር አብዱል መጂድ ...ዳዊት ዮሐንስ ...አዲሱ ለገሰ ...ምሑር ተብዬው ዶ/ር ብሩክ ...ዶ/ር ተቀዳ አለሙ ...የኢትዮጵያ ሬዲዮ ...ሬዲዮ ፋና! ...ቲቪ ...አብዮታዊ ዴሞክራሲ ...ሪፖርተር ...እፎይታ ...እነዚህ ሁላ ትናንት ስለሻዕቢያ ምን ይሉ እንደነበር በትክክል እናውቃለን። የማናውቀው ዛሬ ምን እያሉ እንደሆነ ነው። ...ምክንያቱም የሚናገሩት ሁላ አይሰማማ!!

እነርሱ ትናንት ቄስም ዲያቆንም ሆነው ሻዕቢያን አገልግለዋል። ቀዳሽም አስቀዳሽም ሆነው ሰብከውለታል። ...አሸብሻቢም አጨብጫቢም ሆነው ረግደውለታል። ...ድቤ መትተው ዘይረውለታል። መሬትና ምንጣፍ፣ ስጋጃና ሰሌን ሆነውለታል። ...ሁሉንም ሆነው ተነጥፈውለታል። ከቶውንም በእኛም ላይ ጭምር እንዲረማመድ ...ተመችተውለታል ...አመቻችተውለታል።

...ታዲያ! ...ይሄን ሁሉ የትናንት ነውርና ኃጢያት በጉያቸው ይዘው ...ዛሬ ቢጮኹ እንደምን ይሰማናል?...

"ስለ ኤርትራ ህዝብ ነፃነት ታግለው፣ የአይን ብርሃናቸውን አጥተው፣ አካላቸው ጉድሎ ...መብታችን አልተከበረልንም በማለት ስሞታ ለማሰማት ወደ አሥመራ በመጓዝ ላይ ሳሉ አትመለሱም? ብለው የራሳቸውን አካለ ስንኩላን ታጋዮች በጥይት ቆሉ!" – መለስ ዜናዊ

አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

"በአሥመራ ያለው አመራር ለኤርትራም ሆነ ለኢትዮጵያ ...ለአፍሪካ ቀንድ ህዝቦች አይበጅም!" – ዶ/ር አብዱል መጅድ ሁሴን

አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

"ሻዕቢያ እንደቆሰለ ጅብ ሥጋውን መንጨት አመሉ ነው!" – መለስ ዜናዊ

ኧረ! ... አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

"የኢትዮጵያና የኤርትራ መንግሥታት ያላቸው ባህርይ አብሮ ሊሄድ የሚችል አልነበረም" – ዶ/ር ብሩክ ኃይሌ

ምሑር! ... እባክዎን አይሰማም!!

"በአሥመራ አምስት ዓመት የዲፕሎማቲክ ተግባሬ እንደ ኤርትራውያኑ አስቸጋሪ ሰዎች አላየሁም" አቶ ተቀዳ አለሙ።

አቤት!? ...ምን አሉ? ...አይ .. ሰ .. ማም!!

ለመሆኑ!... እነዚህ ሰዎችና አባባሎች ትናንት የት ነበሩ? ... ይሔንማ እኛ ከነሱ ቀድመን ስንለው ኖረናል። – ድፍን ሰባት ዓመት ሙሉ!

"...ተዎአቸው! ...የሚፅፉትና የሚናገሩት ሁሉ ህልማቸውን ነው!..." ይሔን ነበር ያሉት መለስ። – ትናንትና!

ዛሬስ!?

"ሻዕቢያ ከእግሩ የሚበልጥ ማማ የሚጫማ ወይም መጫማት የሚሻ ነው። በሽፍጥ ይሁን በዕብሪት በሌላው ጫንቃ ላይ እንደመዥገር ይጣበቃሉ። ...የራሱን ታጋዮች ራሱ በጥይት የቆላ ቡድን ክህደት ቢፈፅም ምን ይደንቃል!?" – መለስ ዜናዊ!

አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

"ሀገሬን ሀገሬን ሻዕቢያ አይደፍራትም
እንኳንስ እምብርቷን ጫፏን አይነካትም" – የኢትዮጵያ ሬዲዮ ዘፈን

ተባለ እንዴ!? ... ኧረ አይሰማም!!

እናውቃለን እኮ! ...የኢትዮጵያ ሬዲዮ ከግንቦት 20/1983 እስከ ግንቦት 20/1990 ድረስ ...አንዲትም ቀን እንኳ! ...እንዳው ሳት ብሎት እንኳ! ...ሀገሬ ኢትዮጵያ የሚል ዘፈን አሰምቶ ያውቃል!?

"ሻዕቢያ በአሰሳ ያደረሰው ዕልቂት ይህን ይመስላል ..." – የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን

ኧረ ባኮ! ... አ .. ይ.. ታ.. ይ..ም!!

"እብሪተኛው የሻዕቢያ መንግስት ..." የኢህአዴግ ጋዜጦች – እፎይታ፣ አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ ሪፖርተር ...የዘወትር ዘገባ!

አ .. ይ .. ነ .. በ .. ብ .. ም!!

አዎን! ...ይሄ ሁሉ ነገር ለእኛ አዲስ አይደለም። ትናንት ብለነዋል። ... ትናንት ተናግረነዋል።

የሻዕቢያን እብሪትና እኩይነት ...ነዶ ዘርጣጭነት ...ሴማት ገልባጭነት! ወጭት ሰባሪነትና ጉስጓስ በርባሪነት! ...ገና ከማለዳው አንስቶ ...ብዙ ብዙ ...እጅግ በጣም ብዙ ብለናል። ...ይህን በማለታችንም ...ተብለናል!

በብዕራችን ከትበናል! ...በጋዜጣና መፅሔታችን አትመናል። ...ሞኽናል! ...መክረናል! ...ዘክረናል! ...አሳውቀናል! ...አስጠንቅቀናል! ...አሳስበናል! ...አስገንዝበናል! ...ኡኡ ብለናል ...እሪሪሪሪሪ!! ...ብለናል።

ዋይታና እሪታችንን ሰምቶ "ደረስኩላችሁ!" ያለን ግን ማንም አልነበረም። ይልቁንም "ደረስኩባችሁ" ተብለን ተወንጅለናል። ይህን ደግሞ "ክቡር" ጠቅላይ ሚኒስትራችን ራሳቸው ...በገዛ አንደበታቸው አረጋግጠውታል።

"...ሌሊት ሲያልሙ ያድራሉ! ...ቀን ሲዋሹ ይውላሉ። ...ይፅፋሉ! ...ይለቀልቃሉ ...ፍርድ ቤት ወስደን ቅጣታቸውን እንዲያገኙ እያደረግን ነው!" ...አዎ! ...በአፋቸው ሙ...ሉ! ...እንዲህ ብለው ብለውናል።

ዛሬስ? ...ዛሬ "ህልማችን" እውን ሆነ። ከፉ "አልመን" ከፉ በመድረሱ እናዝናለን! ..."ህልማችን" እውን እንጂ ቅዠት ሆኖ አለመቅረቱ ደግሞ አይፀፀተንም! ...መለስም ሆኑ ቢጤዎቻቸው፣ ሹሞቻቸውም ይሁን አጋፋሪዎቻቸው ...ዛሬ የሚነግሩን ምንም አዲስ ነገር አይኖራቸውም።

ዛሬ እነርሱ እየተናገሩት ያሉት ...የኛውን የትናንቱን "ህልማችንን" ነው። ..."ጨኸቴን ቀሙኝ" ነው የሚባል!? ...ጉበዝ! ህልማችንን ቀሙን እኮ!

አዎን! ... ትናንት የሻዕቢያን "ፀአዳ"ነት እያወደሱ ሲሰብኩ የነበሩ ኢህአዴጋውያን ዛሬ "ፀለምት"ነቱን እየኮነኑ ይደሰኩራሉ። – ግን አይሰማም። – ለእኛ አዲስ አይደለማ!

"ፈፅሞ! ...ፈፅሞ! ...በጭራሽ! ...ሻዕቢያ እኛን ይወረናል ብለን አስበን አናውቅም። ...እንኳንስ ልናስበው አልመነውም አናውቅ..." ነበር ያሉት መለስ ዜናዊ?

መለስ ለመሆኑ ህልምስ አይተው ያውቃሉ? "የፃድቃን መንፈስ ያረፈባቸው ያልማሉ!... ሌሎች ግን ይቃዣሉ!" ያለው ማን ነበር?

የሻዕቢያን ወራሪነት ...እብሪትና ተስፋፊነት ...ዝርፊያና አልጠግብ ባይነት ...መለስ እንኳንስ በውናቸው ሊያስቡት ...ተኝተውም ሊያልሙት አልታደሉም። ...ስለዚህም እኛ በ"ህልማችን" ባንኮራበትም አናፍርበትም።

መለስ እስከትናንት ግንቦት ድረስ ለማለም ያልታደሉትን ህልም እኛ ስድስት ዓመት ቀድመን በማለማችን! ...ብንኮራበትስ? ...ምን ነውር አለው?

እርግጥ ነው!..."ህልማችን" ጦስ ሆኖብናል። ለእሥራት፣ ግርፋት ...ለስደትና ሞት ዳርጉናል። ...ቢሆንም ግን እንፅናናለን! ...ቢያንስ ለገነት በር ቅርቡ እኛ ነንና!

"የፃድቃን መንፈስ ያረፈባቸው ያልማሉ! …ሌሎች ግን ይቃዣሉ!" ያለውን ሰውዬ አወቃችሁት? …

የማይሰማው ድምፅና ጩኸት በርክቷል። ድምፁ – አያሌ! …ጩኸቱ – የት የለሌ ደርሷል። – ግን የቱም አይሰማ!

የኢህአዴጋውያኑ ድምፅና ጩኸት ብቻ አይደለም የማይሰማ! …ሌሎችም የማይሰሙ ውንጀላና ሸንገላዎች አሉ። …የማይሰማን የ"እርጉ ዝንቧ" አሜሪካ "የችሎት ውሳኔ"ም ነው።

የኤርትራ መንግስት በብዙ ሺህ በሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ የግፍ በትሩን አሳርፏል። ብዙዎችን ለሞት ዳርጓል። …ዛሬ በመዲናችን የሚንከላወሱት የጉዳና ተዳዳሪ ወገኖቻችን የሻዕቢያ የግፍ እርምጃ አሻራ ናቸው። …ኃብትና ንብረታቸውን ተዘርፈው …ቅርስና ቅሪታቸውን ተነጥቀው …ሌላው ቀርቶ የወርቅ ጥርሳቸው ሳይቀር በጉጠት እየተነቀለ …መለመላቸውን ከኤርትራ የተባረሩ ኢትዮጵያውያን ዛሬም እንባቸው አልነጠፈም። …ዛሬም ቁስላቸው አልጠገገም …ዛሬም ከሀመማቸው አልዳኑም። ከሞቱት በላይ ካሉት በታች ሆነው የስቃይ ኑሮ ይኖራሉ። …የመከራ ህይወት ይገፋሉ። …ማን አስታወሳቸው!? …ማን ደረሰላቸው!? ከቶስ ማን ተቆረቆረላቸው!? …ማንስ ተሟገተላቸው!!?

ሻዕቢያውያኑ …ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ለስቃይና ለመከራ ዳርገዋቸዋል። አበሳ አሳይተዋቸዋል። …አሳርና ፍዳን አስቆጥረዋቸዋል። ይህ የሆነው ዛሬ አይደለም። …ከኤርትራውያኑ "ናፅነት" ዋዜማ አንስቶ የሆነና እየሆነም ያለ አረመኔያዊ ተግባር ነው።

ይህን መሰሉን ጭካኔ የተመላበት አሰቃቂ ድርጊት አሜሪካ ልታወግዘው ቀርቶ የታዘበችውም አልመሰለች። …ግን ዛሬ በክብርና በማዕረግ ከኢትዮጵያ ለተሸኙት ኤርትራውያን "ሰብዓዊ መብት" እየተሟገተች ነው። ከቶውንም "የፍርድ ውሳኔዋን" አስተጋብታለች።

"የተባረሩት ኤርትራውያን ወደ ቀድሞ ቦታቸው እንዲመለሱ! …የሞራል ካሳም እንዲከፈላቸው!…" – አሜሪካ

ደግነቱ – አለመሰማቱ!!

የማይሰማን የ"እርጉ ዝንቧ" የአሜሪካ "የፍርድ ውሳኔ" ብቻ አይደለም። ሌላም የማይሰማን "እሪታ" አለ። …ከኢትዮጵያ የተባረሩት ኤርትራውያን! …የእነርሱም "እሮሮ" አይሰማንም። …ከቶውንም አይበርደንም አይሞቀንምም።

"ያፈራነውን ሃብት ሳንይዝ ተባረርን!"

አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

የቀማቸው – የሰጣቸው። – …እኛ ምን ቤት ነን!? "አቤቱታው" እንኳንስ ሊያሳዝነን ከንፈርም አያስመጥጠንም!

የትናንት ተድላና ፍስሐቸው …ጓይላና ፈንጠዝያቸው ተካፋይ አልነበርንም። …ትናንት ከኢህአደግ ጋር "እ…ፍ!" ያለ ፍቅር አክንፏቸው ሞቤ ሲረግጡና ዳንኪራ ሲመቱ …እኛንም ጭምር አድመው አልነበረም። …አግልለው እንጂ! …ይብስኑ አርቀው አሽቀንጥረውናል።

ደግነቱ፦ እኛም አልጉመጀን! …ቀድሞ ነገር ፍቅራቸውም አልማረከን! …እናም ኃብቻውን ፈቅደን ዳስ አልጣልንም! …ከመማና ውስኪው አልተቋደስንም። …በሙዚቃቸው አልደነስንም። "ስቴ ሰምሐር" አልነሰነስንም። …"ርሑስ ጋማ" ብለን አላሞቅንም። …"የአብርሐም የሣራ" ብለን አልመረቅንም።

ታዲያ ዛሬ! …ያ! ሲላላሱበት፣ ሲጉራረሱበት …ሲያንቋልጡበትና ሲኳሸሙበት የነበረ የማጉላ ታዛ ቢፈርስ … እኛ ምን ቤት ነን!? …ይሁን ብለን ፈቅደናል? …አፈራርመን አጋብተናል? …ወይስ አዳድረናል!? …የጋብቻ ውል ቢሰረዝ እኛን አይመለከተንም። ሰነዱ ቢቀደድ እኛን አያገባንም። …ቀለበቱ ቢወልቅ ጭራሽ አይታየንም። …"ስሞታና ሮሮው" ቢያይል ከቶ አይሰማንም።

አ .. ይ ., ሰ .. ማ .. ም!!

"…አማራው ክፍል! በጣም እያለቀሰና እያዘነ ነው የሸኘን! …አማራዎች በጣም በጣም ጥሩዎች ናቸው! …" – ከተባረሩት ኤርትራውያ አንዱ።

ድ … ምፅ! … አይሰማም!!

ለመሆኑ! …ትናንት ከትናንት በስቲያ እንዲያ ሲያጣጥሉና ሲያብጠለጥሉት …ሲረግሙና ሲኮንኑት ኖረው ዛሬ እንደምን ይመርቁታል?… እንደምንስ ያመሰግኑታል? …እውን ማመስገናቸው? ወይስ እንጀት መብላታቸው? …ከሆድ መዘፍዘፋቸው?

አብነቱ – አለመሰማቱ!!

የማይሰማን ይሔም ብቻ አይደለም። …የማይሰማን "አዛኝ ቅቤ አንጓቹ" የሻዕቢያ ተራ ሸንገላና ወራዳ ድለላም ጭምር ነው።

"በኢትዮጵያ የአንድ ጉሳ የበላይነት ነግሷል። ምክር ቤቱ ላንቲካ ነው። …አገሪቱን የሚያሾሩት የህወሐት ሰዎች ብቻ ናቸው!" – ሻዕቢያ

ኡኡቴ! … ኧረ አይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

እንዴት ያለ ምስጢር ነግረውናል ጃል? …

"ትግላችን ኦሮሞን ለሥልጣን ለማብቃት …አማራን ነፃ ለማውጣት ነው!" – ሻዕቢያ

ቂ!ቂ!ቂ!ቂ!ቂቂ!ቂ! …"ጥርሴን አታስቂው!" አለ አሉ ሰውዬው!

…እባካችሁ ድምፅ! … አ .. ይ .. ሰ .. ማ .. ም!!

አለመስማታችን በጀ! … ባለመስማታችን ደግሞ አንጉዳም። … የምናጣውም ነገር አይኖርም። ቢቀርብን አንድ ነገር ብቻ ነው። – በዓል …"የአማራው የነፃነት ቀን" እየተባለ በየዓመቱ የሚከበር …ድ…ብ…ል…ቅ…ል…ቅ! ያለ በዓል!

"እኛ ፀባችን ከኢህአዴግ እንጂ ከኢትዮጵያ ህዝብ ጋር አይደለም" – ሻዕቢያ

ም–ን!!!?? … አይ – ሰማም!!

ግን ግን ...ይሄን ሰምተነው ቢሆንስ ኖሮ? ..."አሃ! በክላስተር ቦምብ የነደዱት ህፃናት ተማሪዎች ...ለካስ የኢህአዴግ አባላት ነበሩ" ብለን ልንገረም?

መታደላችን – አለመስማታችን!!

"...ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ! ...በተለይም ደግሞ ለትግራይ ህዝብ – አዲሱ ዓመት የሰላምና የብልፅግና እንዲሆንላቸው እመኛለሁ!!። – ኢሳይያስ አፈወርቂ – መስከረም 1991ም–ን!? ...ምናልክ አ–ተ!? – አይሰማም!

እናንተ!? ...ለካስ አንዳንዴም አለመስማትን የመሰለ ጥሩ ነገር የለምና!? ...አሁን ይሄን ሰምተነው ቢሆንስ ኖሮ? ..."እስኪ ማል!?" ብለን የእጃችንን መዳፍ ለኢሳይያስ አንዘረጋም?

መድህንነቱ – አለመሰማቱ!!

ኢህአዴግና አጋፋሪዎቹ! ...ሻዕቢያና አጫፋሪዎቹ! ...ብዙ! ...ብዙ ...በጣም ብዙ እያሉ ነው። እያወሩ፣ እየተናገሩና እየደሰኮሩ! ...ግን የማንኛቸውም ምናምኒት ቃል አትሰማም!!

ፍቱንነቱ – አለመሰማቱ!!

ብንሰማቸው? ... እኛ ስለነርሱ ባፈርንላቸው!
ብንሰማቸው? ... እኛ ለነርሱ ባዘንላቸው!
ብንሰማቸው? ... እኛ በነርሱ ባፌዝንባቸው!

ቅዱስነቱ – አለመሰማቱ!!

ከዚህ ሁሉ – ምናለ ዝም ቢሉ!? ...በተለይ ኢህዴጋውያኑ! ...ዝ–ም ቢሉ ምንኛ ባደነቅናቸው በነበር? ...እኛን በጦርነቱ ለማሳተፍ ፈልገው ከሆነ ብዙም አይድከሙ።

ጦርነቱ! ...ከማንም በላይ የእኛ ጦርነት ነው። – ከእነርሱም በላይ እንኳን! ...የእኛ ጦርነት ነው። ጦርነቱን የእኛ ጦርነት እንዲሆን ያደረገው ግን የኢህአዴጋውያኑ ልፈፋና ውትወታ ...ዲስኩርና ሐተታ አይደለም።

ዛሬ! ...የማናቸውም ድምፅ አይሰማንም። የማናቸውም ምስል አይታየንም። ...የማናቸውም ፅሁፍ አይነበበንም። – ሁሉንም ትናንት ሰምተናቸዋል ... አይተናቸዋል ... አንብበናቸዋል።

ዛሬ! ... መላው ኢትዮጵያዊ ባንድ ቃል! ... ባንድ ድምፅ እየተናገረ ነው። – ባንድ ስሜት ነቅቷል። ተነስቷል። ገሚሱ በማቴሪያል ዕገዛና በሞራል ድጋፍ ደጀንነቱን እያሳየ ነው። አርነቱን እያስመሰከረ ይገኛል።

ገሚሱ ባድመ ገብቷል! ...ሌላው ሽራሮ ዘምቷል ...ደሞ ሌላው ቡሬ መሽጓል! ... ይሔ ሁሉ ግን የመለስ ንግግር ቀስቅሶት አይደለም። ...የአባይ ፀሐዬ ትንተና አነሳስቶት አይደለም የእፎይታ፣ ሪፖርተር ...የሬዲዮና የቲቪው ሽለላና ቀረርቶ ነሽጦት አይደለም። – ይሔ ጩኸት ብቻ ሆኗል። – የማይሰማ ጩኸት።

ዛሬ! ...በእያንዳንዳችን ልብና አእምሮ ውስጥ የተጫረውን ስሜት የፈጠረው የእነ ዶ/ር አብዱል መጅድና ብሩክ ኃይሌ ገለፃና ማብራሪያ አይደለም።

የአቶ ተቀዳ አለሙ የካበተ "ዲፕሎማቲክ ልምድ"ም ሊሆን አይችልም። ...የኢህአዴግ ባለሥልጣናት ንግግርና ቅስቀሳ ...የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች ስሞታና አቤቱታ ...የማጩት ካድሬዎች ዲስኩርና ልፈፋ ...የእነዚህ ሁሉ ጩኸትና ልፍለፋ ከቶም አልተሰማን! ...የአንዳቸውም እንኳ አይሰማም!

ግን! ...ግን! ...ግን! ግ–ን! ...አንድ የሚሰማን ነገር አለ። – ያም ነው አንድ ያደረገን! ... የመሬታችን መደፈር! ...የህዝባችን መገፍተርና መሸቀንጠር! ...በተለይ ደግሞ በክላስተር ቦንብ የነደዱትና የጋዩት ቡቃያዎቻችን የጣዕር ድምፅ! ...እሪታና ዋይታ! ...የተበጣጠሰው ስጋቸው ...የፈሰሰው ደማቸው!... ይሄ ነው የሚሰማን! ...ይሔም ነው ለፍልሚያው የጠራን! ...

በወገናችን ላይ የተፈፀመው የግፍ እልቂት! ...ይሰማናል! ...ቆዳችንን ሰርስሮ ...ስጋችንን ቦርቡሮ ...አጥንታችንን ድረስ ዘልቆ ይሰማናል። ...አዎን! ...ይሔ ነው የተሰማን! ...ይሔም ነው ያሰማን! ...

## ነፍሰ – ሥልጣን

(ከአትናትዮስ — አ.አ.)

ከነፍስ ቀጥሎ በምድር ላይ የሚያሳሳው ነገር ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? የእርስዎን አላውቅም። በዚህች ከአፍንጫዬ ስር ባልራቀች ግምቴ ግን ሥልጣን የነፍስ ያህል ትጥማለች ባይ ነኝ። ይኼን በየቦታው የሞላውን መገዳደል ስናይና ስንሰማማ "ሥልጣን ነፍስ ናት" ብቻ ሳይሆን "ነፍስም ስልጣን" ናት ያሰኛል።

ባለፉት ብዙ ዓመታት ውስጥ በሥልጣን ሰበብ ስንት የሰው ነፍስ እንደጠፋ በአሁኑ ሰዓት ቆጥሮ ማወቅ ይቻላል? ይህችን ዘለላ አንቀፅ አንብበን እስከምንጨርስ እንኳ ስንቱ ነፍስ ለሥልጣን ጭዳ እንደሚሆን ለማሰብ ጊዜ ካለን አብረን እናስብ።

የመንበረ ሥልጣን አምሮት ጭካኔና ግፍን በራስ ወገን ላይ በመፈጸም መደሰትን ያለምዳል። በራዕይ ተወጥኖ በተስፋ ጉልብቶና አድጉ ለሥልጣን አፍቃርያን የሚታያቸው "የበለፀገ" ህዝብ በገሀዱ ዓለም በተቃራኒው ሆኖ ሲያገኙት፤ ያ ህልማቸውና ምኞታቸው ቅዠት ብቻ እንደሆነ ሲረዱት ከራሳቸው ጋር ይጋጫሉ። "ነፍሰ–ሥልጣንም" አብራ ትደነግጣለች።

ብልጣ ብልጦቹ የሥልጣን ጥመኞች ከሚገኙበት ህብረተሰብ ውስጥ ከሚኖሩ ከማንኛውም ግለሰቦች ሁሉ ራሳቸውን የተለዩ አድርገው የመቁጠር ተቀጥላ ሱስ ያጠቃቸዋል። መንበሩ ላይ ዙፋኑ ላይ ሳሉ ከምንም ከማንም በላይ ለአገር አሳቢ፣ ለህዝብ ተቆርቋሪ እነርሱው ብቻ እንጂ ሌላ ሊሆን እንደማይችል ያስባሉ። በዚህ ደካማ አሳቤያቸው ሳቢያ ብዙውን ጊዜ "ከእኔ በላይ" በሚል ግትርና ጭፍን አመለካከታቸው በአካባቢያቸው በህዝብና በአገር ላይ ከዚያም ዘሎ ድንበር አለፍ በሆኑ ህዝቦችና መንግስታት ህልውና ላይ ውካታ ቀውስና ችግር ይፈጥራሉ። በእነርሱ ጦስ አገር ይደማል፣ ህዝብ ይሳቀቃል፣ ህብረተሰብ ይጨፈለቃል። ሰላም ይደፈርሳል፣ ስምምነት ይጠፋል። በምትኩ ጦርነት፣ ሽብር፣ ረሃብና እልቂት ይነሳል። ባልተፈጠሩበት የፖለቲካ ችሎታና ልምድ ሳቢያ ህዝብ በከፍተኛ ፍጥነት የጓሊት ይራመዳል። ሀገርም እንደዚያው። ከሥልጣን አምሮት ብቻ፣ ከመንበረ ዙፋን ጉጉት ብቻ ሌላ በማያስበው አዕምሮአቸው በሚሰጡት ፍርድ ህዝብን እርስ በርሱ ያናቁራሉ፣ ኃይማኖትን ከኃይማኖት፣ ብሄርን ከብሄር እርስ በርሱ ያጋጫሉ፣ ያፋጫሉ። በየትኛውም መልኩ ቢሆን ሊኖር የሚችለውን የህዝቦችን ታሪካዊ ትስስርና ቁርኝት በደካማው የግል አዕምሮአቸው ለያይተው በትርምስና በግርግር ሥልጣነ ዘመናቸውን

ለማራዘም ይፍጨረጨራሉ።


ከነገስታት ጊዜ ጀምረን አሁን እስከደረስንበት ጊዜ ድረስ ያሉትን የኢትዮጵያ መሪዎች ብንመለከት ይነስም ይብዛም ሁሉም ስልጣናቸውን ለማቆየት ሲሉ የተጋፈያቸውን ነፍስ አጥፍተዋል። – ነገሥታቱ እርስ በርስ እኔ እነግስ እኔ እነግስ ሲሉ ጦርነት አድርገው ነስፍ ጠፍቷል፤ ወደዚህ ቀረብ ብለንስንመጣም በአፄ ኃይለ ስላሴ ጊዜ እነ መንግስቱ ነዋይ፤ ... ለዚህችው ለስልጣን ሽሚያ ሞተዋል፤ በደርግ ዘመን በቀይ ሽብር ያለቀውን ምሁርና ወጣት እንኳ ትተን ለስልጣን ሽሚያ ከአማን አንዶም ጀምሮ ስንቶቹ ሞተዋል፤ አሁንም በወያኔ ዘመን ይኸው በየጊዜው በምናየውና በምንሰማው ሁኔታ የሰው ነፍስ ለምን ስልጣኔን ትጋፋለህ በሚል ስሜትና ፍራቻ ጠፍቷል።

ነፍስ ለሥልጣን ግብር የመሆኗንም ያህል፤ ስንቱ ነፍስ በሥልጣን ለምልሟል መሰላችሁ? ምን ሩቅ አስኬደን? የዛሬ ሰባት ዓመት በጉጠት ተፈልጉ የማይያዘው የጌቶቻችን ጉንሞ ዛሬ ልትወልድ የደረሰች ባዝራ ጡት አክሎ እናየው የለ? ሥልጣን ያለመለማት ነፍስ እርሷ ናት። የዛሬ ሰባት ዓመት ወርቁና ደረቱ እኩል የሚያብለጨልጨው ዜጋ ዛሬ መንፈቀ ዓመት ደለል የተኛበት ተክል መስሎ በየጉዳናው ዳር ምፅዋት ሲጠይቅ እናየው የለ? ያ ደግሞ ሥልጣን ያወየበው ነፍስ አስረጂ ነው። ሥልጣን የቀጠፈውን ነፍስ መቃብር ይቁጠረው። ነፍስ ትፈራለች። ሥልጣንም እንዲሁ ፈሪ ናት። የሥልጣን ፍርሃት ከነፍስ ፍርሃት ባይብስ ነው?

ዛሬ እዚህም፣ እዚያም አንድ ወሬ አለ። የጦርነት ወሬ። "ለምን አንዋጋም?" የሚል ወሬ። አሁን፣ አሁን እዚህም እዚያም አንድ መልስ አለ። "ፍርሃት።"

"ማነው ማንን የፈራው?" ቢባል፤ ያለ ጥርጥር "ወያኔ ሻዕቢያን ፈርቶታል" ነው መልሱ። ፈሪዋ የመለስ፣ የነጋሶ፣ የስዩም፣ የፃድቃን፣ የሳሞራ ... ግለነፍስ አይደለችም። "እርሷማ አስራ ምናምን ዓመት ማካ ለማካ፣ በረሃ ለበረሃ ፍዳ ስትቆጥር ኖራ አይደል የማታ ማታ ወራሽ ምድረገነት የሆነችው?" ፈሪዋስ ሌላ ናት፤ የሥልጣን ነፍስ። የሥልጣን ነፍስ ፍቅር ናት። ትጥማለች። ታባንናለች። መልዐከ ሞት በየት በኩል መጥቶ መደበኛዋን ነፍስ እንደሚነጥቃት እንደማይታወቅ ሁሉ የሥልጣን ነፍስ ቀበኛም ከየት እንደሚነሳ፤ በየት በኩል እንደሚመጣ አይታወቅም። እናም ያባንናል። ያስፈራል። የነፍስ ሥልጣን ፍርሃት ገና ብዙ ያሳየናል። እስካሁን ባየነው ብዙም ባንደነቅ ነው ጥሩ። ■


## በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ አንባብያን ባላት ላንዳፍታ መጽሔት ላይ ድርጅትዎን ያስተዋውቁ!



# A to Z

## ELECTRONICS & GIFTS

TV. - VCR. - Cameras - Phones - Stereos - Fax Machines


Watches - Luggage - Toys -Gift Items - Perfumes

## ኤ ቱ ዚ ኤሌክትሮኒክስ

ከፓል ሴካም ወደ ኤን ቲሲና ከኤን ቲሲ ወደ ል ሴካም ቪዲዎ መገልበጥ
ኢትዮጵያ መሥራት የሚችሉ ባለ 220 ቮልት የኤሌክትሪክ ዕቃዎች
በርካሽ ዋጋ



1713 Church St. Suit A-1
Decatur, GA 30033
(Kroger Shopping Center)
Jayendra Patel & Dipa Patel
Tel/Fax: (404)299-9196



*Hours:*
*Tuesday to Sunday*
*11:00 am - 8:00 pm*
*Monday Closed*

# ኢትዮጵያና ችግሮቿ

(ከአልታዬ ወርቅነህ)

በመጀመሪያ ስለሀገራችን ችግር የሚያወሳ ርዕስ በመምረጤ ለራሴም ቅር የሚያሰኘኝ ቢሆንም እንኳ የማንክደውና አሌ የማንለው ልንሸሽገው የማንችለው በገሀድ የሚታይ የሀገራችን እውነታ ነውና ምንም ማድረግ አይቻልም። ወደ ርዕሴ ልመለስና ኢትዮጵያችን በአሁኑ ጊዜ በምን አይነት ሁኔታ ላይ ነው ያለችው? ለዚህ አጠቃላይ የሆነ መልስ ለመስጠት ሁሉም የሚሳነው አይሆንም – ችግር የመሰለውን በራሱ አስተያየትና ግምት ማንኛውም ሰው ሊናገር ይችላልና – እኔም ለዛሬ ሁሉንም ላነሳ ባልችል እንኳ ዋና ዋና የምላቸውን ላቀርብ እሞክራለሁ።

ከጤናው በኩል ስላለው ችግር ብነሳ፤ ኢትዮጵያ ወይም ህዝቧ ዛሬ ለተለያዩ ወቅታዊና ዘላቂ በሆኑ የተለያዩ በሽታዎች የተወረረች ናት። ታዲያ ለእነዚህ በሽታዎች ያለው መንግስት ይህን ያህል ሰው በዚህ ቦታ አለቀ ወይም ይህን ያህል ሰው ወደፊት በዚህ በሽታ ይቀሰፋል የሚል የ10 ዓመት እቅድ መግለጫዎችን ከማስተላለፍ በስተቀር መፍትሄው ይሄ ነውና ይህን አድርጉ ሲል አይሰማም ወይም አይታይም። ለምሳሌ በአገራችን በአሁኑ ጊዜ ተስፋፍቶ የሚገኘውን የወባ በሽታ ብንመለከት በጣም በሚያስገርምና ተሰምቶ በማይታወቅ ሁኔታ በተለያዩ ክፍለሀገራት በርካታ ሰዎች በዚሁ በሽታ በየቀኑ ሲረግፉ ይታያል። የወባ በሽታን በእኛ አቅም ከነጭራሹ ለማጥፋት የሚቻል ባይሆንም የአደጋውን መጠን ግን ለመቀነስ የሚቻልባቸው የተለያዩ ዘዴዎች አሉ። – በአካባቢው መድኃኒት መርጨት፣ ቆሻሻዎችና በተለይም ውሃ ያቆሩ ቦታዎችን ማፅዳት፣ ክትባት ወይም መከላከያ መድኃኒት አስቀድሞ መስጠት የመሳሰሉት ናቸው። ነገር ግን የሚመለከተው ክፍል ይህን በማድረግ ፋንታ ልክ ሰው ሁሉ በወባ በሽታ መለከፍ እንዳለበት ወይም መሞት እንዳለበት ወይም እንደማንኛውም ጉንፋን በሽታ አቅልሎ በማየት ትኩረት ሳይሰጠው ቀርቷል። አሁንማ ጭራሽኑ የወባ በሽታ እንደዚህ ጉልቶ የታየው ኤሊኒኖ በአለማችን ባመጣው የአየር ማዛባት ምክንያት ነው የሚል ብሂልም አምጥተዋል። (ይህን ነገር ለስንቱ ነገር እንደምክንያትነት እንደሚጠቀሙበት ባይገባኝም) የሚደንቀኝ ነው ለእኔ። ወባ ወቅታዊ በሽታ እንደመሆኑ መጠን የሚከሰትበት ወቅት እስከታወቀ ድረስ በቅድሚያ አስፈላጊ የሆኑ ቅድመ ዝግጅቶችን ወይም መከላከያዎችን ማድረግ ሲቻል ወይም ሲገባ ምን የመሳሰለ አምራች ዜጋ እንደቀላል ነገር በጥድፊያ ለሞት ሲዳረግ ሲታይ አገራችን ወይም ደረጃችን ምን ያህል ዝቅ ያለ እንደሆነ መገመት ይቻላል። እኔ ሰው በሌላ በሽታ ታሞ ቢሞት ላይገርመኝ ይችላል። ምክንያቱም በሽታው ለበሽተኛው ጊዜ ሰጥቶት መድኃኒት ተሞክሮለት (መድኃኒቱም ሲገኝ እኮ ነው እንዳትሉኝ እንጂ) አቅቶት ተዳክሞ ከሞተ አልቻለም ብዬ ላምን እችላለሁ። እንዴት ይወዳደራል አትበሉኝና ኤድስ እንኳ ጊዜ የሚሰጥ በሽታ ነው። ይሄ ግን ዛሬ ከያዘ ዕለቱን አንቀጥቅጦና አንዘፍዝፎ ለግብዓተ መሬት ማብቃት ብቻ ነው።

ለዚህ በሽታ መስፋፋት ዋናው ምክንያት በ1986 ዓ.ም. የወያኔ መንግስት የመዋቅር ለውጥ ሲያደርግ የወባ መከላከያ መስሪያ ቤትን የማያስፈልግ ነው ብሎ ሠራተኛውን በትና መስሪያ ቤቱን በመዝጋቱ ነው። በዚህም ወደመቆጣጠር ተደርሶ የነበረው የወባ በሽታ እያገረሸበትና እየባሰበት መጥቶ ይኸው አሁን አዲስ አበባንም እንደጨመረ በጤና ጥበቃ ምክትል ሚኒስትር በቅርቡ ተገልጿል። ግን አሁንም ምንም የተደረገ ነገር የለም።

በጤናው ረገድ ከጠቀስኩት ወባ፣ ከተስቦና ከሌሎች ቬክተር ወለድ ተዛማጅ በሽታዎች በተጨማሪ የዓለማችን በሽታም ቢሆን ከ15 ዓመት ወዲህ ግን በአገራችን ድምፁ መሰማት የጀመረው የኤድስ በሽታ ወረርሽኝ አድማሱን እያሰፋ መጥቶ በፍጥነትም ሆነ በአሀዝ ጉልቶ እየታየ ነው። – "ዴሞክራሲው" የፈጠረው እንዝላልነት ባህላችንን ሸርሽሮ ወጋችንን አድምቶና አኩሪ የነበረውን የኢትዮጵያን ባህልና ስርአት አጥፍቶ ልቅነትና ጋጠወጥነትን በማስፋፋቱ – እነዚህ የሚፈጥሯቸው የመከራ አንጓዎች የዝሙት ቤቶች መስፋፋት፣ አደገኛ የወሲብ ፊልም ትርኢቶች መበራከት ... የተነሳ በሽታው በፍጥነት ተዛምቶ የሃገር ተረካቢ ዜጋ አልባ ሊያደርገን ሩጫውን ቀጥሏል። ኤድስ ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ትንሽ፣ አዋቂ፣ ህፃን ሳይል የሁሉንም ዕድሜ ክልል ሆነ ፆታ እየጐበኘ ነው። በአገራችን ትልቁን አሀዝ የያዘው ወጣቱ ክፍል ቢሆንም እንኳ ስንት ዘመናት አብረው የኖሩና ለአገሪቱ ጥሩ ዜጐችን ያፈሩ እናቶችና አባቶች በዚሁ ቀሳፊ በሽታ እየተጠራሩ እየተከታተሉ ሲሄዱ እያየን ነው። የእነሱ ልጆችም ከህብረተሰቡም ሆነ ከዘመድ አዝማድ በሀፍረት ተገልለውና ዘመድ አልባ ሆነው የነገ ዕጣቸውን እየጠበቁ ይገኛሉ።

በእርግጥ ኤድስ የሚተላለፍባቸው መንገዶች የተለያዩ ናቸውና በኤድስ የተለከፈ ሰው ሁሉ ከዝሙት ጋር ማያያዙ በጣም ይከብዳል። ነግ በእኔም ነውና። ለምሳሌ አንድ አዛውንት በሌላ በሽታ ይታመሙና በጣም ይዳከማሉ (ይመናመናሉ)፤ ልጆቻቸው በሚያዩት ሁኔታ ይጠራጠሩና ደማቸውን ሲያስመረምሩ ሰውየው ለኤድስ ፖሰቲቭ ይሆናሉ። ቤተሰቡ በጣም ይደናገጥና ከአባትየው ደብቀው እናትየውን ሲያስመረምሩ ሴትየዋ ነፃ ይሆናሉ። ከዛ ልጆቹ ይነጋገሩና አባትየውን ይህ እንዴት ሊሆን ቻለ? ብለው ቤተሰባዊ ውይይት ያደርጋሉ። አባትየው እንቧ ከረዮ ይላሉ። እኔ ከእንዲቷ ሚስቴ በስተቀር ሌላ አላውቅም። በፍፁም ይህ ነገር ይጣራልኝ ብለው ልጆቻቸውን ይማፀናሉ። (ነፃ ሆነው ለመሸኘት እንጂ ሞቱ እንደሆነ አልቀራለቸውም) ልጆቹ ከዛ ሊሆን ይችላል ብለው የገመቱቱን መላ ምት ሲያደርጉ ይቆዩና የቤት ሰራተኛቸውን ያስመረምሯታል። ከዛ እሷ ስትመረመር ፖሰቲቭ ትሆናለች። ልጅቷ ስትጠየቅ አዎን በእሳቸው የጥርስ ብሩሽ ጥርሴን አፀዳ ነበር ብላ ቃል በመስጠቷ የሰውየው በበሽታው መለከፍ ምክንያት ዝሙት እንዳልሆነ ታወቀ። ይህ እውነተኛ ታሪክ ነው። እናም ለማለት የፈለግሁት ጥቃቅኑን ነገር ሁሉ መጠንቀቅ እንዳለብን ነው። አንዱን መንገድ ብቻ ተጠንቅቆ ሌላውን ከተዉት ዋጋ የለውምና። በተለይም በአገራችን የገጠር መድኃኒት ቤቶች የሚታየው የፅዳት ሁኔታ ችግሩን የባሰ አሳሳቢና አስጊ ደረጃ ላይ አድርሶታል።

በአሁኑ ጊዜ በየሆስፒታሉ ለተለያየ ህክምና

ከሚሄደው ሰው በሚደረገው የደም ምርመራ ውጤት ከ70% በላይ የዚህ በሽታ ተጠቂ እንደሆነ መረጃዎች እያሳዩ ነው። አገራችንን የማያውቋት አገሮች ዛሬ እንደ ድርቁ ዘመን በኤድስ እያወቋት ነው። ይህ በጣም የሚያሳዝንና የሚዘገንን ኢትዮጵያዊ ለሆነ ዜጋ ሁሉ ቅስም የሚሰብር ነገር ነው። አንድ ጊዜ አንዲት ልጅ ወደ አረብ አገር ለመሄድ ሜዲካል ከወሰድነው 280 ከምንሆን ልጆች ውስጥ ነፃ ሆነን ወረቀቱን ለመውሰድ ስማችን የተለጠፈው የ18 ልጅ ብቻ እንደነበረ ስትገልፅልኝ ጆሮዬን ማመን ነው ያቃተኝ። ራሴንም እስከመጠራጠር አድርሰኛል። ታዲያ ይህ ሁሉ እየሆነ ኤድስ ቀሳፊው በሽታ እየተባለ እንደቀላል መታየቱ የሚገርም ነው።

መድኃኒቱ በውል ባይገኝ እንኳ ዋናው መከላከያ በአንድ ተወስኖ መኖር መሆኑን ሁሉም ጠንቅቆ እያወቀ ጥንቃቄ ሲያደርግ አይታይም። ከሁሉም በላይ ደግሞ ይህ በሽታ ከከተማ ወደ ገጠር በብርሃን ፍጥነት የመዛመቱ ሂደት ጉልቶ መታየት መጀመሩ ነው። ዛሬ ለአንድ ጉዳይ ወደ ከተማ ብቅ የሚል ገጠሬ የኮንዶምን ጥቅም ቀርቶ ምንነቱን የማያውቅ በመሆኑ የመጣበትን ጉዳይ በውል ሳይጨርስ ይህን ትልቁን አደጋ ተሸክሞ ወደ ምስኪኗ የገጠር ሚስቱ ያስተላልፋል። ከዛ የሚሆነውን መዘርዘሩ አስፈላጊ አይመስለኝም። እንኳን ገጠሬው ከተሜው እንኳ ስለ ኤድስ አስከፊነት ይህ ሁሉ ቅስቀሳ በየዜና አውታሩ እየተነገረ (በዚህ ጉዳይ መንግስት የሚያሳማኝ አይሆንም) እኔ ከተከላከልኩ ማን ያጥቃ፤ ከሞቱ አይቀር በኤድስ በሚል የሞኝ ፈሊጥ በየቀኑና በየሰዓቱ ራሱንና ግማሽ አካሉን እንዲሁም ፍሬውን ለዚህ በሽታ እየዳረገና በአሰቃቂ ሁኔታ እየተሸኘ ይገኛል። ስለዚህ በሽታ አስከፊነት ህዝቡን በመቀስቀስ ትልቁን ስፍራ የያዘው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ነው። (የሌላውን ባላውቅም) ዛሬ ይህች ቤተክርስቲያን ሁሉም ሰው አንድ ለአንድ መወሰን እንደሚገባው የመጽሀፍን ቅዱስን ቃል በመንተራስ ዕለት በዕለት በሚነገሩ ስብከቶች መሀል ስለ ኤድስ አስከፊነት አበክራ ታስተምራለች ታስጠነቅቃለች ትገዝታለች። ግን ማን ይስማ? ማን በምክሩ ተጠቃሚ ይሁን? ደግሞ የሚያሳዝነው በአገራችን ሰው ኤድስ ሲይዘው ኤድስ ያዘው አይባልም ቲቢ(TB) የሚል ስያሜ ሰጥተውታል። በእርግጥ ቲቢ የያዘው ሁሉ የኤድስ በሽተኛ ነው ባልልም ያ ሰው በእውነት በኤድስ በሽታ ተለክፎ ከሆነ ቤተሰብም ሆነ ዘመድ አዝማድ አስታማሚ ጥንቃቄ እንዲወስድ የበሽታውን ምንነት በቅድሚያ ማሳወቁ ጠቃሚ ነው እላለሁ። አለበለዚያ ግን ሌላውም ሰው በሆነ አጋጣሚ ሊያዝ ይችላልና አለመታወቁ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናል። በሌላ በኩል መሻሻል የሚገባው በአገራችን በሚታዩ ቲቪ ድራማዎችና የሬዲዮ ድራማዎች ላይ ሁልጊዜ ማለት እችላለሁ የዚህ በሽታ አስተላላፊ ሴት ብቻ እንደሆነች፤ ወንዱ ኮንዶም መጠቀም ስለሚችል እሷን ተጠንቀቅ እየተባለ ብቻ ይተላለፋል። ይህ በጣም የሚያዘናጋን ነገር ነው። ለዚህም ይመስለኛል በአሁኑ ጊዜ ግብረ ሰዶም በከፍተኛ ሁኔታ በከተማችን ተስፋፍቶ ይገኛል የሚባለው። ይህ መቼም ከባህላችንም ሆነ ከሁሉም አንፃር ምንኛ አስከፊ እንደሆነ አንባቢ መገመት የሚያቅተው አይመስለኝም። እናም ማንኛውም ሰው የበሽተኛውን አስከፊነት በመገንዘብ ጥንቃቄ እንዲያደርግና መንግስትም ትኩረት ሰጥቶ በየህክምናው ጣቢያም ሆነ በየትምህርት ቤቱ በየመስሪያ ቤቱም ሆነ ህዝብ በሚገኝባቸው ቦታዎች አስፈላጊው ምክርና ትምህርት እንዲሰጥ ነው።

ሌላው ደግሞ ትልቁና ዋናው በሽታችን "መንግስታችን" ነው። ይህ መንግስት በብዙ መልኩ ለኢትዮጵያ በሽታ ብቻ ሳይሆን ጥሩ አዋቂ ካልተገኘላት ነቀርሳ የሚሆንባት መንግስት ነው። የሰባት አመቱ ነቀርሳ እንዴት እንደሚድን ባላውቅም መድኃኒት መፈለግ ይኖርበታል። ከየት? ማን? የሚለውን ለአዋቂዎቹ ልተውና በችግሮቹ ላይ ላተኩር።

ከበሽታዎቹ መሀል በተለይ ንቅዘት ሙስናና ጉቦ በአሁኑ ጊዜ እንደ ተራ ጉዳይ የሚታይ ነገር ሆኗል የትም ቢሄዱ ወይም ማንም ባለስልጣን ዘንድ ለአንድ ጉዳይ ቢሄዱ ጉቦ መስጠት እንዳለብዎ ያውቃሉና የቅድሚያ ዝግጅት ያስፈልግዎታል። – ሆስፒታል ታመው ቢሄዱ ከካርድ ክፍል ጀምሮ እስከ ... ድረስ ሁሉም ገንዘብ ፈላጊ ነው። ያንንም አድርገው የተሟላ ህክምና ማግኘት አይቻልም። ህክምናውን ቢያገኙ እንኳ የታዘዘልዎትን መድኃኒት ለማግኘት ከተማውን ለማዳረስ ሳምንት ያስፈልግዎታል። በለስ ቀንቶዎት ካገኙ መልካም፤ አለበለዚያ ግን ዘመድ ፈልገው ከየአረብ አገሩም ሆነ ከየትም ማስመጣት አለብዎት። እስከዛው ድረስ የምትጠብቅ ነፍስ ካለዎት ጥሩ አለበለዚያ ግን በመድኃኒት እጦት መሞት የሌለባት ነፍስ ትጓዛለች ማለት ነው። ደግሞስ መድኃኒት ከውጭ አገር ለማስመጣት አቅም ያለው ስንቱ ኢትዮጵያዊ ነው? መንግስት ለዚህ ነገር ትኩረት ሰጥቶ በአገሪቱ ያለውን የመድኃኒት እጥረት ሊያስወግድ እንዳልቻለ ሊገባኝ አልቻለም። ነው ወይስ ህዝቡን በዚህ ሊቀጣው ፈልጉ ይሆን? ይህም ሌላው ችግርና ጥያቄ ነው።

አንድ ሰሞን እኔም እንደዚሁ በሽታ ያዘችኝና ስመላለስ አንዲት እናት አግኝቼ ያጫወቱኝ ምን መሰላችሁ– ዛሬ ምን ሀኪም አለ? ምንስ ሀኪም ቤት አለ? ሀኪም ድሮ ቀረ አሉኝ። ምነው? አልኳቸው። ያኔ ጥንት እናንተ በተወለዳችሁበት ዘመን ሀኪም ቤት ገብተን ስንወጣ ነጠላችን ሁሉ መድኃኒት መድኃኒት ስለሚሸት ባንታከም እንኳ ተሽሎን ነበር የምንወጣው። ዛሬ እንኳን ነጠላችን ሊሸት የሚዋጠውም መድኃኒት አልተገኘም ብለው ሲናደዱ ላይ ለእኔ ትንሽ አስቆኛል። የሚገርመው በየሆስፒታሉ ያለው ችግር ለህክምና ሲሄዱ ብቻ ሳይሆን የታመመ ዘመድዎን ለመጠየቅ ቢሄዱ የበር ዘቡን ለማለፍ በአካባቢው ካለ ሊስትሮ ጋር ወይም በቅርቡ ካለ አትክልት ሻጭ ጋር የቅድሚያ ውል ማድረግ አለብዎት። ይህን ካሟሉ ዘቦቹ በምን ቋንቋ እንደሚግባቡ ወይም ጉቦውን በምን እንደሚቆጣጠሩት ባይታወቅም እርስዎ ያለ ጥያቄ ሰተት ብለው ይገባሉ።

ጉቦ በተለይ ከመንግስት ስራ ጋር በእጅጉ የተያያዘ ነው። እቃ ከውጭ አምጥተው ጉምሩክ ቢይዝብዎት ቀረጥ ላለመክፈል ወይም ለማስቀነስ የተወሰነ ፐርሰንት ባለስልጣኑ ማግኘት አለበት፤ ከውጭ መጥተው አንድ ቦታ ላይ ኢንቨስት አድርገው ስራ መስራት ቢፈልጉ ፈቃዱን ወይም ቦታውን ለማግኘት የሚመለከተው ሰው ገንዘብ ይፈልጋል፤ የሚኖሩበት ቀበሌ ሄደው መታወቂያ ማውጣት ቢፈልጉ ጊዜው ከፍቷልና በእጅ ካላልከ አይሆንልህም ይልዎታል ... ለዚህ አይን ያወጣ ጥያቄ እርስዎ ህጋዊ አለመሆኖን አውቀው ገንዘቡን ለመስጠት ይፈሩ ይሆናል እንጂ እነሱ እንደመብታቸው ቆጥረው በግላጭ ነው የሚቀበሉት። በየጊዜው ስለዚህ ጉዳይ ብዙ ቢባልም ከላይ እስከ ታች ያሉት ሰዎችም በጉዳዩ ስላሉበት አቤቱታውም ሆነ ትችቱ ውጤት የለውም።

አንባብያን! እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ነገሮች

ይመስለኛል በመኖር ተስፋና ሰላም ማግኘት ያለመቻላችን ምክንያት የሆኑት። እኔ የማያቸው ብዙ ብዙ ... እጅግ በርካታ ፊቶች የተረበሹ ናቸው፣ አይኖችም ተጠራጣሪና ቀጣፊ አቄበርባሪና ዋሾዎችም ናቸው። እኔ ራሴ በጠዋት ገና ስነሳ የገዛ ፊቴን በመስታወት ስመለከት ከአይኔ ውስጥ ... ከገፅታዬ ላይ የሆነ የሀዘን ድባብ አዕልቶበት አያለሁ፤ ዞር ብዬ ወደ ምስራቅም ስመለከት እየወጣች ያለችው የንጋት ጮራ በውጋጋኗ ውስጥ የዚህችን አለም ሁከትና ረብሻ ... ችግርና ሰቆቃ ዝሙትና ርከሰት ሁላ ታመላክተኝና ጾም በአደረ አንጀቴና በልቤ ውስጥ ሽብርና ፍርሃትን ትለቅብኛለች፣ እናም ውሉዬ ሁሉ ሰላመ ቢስ ሆኖ ፊቴም ሰላም አልባ ሆኖ ይውላል። ብዙ ጥርሶች ይስቃሉ፣ ፊቶች ግን የሚገልፁት ሀዘንና ጽልመትን ተስፋ ቢስነትንና የኑሮ ምሬትን ነው። ነፍሳችን ሀሴት ማድረግ ካልቻለችና ሰላሟን ካጣች ምንም ብንቀባባና ብንኳኳል ፍፁም የተሟላ ውበት ከእኛ ላይ አለ ለማለት አያስደፍርም። የትም ቦታ ስንሆን እስቲ ራሳችንን በሌላው ገፅታ ውስጥ ለማስተዋል እንሞክር የምናያቸው ፊቶች የተረበሹ ናቸው የእውነተኛው ዘመን ተምሳሌት።

ትኩረት

ግን፣ ይሄ ሁሉ ችግር በአገሪቱና በህብረተሰቡ ላይ ሰፍኖ እያለ የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች በየሪፖርታቸው ለአገሪቱ ዕድገት በሰራሁት ስራ እርካታ ይሰማኛል እያሉ በአደባባይ ሲናገሩ ስሰማ አንጀቴ ብጥስ ይላል። እስቲ የትኛው መልካም ስራ ነው የሚያረካቸው? መንገዶች ተቆፋፍረዋል፣ በቧንቧ የሚመጣው ውኃ አንዳንዴ የጉርፍ ውሃ መስሎ ይወርዳል፣ በየከተማው የላስቲክ ቤቶች እንደ አሸን ፈልተው የቱሪስቶች ማላገጫ ሆነናል፣ መኖሪያ ቤቶች ከመፈራረሳቸው የተነሳ ተቃቅፈውና ተደጋግፈው ይታያሉ። በጤናውም ሁኔታ በየዘርፉ እንዲህ በዓለም ደረጃ እየተጠራንበት ነው። በኢኮኖሚውም ወድቀናል አገራችን ውስጥ ሰላም ጨርሶ የለም። ችግር፣ ችግሮች በየዘርፉ በአገራችን ላይ ተንሰራፍተው ይናኛሉ።

መሪዎች፣ የየክልሉ ፕሬዚዳንቶች ስለአገሪቱ ችግር ጆሮ ዳባ ልበስ ካሉ እኛ ለአገራችን የምንቆረቆር የምንቆጭ ዜጐች አገራችን ከእንደነዚህ አይነት ችግሮች ውስጥ ገብታ ስናይ በበኩላችን ምን ማድረግ ነው ያለብን? መፍትሔው ሁላችንም ጋ ነውና ያለው ይህን ለሁሉም አንባቢ ትቼ ለዛሬው ቸር ያድርገን ጤና እያልኩ ባበቃስ።

ለውይይት

# ለምሁርማ አርዮስም ምሁር ነበር!!

### አማረ አፈለ – ሎስአንጀለስ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን ሰቅሎ የሰራትን ቤተክርስቲያን ለማፍረስ በመጀመሪያ የተነሱት የቤተክርስቲያን መናፍቃን በአራት ሲከፈሉ፤ የእነዚህ ትምህርት ውሉ አድሮ ሌላውን አስቸጋሪ አቅሙ ትልቅና ግዙፍ ሆኖ የመጣውና የክህደት ትምህርት ያስፋፋውን ሊቀ ፈላስፋ አርዮስን ወልዷል።

አርዮስ እጅግ የተማረና የተፈላሰፈ ቢሆንም የቤተክህነቱን ዶግማ እሱ በፈለገው ትርጉም አጣሞ ማስተማር ጀመረ። አርዮስ በ318 ዓ.ም ጀምሮ እስከተወገዘበት ጊዜ ድረስ እየዞረ ቤተክርስቲያኑን በጥብጧል። አሁን በዓለም ላይ የተለያዩ ቤተክርስቲያን እንዲሆኑ የለየና ክርስቲያኖች እንዳይግባቡ ያደረገ የአርዮስ የክህደት ትምህርት ነው።

ዋናው ይህን ታሪክ እንድጠቅስ ያነሳሳኝ ነገር ቢኖር በላንዳፍታ መጽሔት በህዳር 1991 ዓ.ም "ሰላምታ ከወደ ባህር ማዶ ከገብርዬ" በሚለው አምድ በገጽ 9 ላይ "...አንድ ምሳሌ ልጥቀስልህ አሜሪካ በርካታ ሀገራቸውን የሚወዱ ምርጥ ምሁራን ዶክተሮች አሉ። በአንድ ስቴት ብቻ በማዕከላዊ ቁጥር 18 ይገኛሉ። ከነዚህ በአንዱ ስቴት አንድ ከፋፋይ ተንኮለኛ አራቱን ይገናኛል። በስደት በምትገኘው የኢትዮጵያ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ጥላቻ ስላለውና ግለሰቡም በስራው ስለተገለለ ለነዚህ ምሁራን እየደወለ የጳጳሳቱን ስም ያጠፋል" የሚለውንና ማሩ ለገሰ (አሁንስ በዛ ደሞ ወዴት ወዴት?" እንደገና ጌታቸው ኃብቴ (ኧረ እነሱ በህግ አምላክ?) የሚለውን ጽሁፍ ሳነብ ያስታወሰኝ የክህደት ትምህርት አመሰራረትና የአርዮስ አጀማመር በዚህ ምክንያት የዓለም ቤተክርስቲያን ስም መብዛት ሲሆን አሁንም በእኛ ቤተክርስቲያን ላይ ይህን ተንኮል የሚሰራው ምሁር እንደአርዮስና ተከታዮቹ እንዳይሆኑና አንዱ ምሁር ለመበተን ተንኮል ከሰራ ውሉ አድሮ ሌላውን ከመበከሉ በፊት ወደ ሰላም የሚመጣበት መንገድ እንዲፈለግ ለማለት ነው። በዚህ አጋጣሚም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በታኟ በዝቶ በተቸገረችበት ጊዜ በውጭ ደግሞ የነሱ ተቀጥላ መኖራቸውን ያወቀ ባለመኖሩ፤ ይህን ድብቅ ሥራ መኖሩን ለማጋለጥ ላንዳፍታ መጽሔት አምዷን ክፍት አድርጋ በመስጠቷ ልትመሰገን ይገባል።

ኢትዮጵያውያን መጥፎ የሰራውን ሰው ታሪክ የራሳቸው አድርገው አይፅፉም እንጂ አርዮስ ትውልዱ ልቢያ ቢሆንም ዘሩ ኢትዮጵያዊ ለመሆኑ "ቅዱስ ማርቆስ ኢትዮጵያዊ ነው የተዋህዶ አንበሳም መድኃኒያለም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው" በሚለው የአባ ተስፋ ስላሴ ሞገስ መጽሀፍ ላይ ተጠቅሷል። እንደ አርዮስ ሁሉ በቤተክርስቲያንም ያሉ ምሁራንም ሆነ በስነ መንግስት ፖለቲካ ድርጅቶች ያሉ ምሁራን ምናለ የግል ጥቅማቸውን ተወት ቢያደርጉትና የቤተክርስቲያንና የአገርን ጥቅም ለማስከበር ቢነሱ? እንዲሁም ከአንዱ ምሁር ጋር አልግባባ ሲሉ የራሳቸውን ድርጅት ለመመስረት መሄዱን ምናለ ቢተዉት?

ወደ ምሁራኖቻችን ድርጊት ልሂድና የተማሪው ማህበር ከተመሰረተ በኋላ ከጀብሃ ጋር ተመሳጥረው የኢትዮጵያን አየር ጠልፈው ሱዳን የገቡት የአርዮስ ተከታይ በታኝ ምሁራን ናቸው። ምሁራን በውጭ አገር ድርጅት ለመመስረት በ1964 ዓ.ም ጀርመን በነበረው ስብሰባ ከሁለት ይከፈላሉ። አንዱ አገር በአረብ አገር ሲሰልጥን ኑሮ በ1965 ዓ.ም. መጀመሪያ ወደ ሻዕቢያ በረሃ ገባና በኋላ የጦር አምባውን አሲንባ ይመሰርታል። ሌላው ምሁር ወደ አዲስ አበባ በቦሌ ይገባና የጦር አምባውን ቤተመንግስት ይመሰርታል። እነዚህ በታኝ የአርዮስን አርአያ የተከተሉ ምሁራን ደርግን እየመከሩ የኢትዮጵያን ህዝብ አስጨረሱ። አሲንባ የገቡትም ሆነ ቤተመንግስት የገቡት ምሁራን የተከተሉት ፍልስፍና የማያዋጣቸው ሲሆን የኢትዮጵያን ህዝብ ለደርግ አስረክበው ቀደሞ ወደተማሩበት አገር ፈረጠጡና በየከፍተኛ ትምህርት ቤት ማስተማር ጀመሩ። የራሳቸውን ኑሮ ለማደላደል ቤት መግዛት፣ ልጅ መውለድ እንዲያውም አዲስ አማኝ ጴንጤ፣ ጆሆቫ ሌላም ሌላ ኃይማኖት መስበክ ቀጠሉ።

እነሱ በጀመሩት መንገድ እኔም ሳም ጠባቂው መጠበቁን ትቼ ሌሎችም ኢትዮጵያውያን እነሱን ተከትለን መጣን። ታድያ ይህ በተለያዩ ምክንያቶች የተሰደደው ኢትዮጵያዊ ባህሉንና ታሪኩን ሳለመርሳት ቤተ ክርስቲያን ቢያቋቁም እነዚህ በታች ምሁራኖች አላስቀምጥም አሉ። እንዲሁም እነሱ በያዙት የፖለቲካ ድርጅት አልግባባ ያለ ህዝብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ምክንያት አንድ ሆኖ ሲቀራረብ ሲያዩት ተናደው ቤተክርስቲያኗን ሊበትኗት ታጥቀው ተነሱ። ወያኔ ከደደቢት ወደ አዲስ አበበ ሲገሰግስ የኢትዮጵያ ህዝብ ደርግንና የኢትዮጵያን ወታደር ለይቶ በማየት ሰላማዊ ሰልፍ እያደረገ ወታደሩን ሲደግፍ ምሁራን ግን ሰላማዊ ሰልፍ የሚያደርገውን ህዝብ ሲያወግዙና ወያኔን ሲተባበሩ የነበሩ ናቸው። ይህን በ1982 እና በ1983 በየአካባቢው ይሰበሰብ የነበረው ኢትዮጵያዊ ምስክር ነው። አሁን ተሰሚነት ካላቸው ምሁራን መካከል ከአንድ ስብሰባ ላይ "በቅድሚያ ኢህአዴግን አመሰግናለሁ ምክንያቱም የደርግ አረመኔ መንግስት የደመሰሰ ነው" ብለው የተናገሩ ናቸው። እንዲሁም ሌሎች ምሁራንም "ወያኔን ጊዜ እንስጣቸው እንያቸው" ይሉ የነበሩ ናቸው። እነዚህ ምሁራኖች በትምህርታቸው ተማምነው ወያኔ ይጠራናል እያሉ ሲጠባበቁ በወያኔ አይን የማይገቡ በመሆናቸው ሳይጠሩ በመቅረታቸው ዛሬ የወያኔ ጠላት ለመምሰል እየሞከሩ ናቸው። እነዚህ ከወያኔ ያልታደሙት ምሁራን ዛሬ "አቡነ ዘበሰማያትን" ሳያውቁ ቄስ ልሁን ይላሉ። ምነው ምሁራን በተማራችሁበት ኮርታችሁ የተጣላ አስታርቃችሁ አንድ የሆነችውን ቤተክርስቲያን እንደአርዮስ ለማፍረስ ከመሯሯጥ ለምን ለኢትዮጵያ አንድነት አትነሱም?

የእኛ ምሁራኖች በአገራቸው ፊደል ሊጽፉ አይፈልጉም። የኢትዮጵያውያን ፊደል ግዕዝ የሰው ልጅ አባት አዳም የፃፈበት መሆኑ አይካድም። ግዕዝ የፊደል አባት በመሆኑ የእኛ ምሁራን አይኮሩም። ይልቅስ እነሱ በውጭ ቋንቋ ሲጽፉና ሲናገሩ ነው የሚታዩት። እነዚህ ምሁራኖች በየስብሰባው ሲናገሩ የሚሰሙት በውጭ አገር ቋንቋ እንጅ በእኛ ቋንቋ አይደለም። ዛሬ አንድ ምሁር ቤት እንግድነት ቢኬድ ምሳ ብላ አይባልም። እንዲሁም ቡና ለመጠጣት አብሮ ቢኬድ እንደ ፈረንጅ ሁሉም የየራሱን ይከፍላል። ኢትዮጵያውያን ከሌላው ዓለም የምንለይበት አብሮ መብላት አብሮ መጠጣት መሆኑን እነዚህ ምሁራኖች አልተገነዘቡም። ብዙ ህዝብ ያለበት አሜሪካ እንኳ የራሳቸውን ባህል ሲያከብሩ ይታያል፤ የእኛዎቹ ምሁራኖች ግን ባህላቸውን ያናንቃሉ። አብሮ መብላት፣ በታሪክ መኩራትን፣ ፊደል አለመርሳትን፣ ሠንደቅ ዓላማ ማክበርንና ሌሎችንም ባህሎችን ኢትዮጵያውያን እንዳይረሱ፣ በተለይም አሜሪካን የተወለዱ ልጆች ማንነታቸውን እንዳይረሱ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ባላት አቅም ታስተምራለች። ታድያ እነዚህን ሁሉ የረሱ አንዳንድ ምሁራን ራሳቸውንም በመርሳታቸው ዛሬ ዘመቻውን በቤተክርስቲያን ላይ አድርገዋል። እኔ ምሁራንን ደግሜ ደጋግሜ ሳነሳ የታዘብኩት ስላለኝ እንጅ ከምሁራን ጥላቻ የለኝም። በዚህ አጋጣሚ ለአገራቸው የሚያስቡ አንዳንድ ምሁራን የሚያደርጉትን ቅዱስ ዓላማ ሳላውቅ እወዳለሁ። ለምሳሌ በዚሁ በሎስ አንጀለስ አካባቢ ቀደም ሲል የኢትዮጵያን ማህበር የመሰረቱት አንዲት ምሁር ቢሆኑም ምሁሯ ማህበሩን የግል ንብረት አድርገው ሌሎች ኢትዮጵያውያንን አላስቀርብም ሲሉ አምባሳደር አህዱ ሳቡሬና እንጂነየር ቅጣው እጅጉ ወይዘሪቷን በመቅረብ ማህበሩን አሳደጉት፣ በኋላም ህጋዊ አድርገው ኢትዮጵያውያንን ሰብስበው የሥራ አስኪያጅ መርጠው ለህዝብ አስረከቡ። ይህ የኢትዮጵያውያን ማህበር ትልቅ ግቢ ተከራይቶ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ተሰቅሎ ሲውለበለብ ያስደስት ነበር። ይህ ማህበር የአእምሮ ችግር የደረሰባቸውን ኢትዮጵያውያን ከዚህ ቤት ሰብስበው እንዲቀለቡ ያደርግ ነበር፤ ኢትዮጵያውያን ስብሰባ ሲያደርጉ ከዚሁ አዳራሽ እንደፈለጋቸው አምሽተው ይለያዩ ነበር። ነገር ግን በኋላ ሌሎች ሆዳም ምሁራን አጠፉት። ሌላ ማን እንደተረጎመው ባላውቅም (ተርጓሚው የሚመሰገን ምሁር ነው) በሎስ አንጀለስ የመንጃ ፈቃድ የጽሁፍ ፈተና በአማርኛ ነው የሚወሰደው። እንዲሁም በሎስ አንጀለስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያንን ለማሳደግ የሚጥሩትም አቶ የሰውከል አያሌው በጽሁፍ መገናኛ ኢንተርኔት የኢትዮጵያውያን እምነት እንዲስፋፋ አድርገዋል። እንዲሁም የኢትዮጵያን ፊደል በሰፊት ዌር አስፋፍተው ዛሬ እኛ በቋንቋችን በጽሁፍ መገናኛ በኢንተርኔት እንድንገናኝ ያደረጉ የሚመሰገኑ ምሁራኖች አሉ። በዚህ አጋጣሚ ለእነዚህ ምሁራን የምጠቁመው ቢኖር የሁሉን ፊደል አጠቃሎ የሚያገናኝ የጽሁፍ መገናኛ እንዲፈጥሩ ነው። ምክንያቱም ዋሽራ መገናኘት የሚችለው ከዋሽራ ብቻ ሲሆን፣ ፊደልም መገናኘት የሚችለው ከፊደል ጋር ብቻ ነው። ግዕዝም ሆነ ሌላም ሌላ መገናኘት የሚችለው ከተወሰነው ጋራ በመሆኑ ሁሉም ፊደል መገናኘት የሚችልበትን መንገድ በአንድነት ተባብራችሁ እንድትቀይሱ ነው። እንዲሁም ለኢትዮጵያ ስፖርት ፌዴሬሽን ኢትዮጵያውያን እንድንገናኝ በር የከፈተ በመሆኑ መስራቾቹም ሆነ አሁን ያሉት ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፤ አሁንም ህፃናት ልጆቻችንም እንዲሳተፉ ለልጆች የሚሆን ሰፋ ያለ ዝግጅት እንድታቅዱ አደራ እላለሁ። እንዲሁም ቋንቋን አስመልክቶ እነ ሊቀጠበብት መስፍን ወልደማርያም፣ አባ ተስፋ ስላሴ ሞገስ፣ ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ በየመጽሀፎቻቸው ላይ ጥራዝ ነጠቅ የሆኑትን የውጭ አገር ቋንቋዎች በአማርኛ እየተረጎሙ ያስቀመጡ ናቸው። ብዙ ምሁራን የውጭውን ዓለም ትምህርት ቀስመው በአገራቸው ፊደል ኮርተው መጽሐፍ፣ መጽሔትና ጋዜጣ የሚጽፉ ህዝባቸውን የሚያስተምሩ አሉ። መማር ማለት የአገርን ክብር ለማስጠበቅ ከህዝብ ጋር ሆኖ መሰቃየት እንጂ በውጭ አገር እየኖሩ በስንት ችግር የተመሰረተችውን የአንድነት አርማ ያነገበችውን ቤተክርስቲያን ለማጥፋት መሯሯጥ የምሁሩ የአርዮስ ሥራ ነው። እንግዲህ እኔ ይህን ሁሉ ልልበት የቻልኩት በውጭ ባለችው ቤተክርስቲያን ላይ ሶስተኛ አንጃ በመነሳቱ ነው። ይህ በስደት የነበረ ህዝብ የመሰረተውን ቤተክርስቲያን በ1980 ጀምረው አብረው ከብፁዕ ወአደናግር አቡነ ጳውሎስ ጋር ሁነው ከፈሉት። በ1984 ዓ.ም አቡነ ጳውሎስ በወያኔ ተጠርተው ወደ አዲስ አበባ ሲመለሱ ትግርኛ ተናጋሪ የሆኑና በፖለቲካ እምነታቸውም ወያኔን የሚደግፉ ለብቻቸው ቤተክርስቲያን ሲመሰርቱ የእነሱም ባራኪያቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ሆኑ። ሌሎች አንዳንድ ቤተክርስቲያኖች ከሁለቱም ላለመድረስ የራሳቸውን አቅዋም ሲይዙ አብዛኛው ቤተክርስቲያን በስደት ላይ ያሉትን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስን ተቀብሏቸዋል። እኚህ አሁን በቅርቡ ከስደት ወደ ስደት የመጡት አባት አሜሪካን ሲገቡ ምሁራን በኢንተርኔት እየተቀባበሉ ያዋከቧቸው ጀመር። ይህ እየቀጠለ በመምጣቱ በስደት ያለውን ቤተክርስቲያን

አሁንም እነዚህ ምሁራን ሊከፍሉት ተነሱ። በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ስም የተነሱት ዘመናዊ ምሁራን ለቤተክርስቲያን ያሰቡ አይደሉም። ለተመልካች ግን ይመስላሉ ምክንያቱም አንዳንዴ ዶግማውን ሲጠቅሱ ይታያሉ። እነዚህ ምሁራኖች በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ላይ የሚያቀርቡት ምክንያታቸው ብዙ ሲሆን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ለአብዛኛው መልስ ይሆን ዘንድ ላንዳፍታ መጽሔትና ኢትዮጵያ ሪቪው መጽሔት ላይ ባደረጉት ቃለ መጠይቅ መልስ ሰጥተውበታልና አንባቢ እነዚህን እንዲያነብ አደራ እያልኩ ለአንዳንዶቹ ግን የግሌን ማብራሪያ እሰጣለሁ።

"ቤተክህነቱና አቡነ መርቆርዮስ ከደርግ ጋር ሠርተዋል ይላሉ" አሁን በስደት ላይ ያሉት ፓትሪያርክ እንኳን ከደርግ ጋር ሊያብሩ ቀርቶ የጳጳስነቱን ሹመት ያገኙት ጥር 13 ቀን 1971 ዓ.ም. ነበር። ፓትሪያርክ ሆነው የተሾሙት በ1979 ዓ.ም ሲሆን ነጭ ሽብርም ሆነ ቀይ ሽብር በርዶ ነበር። ነገር ግን የሰሜን ኢትዮጵያ ወያኔዎችና ተገንጣዮች ይዋጉ ስለነበር እልቂትን ለማብረድ ለደርግ መንግሥት፣ ለወያኔ ቡድን፣ ለሻዕቢያ ቡድን በኢትዮጵያ ካሉት የሃይማኖት አባቶች ጋር ሁነው የጻፉት ደብዳቤ ምስክር ነው።

ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆርዮስ ለመንግሥትና ለድርጅቶች ብቻ አይደለም የሰላም ጥሪ ያቀረቡትና ደብዳቤ የላኩት፣ ቀድሞ ከሲኖዶሱ ለተለዩት ጳጳሳት ወደ ሲኖዶሱ እንዲመለሱ ጥሪ ያደረጉና በቤተክስርቲያን ሰላም እንዲወርድ የጣሩ አባት ናቸው። ከእነዚህም ውስጥ ብፁዕ ወአደናግር አቡነ ጳውሎስና ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ማትያስ ይገኙበታል። ታድያ ይህን ያደረጉትን አባት አንዳንድ ቤተክርስቲያንና ዘረኛ ምሁራንና የወያኔ ቅስቀሳ ታክሉበት ስማቸውን ያጠፉቸዋል።

"የኃይማኖት አባት አይሰደድም ይላሉ"

ስደት መስራቹ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ንጉስ ሔርዶስ ሲያስፈልገው ከቅድስት ማርያምና ከዮሴፍ ጋር ወደ ግብፅና ኢትዮጵያ ተሰዷል ተንከራቷል ተሰቃይቷል። ስለዚህ በጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስደት የተጀመረ ሲሆን ውሎ አድሮ በተለያዩ አህጉራት የሚኖሩ የኃይማኖት አባቶች በተለያዩ ጊዜ ሲሰደዱ ሲጋዙ ሲሰቃዩ እንደኖሩ ታሪክ ያስረዳናል። በ840 ዓ.ም በዮዲት(ጉዲት) ዘመን፣ በ1524 በአጤ አህመድ ግራኝ ጦርነት፣ በ881 ድርቡሽ ጉንደርን ሲያቃጥል ህዝበ ክርስቲያን ሲያጠፋ የኃይማኖት አባቶች ተገድለዋል ብዙ የኃይማኖት አባቶች ተሰደዋል። በ1928 ፋሺሽት ኢጣልያ ኢትዮጵያን ባጠቃ ጊዜ የኃይማኖት አባቶች እነ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ጴጥሮስ፣ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ሚካኤል ሲሰየፉ ሌሎች የገዳም መነኮሳት ታርደዋል ተሰደዋል። በ1968 በደርግ ዘመን ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ቴዎፍሎስ ታርደዋል ሌሎች የኃይማኖት አባቶችም ታስረዋል ተሰደዋል። በወያኔ መንግሥት በ1984 ፓትሪያርክ ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሪዎስና ሌሎች ጳጳሳት ተሰደዋል። እነ አምኀ ኢየሱስ ታስረዋል፣ ባህታዊ ገብረ መስቀል ሲታሰሩ ሲፈቱ ፀራቸውን ሲላጩ፣ ባህታዊ ፈቃደ ሰላሴ ተሰይፈዋል ሌሎችም ምዕመናንና የኃይማኖት አባቶች እየተሰደዱና እየታሰሩ ናቸው። ስለዚህ የኃይማኖት አባቶች መሰደድና መታሰር መሰቃየት ያለ በመሆኑ የአሁኖቹ አባቶች ቢሰደዱ ፊሪ አያሰኛቸውም። ታዲያ እናንተ ምሁራን እነዚህን ጳጳሳቱን መሰደድ የለባቸውም ካላችሁ ለምን እናንተስ እንደ ምሁር ሐኪም ሊቀጠበብት አስራት ወልደየስ ለህዝብ አለኝታ አትሆኑም ነበር? ከዚህ ህዝቡን በነገር ከምትከፋፍሉ ከአገር ቤት ገብታችሁ ከዚህ የምትሉትን እዚያው ብላችሁ ከህዝብ ጋር ሁናችሁ አትሞቱምና አትታሰሩም ነበር?

ጽሁፌን ስጀምር እንደጠቀስኩት የዓለም ቤተክርስቲያን መከፋፈል ዛሬ ለእኛም ቤተክርስቲያን በመድረስ ላይ ነው። የትርጉም ችግር ቤተክርስቲያንን ሲከፋፍላት ውሎ አድሮ የፖለቲካ ሰዎች ተጨምረውበት የግላቸውን ጥቅም ለማራመድ ሲሉ ሊቅ መስለው ቤተክርስቲያን የተጠጉት ሰዎች ቤተክርስቲያኗን ከፋፈሏት። የወደፊቱ እጣ ምን ይሆን? በውነቱ ሱባኤ ያስገባል። የኢትዮጵያ ህዝብስ በውጭ ባለው ኢትዮጵያዊ ወገኑም ሆነ በቤተክስርቲያንና በፖለቲካ ድርጅቶች ትልቅ ተስፋ ሲኖረው ይህን የመሰለ ችግር ምሁራን መፍጠራቸውን ሲሰማ እንዴት ይዘን? ስለዚህ ካለፈው ጥፋት ተምሮ ለሚመጣው አብሮ መስራት መጣር ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ መፈክሩ ሊሆን ይገባዋል እላለሁ። እግዚአብሔር ሆይ የተራራቀውን አቀራርበህ የተጣላውን አስታርቀህ የፈረሰውን ህግህን በህብረት እንድንገነባ ልብ ስጠን አገራችንንም እንድንጠብቅ እርዳን መንፈስ ቅዱስን ላክልን ያን ከፋፋይ ሰይጣንን ከመካከላችን አርቅልን! አሜን።

ለደርግ መንግሥት፣ ለወያኔ ቡድን፣ ለሻዕቢያ ቡድን በኢትዮጵያ ካሉት የሃይማኖት አባቶች ጋር ሁነው የጻፉት ደብዳቤ

ሰኔ 29 ቀን 1982 ዓ.ም.

ጦርነት ተወግዶ በምትኩ ሰላምና ደህንነት እንዲሰፍን እኛ የሃይማኖት መሪዎችና መላው ምዕመናን ያልተቋረጠ ጸሎት ስናደርግ ቆይተናል፤ እያደረግንም ነው።

በተለይም በሰሜን ያገራችን ክፍል ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በአሁኑ ወቅት ከመቸውም ይልቅ እጅግ አስከፊ በሆነ ደረጃ ላይ የሚገኘው ጦርነት እንዲቆም በተለያዩ ጊዜያት የተደረጉ የሰላም ውይይቶች እስከዛሬ ድረስ የታሰበውን ያህል እንዳችም መልካም ውጤት ለማስገኘት አለመቻላቸው እጅግ አሳስቦናል። የህፃናት ዕልቂት የቤት ንብረት መፍረስ የብዙ ሺህ ሰላማዊ ህዝብ ህይወት ማለፍ የልማት አውታሮች መፈራረስ በየቦታው የህዝብ ፍርሃትና ሥጋት እጅግ አስጨንቆናል።

በዚህ የተነሳ ሰኔ 27 ቀን 1982 ዓ.ም የጋራ ስብሰባ አድርገን ያወጣነውን የሰላም ጥሪ አንድ ገጽ ከዚህ ጋር አያይዘን እየላክን ጥሪያችንን ተቀብላችሁ በየደረጃውም በምናደርገው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በጉልህ በመሳተፍ ያልተቆጠበ ድጋፍና ትብብር እንድታደርጉልን ከጠበቀ አደራ ጭምር በሁላችንም ፈጣሪ ስም እንጠይቃለን። የምትሰጡንንም መልስ ባስቸኳይ እንጠባበቃለን። የሁላችንም ፈጣሪ በሀገራችን ሠላም ይስጠን።"

| | | | |
|---|---|---|---|
| (ፊርማ) | (ፊርማ) | (ፊርማ) | (ፊርማ) |
| አባ መርቆሬዎስ | ሐጂ ዑመር ሑሰይን ዓብዱልዋሒድ | አባ ጳውሎስ ዓድዋ | ቄስ ፍራንሲስ እስጢፋኖስ |
| ፓትርያርክ ርዕሰ | የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች | ካርዲናል ሊቀ ጳጳሳት | የኢትዮጵያዊት ወንጌላዊት |
| ሊቃነ ጳጳሳት | ከፍተኛ ጉባኤ | ዘካቶሊካውያን | ቤተክርስቲያን መካነ የሱስ |
| ዘኢትዮጵያ | ሊቀመንበር | | ፕሬዚዳንት |

✝

# ወይዘሪት እመቤት ለገሠ

## 1960 — 1991



### የወይዘሪት እመቤት ለገሠ አጭር የሕይወት ታሪክ

ወይዘሪት እመቤት ለገሠ ከአባቷ ከአቶ ለገሠ ቢነግድ ከእናቷ ከወይዘሮ ወለላ ሚያዝያ 1960 ዓ.ም. (እ.ኢ.አ) ተወለደች። ለእናትና አባቷ አንድ እሷ ብቻ በመሆኗ የብርቅ ልጅ ነበረች። ዕድሜዋ ለትምህርት እንደደረሰም የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በአዲስ አበባ አሜሪካን ሚስዮን እንደፈፀመች አዲስ አበባ በሚገኘው መድኃኒያለም 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በመግባት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን አጠናቀቀች።

የምትወዳቸው ወላጆችዋንና ሀገሯን ተለይታ መጀመሪያ በሱዳን ከዚያም ኬኒያ በስደት ስትኖር ቆይታ ወደ አሜሪካ በመምጣት ኖሮዋን ስትመራ ቆየች። እመቤት ከልጅነት እስከ ሕይወቷ ፍፃሜ ድረስ ትሁት፤ ሰው አክባሪና ከፍተኛ የሰው መውደድ ተሰጥዖ ነበራት።

እመቤት ለገሠ ባደረባት ሕመም ከሆስፒታል ገብታ ስትረዳ ከቆየች በኋላ ህመሟ ሊሻላት ስላልቻለ ጥር 5 ቀን 1991 ዓ.ም. ( 1/12/99) ከዚህ ዓለም በሞት ተለየችን። እመቤት ሆስፒታል በነበረችበት ጊዜ በቅርብ ሆናችሁ ስታስታምሙዋት ለነበራችሁና በመመላለስም ለጠየቃችሁ እንዲሁም በፀሎታችሁ ላልተለያችኋት የኢትዮጵያ መረዳጃ ማህበር በኔቫዳ ጥልቅ የሆነ ምስጋናውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያ መረዳጃ ማህበር በኔቫዳ (ኢመማኔ) አባላቱን ደጋፊዎቹንና ሌሎች የቅርብ ወገኖቿን ጭምር በማስተባበር አስፈላጊ ሁኔታዎች ሁሉ እንዲሟሉ በማድረግ አስክሬኗ ወደ ኢትዮጵያ ተልኮ ዘመዶቿ ባሉበት የቀብር ሥነ ሥርዓቷ በክብር እንዲፈፀም አድርጓል።

በቅርብ ተገኝታችሁ፤ ከርቀትም መጥታችሁና በስልክም ሀዘናችሁን ለገለፃችሁ በሙሉ የኢትዮጵያ መረዳጃ ማህበር በኔቫዳ (ኢመማኔ) ጥልቅ ምስጋናውን ያቀርባል።

የኢትዮጵያውያን የመረዳጃ ማህበር በኔቫዳ ላስ ቬጋስ
2005 PARADISE ROAD - LAS VEGAS, NV 89104
(702)791--5155

# ልብ ወለድ

## ስጋት

(ከልሳነ ላንዳፍታ – አዲስ አበባ)

"... ለዚህ ነገ ትተናት ለምናልፍ ዓለም .... ጥላቻን፣ መራራቅን፣ መቃቃርን መቦጫጨቅን ምን አመጣው? .... ክፉ ክፉውን ትተን ደግ ደጉን እናስብ። በየቤታችን፣ በየጕረቤታችን፣ በየሀገራችን እርቅ እናውርድ ይቅር ለእግዚአብሄር እንባባል።"

ዕምኛዬ ከራስጌዬ ቆማ እንዲህ አይነቱን ነገር ስታነበንብ ከእንቅልፌ ነቅቼ አዳመጥኳት። የተሸፋፈንኩበትን አንሶላ ከፊቴ ላይ ገልጬ ስመለከታት ውሀ በብርጭቆ ይዛ ቆማለች።

ዕንቅልፍ ባጨናበሰው ዓይኔ ስመለከታት ቀይ ፊቷ ወደ እንጆሪነት አደላብኝ፣ ትላልቅ ዓይኖቿ የኤሌክትሪክ ባውዛ መሰሉኝ፤ የቁመቷ ርዝመት የእኔን እጥረት የመጣን ስሜት አሳደረብኝ፤ ረዥሙ ሹሩባዋ ደግሞ የባህታዊ ምስል ፈጠረብኝ። እኔ ርዝመቷን፣ ቅጥነቷንና ቅላቷን እንደማደንቅላት ሁሉ፣ እሷም እጥረቴን፣ ደንዳና ሰውነቴንና ጠይምነቴን ስታደንቅልኝ ኖራለች። በጥርስ፣ በአፍንጫና በአንገት ውበት አንተናነስም።

"በጥዋት ለምን እንቅልፍ ትነሺኛለሽ ሳባ? ምንድነው የምታነበንቢው?" አልኳት ተበሳጭቼ።

"እንቅልፋም። ይልቅ ተነሳ። እኔ እንኳን ቤተክርስቲያን ደርሼ አስቀድሼ መመለሴ ነው። ቄሱ ለተሰበሰበው ምዕመናን የተናገሩትን ነው አሁን የደገምኩልህ። ካስፈለገም ደግሞ ፀበል እረጭሀለሁ"። ብላ ውሀውን በእጇ ሰፈረች።

"ተይ እባክሽ ... ቀልድ ድሮ ቀረ" ብዬአት እንደገና ልሸፋፈን ስሞክር፣ ብርጭቆዋን አስቀምጣ ገፈፈችኝ።

"እንዴት! ... አሁንም ገና የማታው አልበረደልህም እንዴ? ... ይልቅስ ተነስ"

"ተይኝ ብዬሻለሁ ... ልተኛበት። ሰላም ስጪኝ"

"ሰካራም። ለመሆኑ ማታ የሰራሽውን ታስታውሰዋለህ? ሆድ ያባውን ብቅል ያወጣዋል አሉ" አለች

ዝም አልኳት። ማታ ተበጣብጠን ተኳርፈን ማደራችንን አስታውሳለሁ። አሁን እንዲህ ልታግናረኝ መብቃቷም ቤተክርስቲያን ደርሳ በመመለሷ እግዚአብሔር ታርቋት ይሆናል።

"ተናገር እንጂ ኤልያስ" ስትል አፋጠጠችኝ።

"በእርግጥ ማታ ሞቅ ብሎኝ ነበር። መጠጥ ያሰከረኝ እንዳይመስልሽ – ነገር ነው ያሰከረኝ።"

"ነገር እንዳሰከረህማ አውቃለሁ። አንተ ሰክረህ እኔንም አስክረኸኝ አደርክ። ... ለመሆኑ ቀለበትህን የት እንደጣልከው ታውቃለህ?"

ቀለበቴ ጣቴ ላይ ያለመኖሩን ስመለከት ለጊዜው ደነገጥኩ። የአዕምሮዬን ክር አጠንጥኼ የማታ ሁኔታችንን ሳስታውስ ግን ወዲያው ተረጋጋሁ። ምንም ብሰክር ራሴን አልሳትኩም ነበር።

"ለማንኛውም አሁን ተነስ። የዕሁድ ቡና ሳሎን ውስጥ አፈላለሁ። ማንኛውንም ነገር እዚያው እንነጋገራለን" ብላኝ ልብሷን ቀያይራ ከመኝታ ክፍል ወጣች።

ትላንት ማታ መጠጥ ቢጤ ቀማምሼ ነበር የገባሁት። እና እንዳልኩትም ያሰከረኝ መጠጥ ሳይሆን ነገር ነበር። ከጓደኞቼ ጋር እየጠጣን የሰሞኑ የኢትዮጵያና የኤርትራ የድንበር ግጭት ምክንያት ስለሚኖረው የመለያየት አደጋና ስጋት ሁኔታ እያነሳን ስንነታረክ ነበር። ባለቤቴ ሣባ ገ/ተንሳይ የኤርትራ ተወላጅ መሆኗን ጓደኞቼ በሙሉ ስለሚያውቁ በውይይታችን ጣልቃ "ይብላኝልህ" እያሉ የተወራረዱብኝ ይመስለኛል። ከመጠጡ ጋር ይህን መራራ ነገር ስጠጣ አምሽቼ ወደ ቤቴ ስገባ ሣባ ራት አዘጋጅታ ስትጠብቀኝ አገኘኋት። በሠርግ ባንጋባም ቀለበት ካደረግንበት ጊዜ ጀምሮ አብረን መኖር ጀምረናል። በጥንቃቄዋም ይሁን በአጋጣሚ ልጆች ግን አልወለድንም። እኔም ልጅ የመውለድ ሀሳቡ ለጊዜው ስለሌለኝ ውለጅልኝ ወይንም ለምን አልወለድሽም ብዬ ጠይቄያት አላውቅም። ለሠርግ እየተዘጋጀንና አልሞላ እያለን በቀለበት ብቻ ከስምንት ዓመታት በላይ ስንቆይ በፍቅራችን መሀል ንፋስ ገብቶ አያውቅም ነበር። እሷም ሆነች እኔ የዘር ጉዳይ ችግር ሆኖ ሳያስጨንቀን በፍቅር የበላይነት ቆይተናል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በኢትዮጵያና በኤርትራ መንግስት የተፈጠረው ችግር እንደሌላው ሁሉ የእኔንና የሳባንም ቤት እያንኳኳ መሰለኝ። እኔ በተፈጥሮዬ በጣም ነፃ ሰው ስለሆንኩ እሷም ነፃ እንድትሆን ስለምፈልግ እንደሌላው ወንድ የት ወጣሽ? የት ገባሽ? ዛሬ ምን ስትሰሪ ነበር? ... የሚሉትን ነገሮች አንስቼ አላውቅም። ለእሷ ግድ ስለሌለኝ አልነበረም። ነገር ግን በቃ ሰው ነፃ ሳደርግ ደስ ስለሚለኝ ነው። ግን አሁን ልክ እንዳልነበርኩ አይነት እየተሰማኝ ሲመጣ በራሴ ላይ መነጫነጭ ጀምሬያለሁ። እሷም ነገሩ የገባት ይመስለኛል። ራሳችንን መደበቅ ጀምረናል፣ መኰራረፍና ሳንነጋገር መክረም ጀምረናል፤ ያለመተማመን ይታይብናል። ትላንት ማታ ደግሞ ከዚህም ደረጃ አልፈን ክፉና ደግ ተነጋግረናል። ወደፊት አብረን የመኖር ተስፋችንን ይህ የሰሞኑ ጦርነት እንዳጨለመብን በምሬት ነግሬያት፣ ከወዲሁ እንድንለያይ ቀለበቴን አውልቄ መወርወሬንም አስታውሳለሁ። ከዚያ በኋላ ምን እንደተደረገ አላውቅም። በነገር ደንዝዤ ስለነበር ጭልጥ ያለ ዕንቅልፍ ወስዶኛል። ሳባ ከጐኔ እንዳላደረች እርግጠኛ ነኝ። ምናልባት እዚያ ጠባብ ሶፋ ላይ ተኰራምታ ነገሩን በሆዷ ስታኝክ አድራ ይሆናል። ...

ለማንኛውም አሁን የተቀደሰውን የዕሁድ ቡና አብረን እንድንጠጣ በሌሊት ልብሴ ላይ ጋቢዬን ደርቤ ወደ ሳሎን ወጣሁ።

ባህላዊው የቡና አፈላል ስርዓታችን ደስታን ከሚሰጡኝ ነገሮች አንዱ ነው። ሣባ ሁሌም በቡና ጀበናው፣ በስኒው፣ በከሰል ምድጃው፣ በዕጣን ዕቃው፣ በፈንድሻውና በቄጠማው ተከብባ መሀሉ ላይ ስትቀመጥ ድምቀቱን ትጨምርለታለች። ዛሬ ግን ከፊት ለፊቷ ቁጭ ብዬ የቡናውን ስርዓት ለመካፈል ሳያት የምትጠነቀቅልም መስላ ታየችኝና ቀና ብዬ አየኋት። የሆነ ነገር ታጉተመትማለች።

ሣባ ቡናውን ቆልታ ቤቱን ካሸተተች በኋላ ጀበናውን ከሰል ምድጃው ላይ ጥዳ ቡናውን ልትወቅጥ ወጣች። በኤሌክትሪክ መፍጨቱ የስርዓቱን ውበት

ስለሚቀንሰው በሙቀጫና ዘነዘና መወቀጥ አለበት ባይ ናት። ሣባ ከአጠገቤ ዘወር ከማለቷ ፣ እኔ የቡና ጀበናውን እየተመለከትኩ በሀሳብ ጭልጥ ብዬ ሄድኩ።

የቡና ጀበናው ቅርፅ የኢትዮጵያን ካርታ መሰለኝ። ደግሞም በመጠኑም ይመስላል። ኢትዮጵያ የቡና ሀገር በመሆኗ በጀበናው ቅርፅ ተስላ ይሆናል፤ ወይንም የቡና ጀበናው በኢትዮጵያ ቅርፅ ተበጅቶ ይሆናል። በዚህ ቅርጿ ትቆይ ይሆን? እንደገና ሌላ አዲስ ቅርፅ እየተነደፈላት ይሆን? ... ከሆነስ አዲሱ ቅርጿ የጥንቱን ባህል፤ ቅርስ፤ እምነት፤ አኗኗርና አጠቃላይ ህይወት ለውጦ በአዲስ እምነትና ፍቅር ያኖረናል ወይስ ህልውናችንን ከመሰረቱ አናግቶ ያጨራርሰናል? ... አሮጌውን ቂም አስረስቶ በሰላም ያኖረናል ወይንስ አዲስ ቂም አስረግዞ ለትውልድ ያስተላልፍልናል? ይህ ነው ትልቁ ጥያቄና ትልቁ ስጋት! ለጥያቄው ሁሉም እንደየስሜቱና እንደየአመለካከቱ ይመልሳል። አፈንድቶ መፈንዳት የሚፈልግ አለ፤ አርግቦ መርገብ የሚፈልግ አለ፤ አስታርቆ መታረቅ የሚፈልግ አለ ... በየዓይነቱ ነው። የማይሰጋ ልብ አለት መሆን አለበት። ትንሿ ልቤ ሁሌ ትሰጋለች። ስጋቴን ዕውነት ከመሆን ያድነው። ...

"ሰሞኑን ፀባይህ በጣም ተቀይሯል" አለችኝ ሳባ፤ ቡናውን ወቅጣ ተመልሳ ዱቄቱን ጀበናው ውስጥ እየጨመረች።

የማታውን ፀብ ልትቀሰቅስብኝ መሰለኝ፤ ሆኖም መልስ መስጠት አለብኝ።

"ባይታወቅሽ ነው እንጂ የአንቺም ፀባይ ተቀይሯል" አልኳት።

"ምክንያቱ ምን ይመስልሀል? ..." አለችኝ አይን አይኔን እያየች።

"ስጋት ይመስለኛል ..."

"የምን ስጋት? ..."

"የመለያየት ስጋት ... ፍቅራችንን የማጣት ስጋት ... የጦርነት ስጋት ... ህብረታችንን የማጣት ስጋት ... ንብረታችንን የማጣት ስጋት ... ለእኔነታችን ስንስገበገብ እኛነታችንን የማጣት ስጋት ... እኔና አንቺ ደግሞ ከተለያየ ዘር ልበለው ሀገር የመጣን ስለሆንን አብሮ የመቆየት ዕድላችን ራሱ ስጋት ላይ ወድቋል ..."

ለአንዳፍታ ንግግሬን አቋርጬ ስለ ሣባ ማሰብ ጀመርኩ። ተወልዳ ያደገችው እዚሁ አዲስ አበባ ውስጥ ቀበና ወንዝ አካባቢ ነው። ሣባ የልጅነት ትዝታዬ፤ ፍቅሬ፤ ሚስጥሬ፤ ስብዕናዬ ኑሮዬ የተገነባው ቀበና ላይ ነው ባይ ናት። እናቷ አማርኛ መናገራቸውን ከማወቄ በቀር ወሎዬ ይሁኑ ጉጂሜ፤ ጉንደሬ ይሁኑ መንዜ አጥብቄ አልጠየቅኳትም። አባቷ ቅልጥ ያለ ኤርትራዊ ነው። እንግዲህ ሣባ አሁን ባለው ሁኔታ ከየቱ እንደምትመደብ ባላውቅም እንደባህላችን የአባት ዘር ነውና የሚታየው ኤርትራዊ መሆኗ ነው። እኔ እስከማውቀው ድረስ ሣባ በኤርትራዊነቷ እኔን የጎዳችኝ ነገር የለም። ልክ እንደሌላው ሰው ነው የተቀበልኳት የተቀበለችኝ። ግን በግሏ በአገሬ ላይ ችግር አድርሳ ወይም እያደረሰች እንደሆነ የማውቀው ነገር የለምና በዚህ በኩል አፌን ሞልቼ መናገር አልቻልኩምና ጥርጣሬው አለኝ።

"...እና መፍትሄው ምን ይመስልሃል?" አለች ሣባ ዓይኖቿን ከጀበናው ላይ ነቅላ ወደ እኔ እያተኮረች።

"የምኑ?" አልኳት ሀሳብ ውስጥ በመቆየቴ ተደናግሮብኝ።

"አሁን ያነሳኸው አጠቃላይ ችግር ... እና ደግሞ ... በተለይ የኔና የአንተ ችግር ..."

ለጥያቄዋ አፋጣኝ መልስ ልሰጣት አልቻልኩም። ትንሽ ማሰብ ነበረብኝ።

"ትላንት ማታ እንዳደረግከው ቀለበትህን አውልቀህ መወርወሩ መፍትሔ ይመስልሃል?" አለችኝ፤ እሷው ቀድማ ግንባሯን በማኮሳተር።

አዝማሚያዋ የጦርነት እሳት የሚጭር ስለመሰለኝ አሁንም ዝም አልኩ። ቡናው ፈልቶ ሊገነፍል የጀበናውን ከዳን ሽቅብ ሲገፈትረው አይኔን ሳበው። ጀበናው ውስጥ የሚፈሉት፤ የሚንተከተኩትና የሚገነፍሉት የኢትዮጵያ ልጆች መስለው ታዩኝ። ወደው አይደለም። የአስተዳደር እሳት፤ የፖለቲካ እሳት፤ የድህነት እሳት፤ የቁጭት እሳት፤ የአድልዎ እሳት፤ ከስር እየጠበሳቸው ነው። እሳቱ በዝቷ ል! ጀበናው ይተረተር ይሆን? ቡናው ከእሳቱ ላይ ወርዶ ከመስከኑ በፊት ገንፍሎ ቢያልቅስ? በስጋት ተኮማትሬ ፈዘዝኩ። ...

"እንዳንተማ ቢሆን ትላንት ማታ የመጨረሻ መለያያችን ነበር" አለች፤ ቡናው እንዳይገነፍል በስኒ ቀንሳ እየጠበቀች – እያንተከተከችው።

"እንዴት?" አልኳት፤ ሆን ብዬ ነው።

"አብደህ አሳብደኸኝ ነበር፤ ከቤቱ ውጭልኝ ብለህ ቀለበትህን አውልቀህ ስትወረውር ትዕግስቴን ጨርሼ ለመሄድ ተነስቼ ነበር። ጭለማው ስላስፈራኝ ሶፋ ላይ ተኮራምቼ አድሬ እስኪነጋ ጠበቅኩ። ጠዋት ደግሞ እግዚአብሔር ንዴቴን አስረስቶ ወደ ቤተክርስቲያን እንድሄድ መራኝ። እዚያም የተቀደሱ ስብከቶችን ሳዳምጥ ስለቆየሁ ከመጥፎ ይልቅ ቀናውን መንገድ አሳየኝ። እና ይኼው እኔና አንተም በሰላም ለመነጋገር በቃን" ብላ ጀበናውን ከእሳቱ ላይ አወረደችው።

ጀበናው ከወረደም በኋላ ቡናው መንተክተኩንና ለመገንፈል ሽቅብ ሽቅብ ማለቱን አላቋረጠም። ቶሎ ይሰክን ይሆን?

ሳባ ፈንድሻውን አስከተለች። በትንሽ ብረት ድስት ውስጥ ትንሽ ዘይት ጠብ አድርጋ ፈንድሻውን ከጨመረች በኋላ ከድናበት እሳቱ ላይ ጣደችው።

"ለመሆኑ እንዲህ አይነት ፍቅርና ጋብቻ በኔና በአንተ ብቻ የተጀመረ ይመስልሀል?"

ጥያቄዋ ድንገተኛ ቢመስልም መልዕክት አለው። የታላቅ ወንድሜን ቤተሰቦች ልታስታውሰኝ ፈልጋ ነው። የሦስት ታላቁ የሆነው ወንድሜ ሚስቱ ኤርትራዊ ስትሆን ብዙ ዓመታት አብረው በመኖር ስድስት ልጆች አፍርተዋል። እስካሁን ድረስ ፍቅራቸው ሳይናጋ በሰላም ይኖሩ ነበር። ከሣባም ጋር የተገናኘነው ታላቅ ወንድሜ ቤት በተደረገ ድግስ ላይ ነው። የወንድሜ ሚስትና የሳባ ዘመዶች የአንድ መንደር ትውልዶች መሆናቸውን እሷው ከተቀራረብን በኋላ አጫውታኛለች። ወንድሜና ሚስቱ

እንደቀድሞው በፍቅር ይኖራሉ? ወይንስ በስተርጅና አዲሱ "የድንበር ፖለቲካ" ቤታቸው ገብቶ የመለያየቱ ዕጣ በእነሱም ቤት ገብቶ ያምሳቸው ይሆን? ከሚለው ስጋት ነፃ አይደለሁም።

"ሁኔታው አዲስ አይደለም፤ በእኔና በአንቺም አልተጀመረም። ሆኖም አሁን ሁኔታው ሁሉ ተቀይሯል፤ ፍቅሩ የእኛ ቢሆንም ለእኛ አብሮ መኖር ወሳኙ ሌላ ሆኗል" አልኳት እየፈራሁ።

"የፍቅርና የአብሮ መኖር ፍላጐት ካለ እንኳን እኔና አንተ በፍቅር አብረን ያለነው ይቅርና ድሮ ተጣልተው የነበሩ አማራ ባልና ኤርትራዊ ሚስቶች ዛሬ ለዚህ ስጋት ብለው ይቅር ለእግዜር ተባብለው ተጣምረው የለ!" አለችኝ። እነማንን ለማለት እንደሆነ ስለገባኝ

"ሣባ ስለሌላው አላውቅም፤ እንኳን ስለሌላው ስለራሴም አላውቅም" አልኩኝ።

"እንዴት?"

"አዎና! በእርግጥ እንደምትወጂኝ አውቃለሁ። ነገር ግን ስለ ኤርትራና ኤርትራዊነት ያለሽን ስሜትም ሆነ ተሳትፎ አውርተንም ሆነ አንስተን ስለማናውቅ ያለሽን ተሳትፎም ሆነ ግንኙነት ማወቅ ይሳነኛልና ... " አልኳት። ስራሽ ያውጣሽ እንደማለትም ጭምር ነው።

"ኤልያስ በዘር ላይ ያለኝን ስሜት በደንብ እያወቅክ አንተም ሌላው መጠቋቆሚያ እንዳደረገኝ ትጠረጥረኛለህ ማለት ነው? ይህ ለእኔ በጣም አንጀት የሚቆርጥ ንግግር ነው" አለች እንደልማዱ እንባዋ እየቀደማት።

"ሳብዬ ይቅርታ አድርጊልኝና እኔ ከሁሉም ጋር ሳትነካኪ ቀርተሽ ነፃ ሆነሽልኝ በፍቅር ብንኖር ምርጫዬ ነው ግን እንዳልኩሽ ስጋቴን ነው የገለፅኩት። ደግሞ ማወቅ ያለብሽ ዝም ብሎ የሚያባርርሽ የለም ሁኔታው ዘርን (ኤርትራዊነትን) ብቻ የሚመለከት አልመሰለኝም ሰዎቹ የሚያዩት ተሳትፎ ነው ተብሏል። ይህን ማለቴ ደግሞ ሊያናድድሽ አይገባም" አልኳት

"ለምን አልናደድም? ከዛሬ ነገ መነጠቁኝ እያልኩ በማስብበት ወቅትና አንተን መሸሸጊያ ባደረግኩህ ወቅት አንተ ደግሞ የራስሽ ጉዳይ አይነት ስትሆንብኝ ለምን አልናደድ?" ብላኝ የፈንድሻውን ብረት ድስት ጆሮዎች ይዛ እየነቀነቀች ማብሰል ቀጠለች።

ዝም አልኳት።

"እኔ እኮ እዛ መሄዱን አይደለሁም የፈራሁት። ከአንተ እስከዘለዓለሙ ተለይቼ እንዳልቀር ነው ስጋቴ" አለችኝ።

ፈንድሻው ሲበስል እየተንጣጣና እየፈካ የድስቱን ክዳን ገፍትሮ ለመውጣት ሲሞክር ሀሳቤን እንደገና ጠለፈው። ሁሉም በየአካባቢው ብሶተኛ ነው። ማንም መታፈንን አይፈልግም። ግውዙ ፈንድሻ እንኳን ሳይቀር ክዳኑን ገፍትሮ ነፃ መውጣት ይፈልጋል። ለዚህ መድኃኒቱ ዕውቀትና ሙያን ተጠቅሞ መያዝ ነው። ተበታትኖ እንዳያልቅ ባለሙያ ያስፈልገዋል።

የሰው ልጆች በያሉበት ችግሮቻቸውን ፈትተው፣ ግጭቶቻቸውን አስወግደው፣ ከጦርነት ርቀው በሰላም እንዲኖሩ ሁሌም እመኛለሁ። ነገር ግን ምኞት ብቻ ሆኜ ቀረሁ። የእኔ ሙያ ምህንድስና ነው። የግዑዝ ነገር መሀንዲስ ሆኜ የአፈርና የድንጋይ ቦታ ስቀይስ ከምኖር፣ የሰው ልጆች ልብ መሐንዲስ ሆኜ ቀናውን መንገድ ባሳያቸው እመርጥ ነበር። የማህበራዊ ሳይንስና የስነልቦና ጠቢባን የሰዎችን ልብ መግራትና አመለካከታቸውን ማጥራት ካልቻሉ ሙያቸው ምን ይሰራል? ... መፈላሰፍ ጀመርኩ።

"ትሰማኛለህ ኤልያስ? ..." አለች ሣባ ፈንድሻውን ከእሳቱ ላይ አውርዳ ከብረት ድስቱ ወደ እርቦ እየገለበጠች።

"እያዳመጥኩሽ ነው ሣባ"

"የስጋት ማስታገሻውም ሆነ ማርከሻው ዋናው መድሐኒቱ ፍቅር ነው። ጊዜያዊ ግጭቶችና የሚያስከትሏቸው ስጋቶች በሙሉ ከፍቅር በታች ነው። ጠንካራ ፍቅር ሁሉንም ያሸንፋል"

ይህማ ያደግኩበትና የኖርኩበት ዕምነቴ ነው። አሁን የጊዜው ትኩሳት ዕምነቴን እያናጋ ትንሽ አዘበራረቀብኝ እንጂ! ...

"ይኼውልሽ ሳቢና ...አሁን ፍቅሩ ያለው እንደእኔና አንቺ ባሉት በተጣመሩ አንዳንድ ቤተሰቦች ቤት ብቻ ላይ ነው። ሌላው ቦታ ግን ጥላቻው ከገደብ ሞልቶ አፍንጫው ላይ ደርሷል። እናም ይህች ጊዜ የሁሉንም ጥላቻ የምታስተነፍስ ናትና እሰጋለሁ በጣም እሰጋለሁ።"

ዝም አለች።

"እናም ሳቢና ምንጊዜም እኔና አንቺው ብንነጋገር፤ 'እናውቅላችኋለን' የሚሉ ጣልቃ ባይገቡብን፣ 'እንወክላችኋለን' የሚሉ ቡድኖች ባይረብሹን ጥሩ ነበር። እኛም የሌሎች የጥቅም መሣሪያ ባንሆን፣ ባንቸኩልና ሁሉም ነገር ውስጥ ለመግባት ባንደነብር ጥሩ ነበር" አልኳት።

ምን ለማለት እንደፈለግሁ የገባት አልመሰለኝም። ወይም አልሰማችኝም። ሣባ ፈገግ ብላ ዕጣኑን ማጨሻው ገል ላይ ጨመረች። የቡናው ስርዓት ደመቀ። እኔና ሣባም በዕጣኑ ጭስ ውስጥ እንደገና . . . ተያየን።

ቡናው ሰክና ኮለል ብሎ ተቀዳ። ፈንድሻውም ተዘገነ። ሁሉም ነገር እንደቡናው ቶሎ ይሰክን ይሆን? ...እግዚአብሔር ያውቃል።


**በዓለም አቀፍ ደረጃ ብዙ አንባብያን ባላት ላንዳፍታ መጽሔት ላይ ድርጅትዎን ያስተዋውቁ!**

# ትዝ ከሚለን . . .

(ከደንዬው ደነባ)

ወረቀት ላይ ሰፍረው የተነበቡ፣ በሬዲዮ ተነግረው የተደመጡ! ...ምናልባትም ያላስተዋልናቸውና ልብ ያላልናቸው አልያም ጨርሰን ያልሰማናቸው...ድጋሚ ብናነባቸው እንኳ የማንደበርባቸው ይልቁንም የምንደመምባቸው ...ገረሜታን የሚጭሩና ደነቁታን የሚፈጥሩ አንዳንድ ነገሮች እኒሁላችሁ።

## ቁባቶች

"ዎልድሜየር እንደፃፈው አፄ ቴዎድሮስ በመቅደላ ተራራ ላይ ብቻ 28 ቁባቶች አስቀምጠው ነበር። በዚህ ምክንያትም በአባት እንጂ በእናት የማይገናኙ ልጆች ነበሯቸው። ...ቴዎድሮስ ወ/ሮ የተመኙ የሚባሉ የየጁ ተወላጅ ቁንጅናቸው ስለማረካቸው ከባላቸው ነጥለው አስመጥተው የራሳቸው አድርገዋቸው ነበር። እስከህይወታቸው ፍፃሜም ድረስ ሲወዷቸው ኖረዋል።

በተጨማሪም የደንቢያዋን ወይዘሮ ሂሩትን በቁንጅናቸው አድንቀውና ወደው ቁባት አድርገው አስቀምጠዋቸው ነበር። ..."

## ልጅ

"...አጤ ቴዎድሮስ ስድስት ልጆች ቢኖራቸውም ከህጋዊ ሚስት የተወለደው ግን ዓለማየሁ ብቻ ነው። አለማየሁ ደብረ ታቦር ከተማ በ1853 ዓ.ም. በተወለደ ጊዜ አፄ ቴዎድሮስ ተደስተው መድፍና ጠመንጃ አስተኩሰዋል። 500 ያህልም እስረኞች ፈተዋል።

ቴዎድሮስ አንድ ቀን ከመኳንንቶቻቸው ጋር ሲጫወቱ ድንገት በጨዋታው መኃል "በዓለም ላይ ካለ ነገር ሁሉ ሽታው እጅግ ደስ የሚልና ልብ የሚመስጥ ምንድነው?" ብለው መኳንንቶቹን ጠየቁ።

መኳንንቱም ሁሉም የሚያውቀውን የሽቶ ዘርና ሊላም ሁሉ ተናገረ። ቴዎድሮስም ሁሉንም አላወቃችሁም ካሉ በኋላ "የህፃን ልጅ ጠረን ነው" ብለው መለሱ ይባላል።

ቴዎድሮስ አለማየሁን ታቅፈው ሲስሙ ንዴትና ብስጭታቸው ሁሉ ይጠፋላቸው ነበር ይባላል።

## እንዴት ተገናኛችሁ?

ያ...ኔ! ያኔ ... እጅግ ተወዳጅ፣ ተናፋቂና ተደማጭ የነበረው "የእሁድ ጥዋት የሬዲዮ ፕሮግራም" (ለመሆኑ ዘንድሮም አለ?) ባልና ሚስት እየ ጋበዘ የሚያነጋግርበትና "እንዴት ተገናኛችሁ?" እያለ የሚጠይቅበት ዝግጅት ነበረው።

መቸስ ያኔ ያልተሰማ ድንቅ ገጠመኝ አልነበረም። አንዳንዱማ ተዓምር የሚያሰኝ ነበር።

" ...አንድ እሁድ ረፋዱ ላይ ነው። ድንገት መንገድ ስታቋርጥ አየኋት። በቃ! ...ቀልቤ አረፈባት። ደስ ስላለችኝ ተከተልኳት። ቀረብ አልኩና ላናግራት ሞከርኩ። ገላመጠችኝ። አልደነገጥኩም። ራመድ ራመድ ብላ አውቶቡስ ውስጥ ገባች። እኔም ገባሁ። ብዙ ፌርማታዎችን ካለፍን በኋላ ወረደች። እኔም ወረድኩ። የባጥ የቆጡን እየቀባጠርኩ ተከተልኳት። ወሬዬ ሁሉ ቁብም አልሰጣት። ጥቂት እንደሄድን አንድ ትልቅ የብረት በር አንኳኳች። ተከፈተ። ገባች። ...እኔም ግብት! አባት እናቷ ሌሎችም ቤተሰቦቿ በረንዳ ላይ ሆነው ቡና ይጠጣሉ። እርሷ ደንግጣለች። እነርሱም ተገርመው ያዩናል። ድንገት ፈገግ አለችና 'የመሥሪያ ቤቴ ባልደረባ ነው፣ እዚህ ሠፈር ያሉ ዘመዶቹን ሊጠይቅ መጥቶ ...' ብላ ቀበጣጠረችና አስተዋወቀችኝ። ዞር ብላ ደግሞ በግልምጫ አነሳችኝ! በቃ! ከዛ ወዲያ ቤተኛ ሆንኩኝ። ከልጅቱም ጋር በቅጡ ተግባባን! ...ይኸው ዛሬ ትዳር መስርተን ሁለት ልጆች አፍርተናል።" አንዱ አባወራ

## ለቅሶ ቤት

"... አንድ ወዳጄ አባከህ ቀብር አለብኝና አብረን እንሂድ ሲለኝ ተከትዬው ሄድኩ። እዛ ስንደርስ አየኋት። ደረቷ ገለጥ ብሏል። በቃ! በደረቷ ተማረኩ። ያን የሚያምር ደረቷን በጣቶቿ እየደቃች ...እየሾኸች ታለቅሳለች። አይኔ ከደረቷ ሊነቀል ነው? አይ ደረት!

ቀልቤ አረፈባት። ነፍሴም ወደዳት። ከቀብሩ ሥነ ሥርዓት በኋላ ቤታቸው መመላለስ ጀመርኩ። የአባቷ አርባ እስኪወጣ ድረስ እየተመላለስኩ አስተዛዘንኩ።

ቤተሰቡ በሙላ 'ይሔ ደሞ ማነው?' በሚል ዕንቆቅልሽ ሲጠያየቅብኝና ሲጠቋቆምብኝ ሰነበተ። መጨረሻ ላይ ባል ሆኜ ተገኘሁ። ያቺ ደረቷ የማረከኝ ልጅ የዛሬዋ ባለቤቴ ናት ።

ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ – ነፍስ ይማር!

## ሊፍት ውስጥ

"...መጀመሪያ ሳያት በፀጉሯ ወደድኳት! ከዛ ማዘጋጃ ህንፃ ሊፍት ውስጥ ድንገት አገኘኋት። ሳታስበው ሳም አደረግኳት! በቃ! በዚህ የተጀመረው ፍቅር ለጋብቻ አበቃን። ...ልጆችም አፈራን።" –

መሬቱ ይቅለለውና አርቲስት ወጋየሁ ንጋቱ

## በግጥም

"...ትምህርት ቤት ነው። አጋጣሚ አየኋትና ደስ አለችኝ። በቃ ጊዜም አልሰጠሁ። ደብዳቤ ፃፍኩላት ያኔ ወጉ ይኼው ነበር።

'ስንጋ ፈረስ መጣ እያለ ክም ክም
አንቺን ካላገባሁ ሱሪ አላጠልቅኩም'

ይህን ግጥም ፅፌ ሰደድኩላት። ያው እንደዛትኩት ሆነና እሷኑ አገባሁ።" – ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን

## "አፍ ዘጊም ብሏል"

" ...በልጅነቴ ዕንቁላል እያዞርኩ እሸጥ ነበር። ይሄን ሥራ ሁሉም የሠፈሬ ልጆች እየለመዱት መጡና ገቢዬ ቀነሰ። እኔ ይሄኔ ጥሬውን ተውኩና የተቀቀለ እንቁላል ማዞር ጀመርኩ። በዚህም ሲመጡብኝ ደግሞ ዕንቁላሉን በምግብ ቀለም እያቸጉረጉርኩ 'ከሁሉም የተለየ ባለቀለም እንቁላል!' እያልኩ መሸጤን ቀጠልኩ።

ቆየሁና ደግሞ ጋዜጣ ማዞር ጀመርኩ።

'እዚችው ቁጭ እንዳሉ! ...መላዋን አለም ይመልከቱ!' እያልኩ ጋዜጣ ቸበቸብኩ።

ፓስቲ ቤት ሁላ ተቀጥሬ ሰርቻለሁ። ባለቤቱ አንድ አይነስውር አረብ ነበር። ሁሌም ከባንኮኒው አጠገብ አይጠፋም። እዛችው ስር ቁጭ ብሎ ማቱን ይቅማል። እኔም እዛው ሆኜ ፓስቲ ስሸጥ እውላለሁ። ግን ይጠራጠራል መሰለኝ በሙሉ ልቡ አያምነኝም። አይነ ስውር ስለሆነ ከፖስቲው እየሰረቅኩ የምበላ ይመስለዋል።

ቀኑን ሙሉ ባንጐራጐር ብዘፋፍን ወይ ደግሞ ዝም ብዬ ባወራና ብለፈልፍ ደስ ይለዋል። ብቻ ዝምታዬን አይወደውም። በቃ! ...ወይ ማፍጨት አለብኝ።

ለተወሰኑ ደቂቃዎች ዝም ካልኩና ድምፄን ካልሰማ ይጠራጠርና ሙ—ክ! ብሎ 'ፓውሎስ አፍ ዚም ቢሏል አይነጋገሪም! ፓስቴ እየበላ ኖ?' ይለኝ ነበር።"

– ጋዜጠኛና ደራሲ ጳውሎስ ኞኞ – ነፍስ ይማር!

## "ከሱ ጠቆሩ!"

"ፕሬዚዳንታችን ለኢትዮጵያ እያሰቡ ከሱ! ጠቆሩ እንጂ ለመሆኑ መልካቸው እንዲህ ነበር? እውን የጓድ መንግስቱ መልክ ይሔ ነበር!?"

በዘመነ ደርግ የደቡብ ኦሞ አስተዳዳሪ የነበሩት አቶተፈራ እንዳለው በ2ኛው የሸንጐ ጉባዔ ላይ ከተናገሩት

## "ለምን ያስፈራሩናል?"

" ...አንደኛ በምሑርነቴ፣ ሁለተኛ በህዝብ እንደራሴነቴ፣ ሦስተኛ በአስተማሪነቴ እውነትን መናገር ይገባኛል። ለእውነት ሲባልም ራስንም መግደል ይቻላል። የኢትዮጵያን ችግር በመፍታትና በመተንተን ረገድ እርስዎ ሁሉንም እኔ እፈፅማለሁ የሚሉት ለምንድን ነው? ለምን ያስፈራሩናል። ለምንስ ያፍኑናል? በተደጋጋሚ ስለ ሂስ መራራነትና ያቺንም መራራ ኪኒን ስለመዋጥ ያነሳሉ። ይህችን መራራ ኪኒን እርስዎ ራስዎ መዋጥ አለብዎ። የኢትዮጵያ ችግር የሚፈታው በቁጣ አይደለም። በመሞህም አይደለም። እርስዎ የፈለጉትን ብቻ በመፈፀም አይደለም። ለምሳሌ የፕሮፌሰር መስፍንን የሰላም ፎርሙላ ለምን ያንኳስሱታል? ይህንን ለመቀበል አንችልም። በኢትዮጵያ ጉዳይ ሁላችንንም ያገባናል። ..."

ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በመጨረሻው የሸንጐ ስብሰባ ላይ መንግስቱ ኃ/ማርያምን ሲወርፉ

## ወንጀለኛ አይደለሁም

"...እነ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም የሚመሰረተው የሽግግር መንግስት ያለፈውን መንግስት አባላት በወንጀል እንዳይፈልግ የሚል ሃሳብ በፎርሙላቸው ውስጥ አስፍረዋል። ይሄ ምን ማለት ነው? እኔ ወንጀለኛ አይደለሁም። መስፍን ወልደማርያም ምህረት የሚሰጠኝ ሰው አይደለሁም። ለመሆኑ ማነው መስፍንን ፕሮፌሰር ያደረገው? እኛ እኮ ፕሮፌሰር ለመባል ወረቀቱን ባናቀርብም በዚህች አገር እኮ ብዙ ምርምር አድርገናል። ለዚህች አገር ዕድገት አዕምሯችን ቆስሏል። ደም ፈሶበታል! ..."

– ኮ/ል መንግስቱ ኃ/ማርያም

በመጨረሻው ሸንጐ ስብሰባ ላይ በምሬት ከተናገሩት

## እሱ ..ን – ተው..ው!

" ...ውድድሩ የተካሄደው ውጭ አገር ነው። የ3 ሺህ መሰናክል የሩጫ ውድድር ነው። የለበስኩት ቁምጣ ጠበብ ያለ ስለነበር ጠበቅበቅ አድርጐኛል። ውድድሩ ተጀመረ። በአንደኝነት እየመራሁ ቆይቼ ልጨርስ ጥቂት መቶ ሜትሮች ሲቀሩኝ የለበስኩት ቁምጣ ድንገት 'ፏ !' ብሎ ፈነዳ። ቁምጣው ደግሞ ከፓንት ጋር አንድ ላይ ተያይዞ የተሰራ በመሆኑ ከውስጥ የለበስኩት ሌላ ነገር የለም። እና እንትን! ይሄ እንትኔ ከግራና ከቀኝ ታፋዬ ጋር እየተጋጨ አስቸገረኝ። ደግሞም ሁኔታው አሳፍሮኛል። እና ሀሳቤ ሁሉ ወደዚያው ሄደ። እጄን ወደታች እየሰደድኩ ለማስተካከል ስገታል አሰልጣኝ ንጉሴ ሮባ ሜዳ ውስጥ ገብቶ ጐን ጐኔ እየተከተለ 'እሽቱ! እሽቱ! በፈጠረህ እሱን ተወው!' እያለ የጮኸው መቼም አይረሳኝም። አትሌት እሸቱ ቱራ

## በላይ

" ...እኔማ! መጀመሪያውንም እናቴ ስትወልደኝ በላይ ብላኛለች!"

–ገሚሱን ደጃዝማች፣ ገሚሱን ቀኛዝማች እያልክ በስርህ ያሉትን ሰዎች አንተው ራስህ ሹመት ስጠሃቸው። ለመሆኑ አንተን ማን እንበልህ? ለሚለው የጃንሆይ የለበጣ ጥያቄ ጀግናው በላይ ዘለቀ የሰጠው ምላሽ።

---

## . . .መቼ ይሆን እኛም ...

(ከገፅ 11 የዞረ)

ተጠያቂ መሆኑንና ተገቢውን ቅጣት እንደሚቀበል ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ዕድሜያቸው ለጋ ቢሆንም ስለሀገራቸው ሁኔታ ምን ያህል ግንዛቤ እንዳላቸውና ብዙ ህዝብ በተሰበሰበበት ተነስተው ለመናገር መድፈራቸው ለወጣት ኢትዮጵያውያን እንደምሳሌነት የሚጠቀስና ወጣቶቻችን ሀገራችንን በሚመለከት ጉዳይ ላይ በሚደረጉ ስብሰባዎች እንዲካፈሉ ግንዛቤያቸው እንዲዳብር ማስተማርና ሐሳባቸውንም እንዲሰጡ ማበረታታት ከሁላችንም የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑን ያስታውሰናል። "የልጅ ነገር" የሚለውን ማንኳሰሻ ጣል አድርገን የዛሬዎቹ ልጆች የወደፊት ሀገር ተረካቢዎች መሆናቸውን ከአእምሮአችን ለደቂቃ እንኳን ማውጣት እንደማይገባን መገንዘብ አለብን። ዛሬ ከሁሉም በላይ በሞራል ውድቀት የወደፊት ህይወታቸው ብሩህ ተስፋ የጨለመባቸው የሀገራችን ወጣቶች ናቸው ወደድንም ጠላንም ነገ ሀገሪቱን የሚመሩት፣ ከእነሱ በኋላ የሚመጣውን ትውልድ የሚያስተምሩና ምሳሌም የሚሆኑ።

የኒውዮርኩን ከተ[illegible] ስብሰባ የጠሩት ሚስተር ሼይስ የኢምፒችመንት ደጋፊዎችና ነቃፊዎችን ሪፐብሊካን፣ ዲሞክራት ወይንም Independent party አባሎችንና ተከታዮችን ሚዛኑን በጠበቀ ሁኔታ ለሁሉም ወገኖች እድል በመስጠት የመረጣቸውን ህዝብ አስተያየት በጥሞና በማዳመጥ ለሚቀርብላቸው ህጋዊም ሆነ ፖለቲካዊ ጥያቄ እንደአመጣጡ እየመለሱ ሳለ ፕሮግራሙ በቴክኒክ ችግር ምክንያት እስከ ስብሰባው ማብቂያ ድረስ መተላለፍ እንደማይችል የሚገልፅ ማስታወቂያ ከሬዲዮ ጣቢያው ሲነገር እኔም ውይይቱን በተመስጦ ከምከታተልበት ነቃሁ። የቅናት ስሜት አደረብኝ፣ አንገበገበኝ። እኛስ ለዚህ እንበቃ ይሆን ብዬ ራሴን ጠየቅኩ። አዎ! እንበቃለን ለምን አንበቃም ሰው ከደረሰበት እንደርሳለን ተባብረን ልዩነታችንን አስወግደን ብዬ ለራሴ ቃል ገባሁ። ከሀገራችን ውጭ የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ከአምባገነን መሪዎች መንጋጋ አምልጠን የሀገራችንን ሁኔታ በመመልከት በሀዘን ልባችን እየደማ ቅሬታችንን ብንገልፅ የወህኒ ቤት ጨለማ ይበላናል፣ ደማችን ደመ—ከልብ ሆኖ ይቀራል ብለን ሳንፈራ እንደልባችን መናገር የምንችልበት ቦታ ስለሆነ ያለነው ይህንን ዕድል እንጠቀምበት፣ እንወያይ፣ ተቃራኒ ሐሳቦችን አቅርበን እንፋጭበት፤ ከሁሉም በላይ ግን በሐሳብ ስለተለያየን በመካከላችን ጥላቻን አናፍራ። በሀገራችን "ከባህር ማዶ" የሚለው ቃል ብዙ ጊዜ መራቅን ብቻ ሳይሆን በትምህርታቸው የገፉ፣ በአስተሳሰብ የበሰሉ፣ በሥልጣኔ የተራመዱ የዓለም

(ወደ ገፅ 43 ይዞራል)

# ኑሮ በአሜሪካ

በአሜሪካ ኑሮአችሁ ምን ገጠማችሁ? ኑሮን ለማመቻቸት በሚደረጉ ጥረቶች ላይ ባሉ የማህበራዊ ኑሮ ችግሮች ላይ ለመወያየት ይህ አምድ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል እምነት አለን። በውይይት የጋራ መፍትሄ ለማግኘት ይቻላል። በተጨማሪም በዚህ አገር ኑሮአችን ተሰባስበን በጋራ የምናከናውናቸውን ተግባራት ለማስተዋወቅም ትልቅ አስተዋጽኦ ያደርጋል እንላለን። በአምዱ ላይ በተለይ ካልተጠቀሰ በስተቀር የሚቀርቡት አስተያየቶችም ሆኑ የገጠመኝ ታሪኮች አንባብያን የሚልኩልን መሆኑ ይታወቅልን።

## ኑሮ በዘዴ

(ከበደ ኃይሌ – ከአትላንታ)

በዚህ በውጭው ዓለም ያለን ሰዎች የአገራችንና የውጪው አገር የአኗኗር ዘዴዎች ምን እንደሚመስሉና ልዩነታቸውንና ተመሳሳይነታቸውን እስካሁን ሳንገነዘብ የቀረን አይመስለኝም። ቢሆንም ከልምድ ያገኘኋቸውን ዘዴዎች በተግባር ላይ አውዬም ጠቃሚነታቸውን ያረጋገጥኳቸውን ስልቶች በጽሁፍ ለአንባብያን ባቀርብ የማያውቁ በተለይ ለውጭ አገር ኑሮ አዲስ ለሆኑ ወገኖቼ ጠቃሚ ሀሳብ ይሰጡ ይሆናል በማለት ለማካፈል አሰብኩ።

"ራስህን በማሻሻል ኑር" ተብሎ የተነገረውን የአባቶችን አባባል በተግባር ላይ ለማዋል ያለንን መጠነኛ የገቢ ምንጭ በቁጠባ እየተጠቀምንበት ጥሩ የገቢ ምንጭ ካላቸው ነዋሪ ወገኖች እኩል ለመኖር እየጣርን ኑሮን ማሻሻል የእያንዳንዳችን ግዴታ ሊሆን ይገባዋል። በእርግጥ በዕድሜ መግፋት፣ በጤና መታወክና ከአቅማችን በላይ የሆኑ ምክንያቶች ካሉን በቂ ማስረጃዎች ስለሆኑን ምንም ማድረግ አይቻልም። ካለበለዚያ ግን በራሳችን ስንፍና ራሳችንን ከኮሚኒቲው የአኗኗር ደረጃ ዝቅ አድርገን እየኖርን ከሆነ አገርንና ታታሪ ወገኖችን ማስናቅና ማስወቀስ ይሆናል።

ማንኛውም ሰው አንዴ ከአገሩ ከወጣ በኋላ ሁኔታዎች እስከሚስተካከሉ ድረስ በትዕግስት ኃላፊነትን እየተወጡ ራስን በመርዳት አልፎ ተርፎም አገር ቤት ያሉትን ዕርዳታ ፈላጊ ዘመዶቻችንን ለመርዳት መድረሱ ራሱን የቻለ የህሊና ንቃት፣ ሞራል የሚሰጥ የአኩሪ ዜጋ ውጤት ነው። በውጭ አገር በሙያው ተሰማርቶ የሚተዳደር ወገን ቁጥር እጅግ በጣም ጥቂት መሆኑን እያወቅን በሙያዬ (በትምህርቴ) ስራ ካላገኘሁ ተራ ሥራ አልሰራም ወይም አገሬ ባለስልጣን የነበርኩ ሰው ይህን አናሳ ሥራ ስሰራ የሚያውቀኝ ሰው ቢያየኝ ምን ይለኛል እያልን በማማረር ብቻ ያመጣናትን ቅርስ እየበላን ሰው በማስቸገር ራሳችንን ዝቅ አድርገን በህብረተሰቡ መታየቱ የባሰ ስለሚሆን አገራችን ያሳለፍነውን ወርቃማ ጊዜ ማስታወሱን ትተን፣ እንዲሁም በስደት የምንኖርባቸው አገሮች ከአገራችን የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ በጣም የተሻሉ መሆናቸውን ተገንዝበን በእነዚህ አገሮች በመኖራችን የኑሮ መሻሻል ዕድል እንደሚገጥመንና አካባቢውን መስለን ማደር እንዳለብን አስቀድመን በመገንዘብ ከኮሚኒቲው፣ ከተማሩ ሰዎች፣ በችግሩ ውስጥ ታግለው ከወጡት ወገኖች ምክር በመቀበል ራስን ለማስተካከል ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው።

አብዛኛው ሰው አገሩ በነበረበት ጊዜ የውጭ ኑሮ በቀላሉ ወርቅና ገንዘብ ብዙ ሳይደከም የሚገኝበት መስሎ ይታየዋል። ግን እዚህ ተመጥቶ ውስጡ ገብተን በተግባር ስናየው ኑሮን አሸንፎ ለመኖር ቀን በብርሃን፣ ሌት በጨለማ ተጉዘን፣ በፀሀይ ሐሩር ተቃጥለን፣ በክረምት በብርድ ተቆራምደን፣ የሰው ፊት ገርፎን፣ ከሌባው ከቀማኛውና ከነፍስ ገዳዩ ታግለን፣ አዕምሮአችንን ደንዝዞ መላው ሰውነታችን ዝሎ ወገባችን ተቆርጦ፣ ውስጥ እግራችን ተቃጥሎ እየሰራን ገቢ የምናገኝ መሆኑን ተገንዝበናል። ታዲያ በእንዲህ ያለ ሁኔታ የምናገኘውን ገንዘብ በቁጠባና በዘዴ እየተጠቀመን የኑሮ ፍላጐታችንን ሁሉ አሟልተን እንድንኖር ካልጣርን ድካማችንን ለምንድን ነው?

ለዚህ ችግር መፍትሔ ይሆናሉ ብዬ የዘረዘርኳቸውን ሃሳቦች እንደአስፈላጊነታቸው፣ እንደየስፍራውና ሁኔታው አጣጥሞ በተግባር በማዋል ጠቃሚነታቸውን መመዘን የአንባቢ ድርሻ ይሆናል።

■ በየጊዜው ቼክ ስንቀበል በእጃችን ላይ ብዙ ገንዘብ የተትረፈረፈ ስለሚመስለን ገበያ ከመሄዳችን በፊት የምንፈልውን ዕቃ ለመግዛት ወጪና ገቢያችንን የሚያሳይ ዝርዝር በቅድሚያ በማውጣት በጀት መድቦ በመያዝ በወቅቱ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ብቻ መግዛት፣

■ ያልታሰበ ዕዳ ውስጥ እንዳንገባ አስፈላጊ ባልሆነ ጊዜ ክሬዲት ካርድ ይዘን እንዳንወጣ መጠንቀቅ።

■ ወጪን በጋራ እየሸፈኑ መኖር፦ ይህ የአኗኗር ዘዴ ከፍተኛ ትዕግስትን ይጠይቃል። ስለሆነም ኢኮኖሚውን ተቋቁም ትርፍ ገንዘብ እያስቀመጥን ለመኖር ከተፈለገ ወገብን ጠበቅ፣ ፍላጐትን ገታ፣ አመልንም በጉያ አድርጐ ካልተኖረ በስተቀር ሁልጊዜ ተዝናንቶ የፈለግነውን ሁሉ አድርገን ተቀማጭ ቅርስ ይኖረናል ብለን ማሰብ ከንቱ ምኞት ነው። ስለዚህም ያልታሰበ ማህበራዊ ኑሮና የጤና ችግር ከሚያመጡብን ነገሮች ሌላ በተቻለ መጠን የጋርዮሽ የአኗኗር ዘዴን መጠቀሙ ወጪያችንን ለመቀነስ የሚረዳ አንዱ ዘዴ ነውና ይህንን ዘዴ ልናገኝና ልንጠቀም የምንችልበትን መንገድ ማመቻቸቱ ጥሩ ነው። ከነዚህም አንዱ መኖሪያ ቤት በጋራ መከራየት፣ ምግብ ነክ የሆኑ ነገሮችን አብሮ በማዘጋጀት በአንድነት መጠቀም ... የመሳሰሉት ናቸው።

■ ምንም ቢሆን ያገር ልጅ ለክፉ አሳልፎ አይሰጥም ብለን እያሰብን የምንፈልገውን ነገር ለማግኘት ስንል ወገኖችን ወይም በቅርብ የምናውቀውን ሰው ይሉኝታ ሳይዘን በሚሰጡን መረጃዎች ለመጠቀም ሙከራ ብናደርግ ዓላማችንን ግብ ለመምታት ይረዳናል።

■ የሳንቲም ጥርቅም ብር ይሆናል፦ ገንዘብ አክባሪዋን ትጠጋለች እንደሚባለው ደቃቅ ሳንቲሞች ሲኖሩን እያጠራቀምን ብንጠቀምባቸው ወይንም ባንክ ብናስቀምጣቸው ጥቅም እየሰጡን ለኑሮአችን አስተዋጽኦ ያደርጋሉና ሳንቲሞች ዋጋ በሚሰጥባቸው አገር ውስጥ ተቀምጠን ዋጋ አለመስጠቱ ሞኝነትና ራሳችንን ከአካባቢው ጋር አለማዋሃዳችንን ይጠቁማል።

■ አብዛኞዎቻችን የምንጠቀምባቸው የሥራ ልብስና ጫማ ከሚያሰራን ኩባንያ በሚሰጡን ዩኒፎርም በመሆኑ በየጊዜው የምንገዛቸው ልብሶችና መጫሚያዎችን

ለመጠቀም ዕድሉ ስለማይኖረን በአየር ጠባይ፣ በሌላም ሌላም ነገር ቀለማቸውም ሊቀይር ይችላል፤ እንዲሁም የመገልገያ ዕቃዎቻችንም ብዙ ሳንጠቀምባቸው ቀለማቸው ተላልጦ ስናያቸው አገልግሎት አይሰጡም ብለን ልንጥላቸው እንችላለን። ከዚህ ሁሉ እነዚህን ነገሮች የማንጠቀምባቸው መሆኑን ከወሰንን ወደ አሮጌ ዕቃ መሸጫ መደብሮች ወስደን በመጠነኛ ዋጋ መሸጥ አለበለዚያም ለሰብዓዊ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች በዋጋ አስተምነን ብንሰጥና ደረሰኝ ብንቀበል በዓመቱ መጨረሻ ላይ ከIRS ጋር ገቢና ወጪዎቻችንን ስናወራርድ ብናስመዘግብ ክሬዲት ይሰጠናል።

■ የነጋዴዎች የገበያ መሳቢያ እንዱና ዋናው መንገድ በማስታወቂያ ዘዴዎችና የቋንቋ ስልቶቻቸው ሳቢያ በመሆኑ ማስታወቂያዎችን በመስማት ብቻ ወደ ገበያ ሄደን ዕቃ ከመግዛታችን አስቀድመን የሚከተሉትን መርሃ ግብር እንከተል፦

– በልዩ ልዩ አቅጣጫ የዋጋ አሰሳ በማድረግ ዋጋ እናመዛዝን

– የምንሄድባቸውን መደብሮች ቦታ እንወስን

– የሽያጭ/የማጣሪያ የግብይት ወቅቶችን በተቻለ መጠን እንጠቀምባቸው።

■ በዓላትን አስታከን የቅርብ ወገኖች መገናኛ ድግስ(ፓርቲ) ለማዘጋጀት በምንፈልግበት ጊዜ እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በሚል ስሜት ያልታሰበ ወጪ እንዳናደርግ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። እንዲሁም የምንጠራውን እንግዳ ብዛት መወሰንና ከዛም በምንጠራው እንግዳ መጠን ድግሱን ለማዘጋጀት በጀት መወሰን አስፈላጊ ነገሮች ናቸው።

■ በየወሩ ስለሚደርሱን የክፈሉ መጠየቂያዎች ሰነዶች (ቢልስ) በሚደርሱን ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ ትኩረት የምንሰጠው የገንዘቡ መጠን ከፍ ብሎ ስናየው እንጂ ዝርዝር ጉዳዩ ውስጥ ገብተን ነጥብ በነጥብ ሂሳቡ እንዴት እንደተሰራ የመመልከት ልምዱም፣ ጊዜውም፣ ትዕግስቱም አይኖርንም። ስለዚህ ያለአግባብ ከሆነ የወጪ ክፍያ ለመቆጠብ፣ – አጠቃቀም ላይ ጥንቃቄ ማድረግ፣

– የክፍያው መጠን (ገንዘቡ) ካለወትሮው በዛ ብሎ ካገኘነው ከመክፈላችን በፊት ኩባንያውን (ድርጅቱን) ማነጋገር

– ከክፍያው ቀን በፊት ዕዳን ከፍሎ ማጠናቀቅ ከቅጣት ከመዳናችንም በላይ ድርጅቱ በእኛ ላይ እምነት እንዲያድርበት ያደርጋል።

– የከፈልንባቸውን ቢያንስ የመጨረሻ ደረሰኞች ለማስረጃ ስለሚረዱን ለጊዜው መያዝ የሚሉት ናቸው።

እንግዲህ ከላይ አጭሩ ለመግለጽ የሞከርኳቸው የኑሮ መቆጣጠሪያና የማሻሻያ ዘዴዎች ሁሉንም ጠቅሼአቸዋለሁ ባልልም ለመነሻ ያህል ስለሚያገለግሉ በተግባር ላይ በማዋል ውጤታቸውን መመልከት ይቻላል።

## የሴቷ ወይስ የወንዱ?

(ገሊላ አያሌው – ከሳንሆዜ)

ይህን ፅሁፍ ለማቅረብ ያነሳሳኝ ባለፈው የላንዳፍታ እትም ላይ ጋብቻን በተመለከተ ከበደ ኃይሌ የተባሉ አንድ ፀሐፊ ከአትላንታ የፃፉትን በማንበቤ ነው።

የሴትና የወንድን ተፈጥሮአዊ የመሳሳብ ጉዳይ አስመልክቶ ብዙ ሲነገር ቆይቷል። በተለያየ መንገድ ተተርኳል። ብዙ ብዙ ትርጓሜዎች እየተሰጡት ሲደመጥ ሲነበብ ተከርሟል። ይህ ጉዳይ የብዙዎቻችንን ትኩረት የሚስብበት ምክንያት ለሰው ልጆች ኑሮ ዋናውን ቦታ ስለያዘ ነው። አንድ ወንድና ሴት ይፈላለጋሉ፣ አልፎም ይቀናጃሉ ቀጥሎም የእሱን ውጤት ሌላ አዲስ ፍጥረት ያበረክታሉ። እያሉም እየበዙ እየበዙ ቤተሰብ ከፍ ሲልም ህብረተሰብ ወደሚለው ደረጃ ይደርሳሉ። እንግዲህ ለዚህ ታላቅ አስተዋጽኦዋቸው መነሻቸውን ማሳመር አለባቸው። "ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል" እንዳይሆን የእነሱ ድርጊት ለሚፈጥሩት ቤተሰብ አልፎም ህብረተሰብ ቃር እንዳይሆን ጥንቃቄ ማድረግ ያሻል። ኃላፊነቱ የሴቷ ወይንም የወንዱ ብቻ ሳይሆን የሁለቱም መሆን አለበት እላለሁ።

የፊዚክሱ ህግ ተቃራኒ ኃይሎች ይሳሳባሉ አይደል የሚለው? ተቃራኒ ፆታዎችም እንደዚሁ ህግ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ ሊሳሳቡ ይችላሉ። ይህ ተፈጥሮአዊ ህግ ነው። ግን ብዙ ሴቶች ወይንም ወንዶች መሀል አንዷን ወይንም አንዱን ወደ አንዱ ወይንም ወደ አንዷ እንዲሳቡ የሚያደርጋቸው ምንድን ነው? ለዚህ የተለያየ ምክንያት ይኖራል። ሲተያዩ ልባቸው ሊደነግጥ ይችላል። አስደንጋጩን ኃይል ግን በውል ይህ ነው ብሎ ለመግለፅ ያስቸግራል።

ለሴቷ ምናልባት ቀጠን፣ ረዘም ያለ ለግላጋ ቁመና ወይንም አጠር ደቦልቦል ብሎ እንኳንስ በእጅ በዓይን ገረፍ ቢያረጉት ሊፈነዳ ይችላል ተብሎ የሚገመት ሰውነት ያለው ወንድ በሚጥም ፈገግታ የተሞላ፣ በእጅ የያዙትን የሚያስረግፍ፣ የአነጋገርና የአቀራረብ ሁኔታ የተላበሰ ጉብል ወይንም ይሄ ሁሉ ሳይሆን የዳበረ ኪሱ፣ እንደ ውሀ የምትፈሰው መኪናው አልያም አዋቂነቱ ብስለቱ የአስተሳሰቡ አድማስ ስፋትና ሌሎች ሌሎችም ሊሆኑ ይችላሉ። ወንዱም በፊናው በሴቷ የሚደነግጠው በፀጉሯ፣ በማራኪ የውበት ገፅታ፣ በፍልቅልቅ ፈገግታ በታጀበ ጉራዳ አፍንጫ፣ ሰበር ሰካ መጣሁ ደረስኩ በሚል አካሄድ፣ ደልደል ብሎ ውዝዋዜን ያስከተለ ዳሌ፣ እንገት ደፋ ተደርጐ በመሽኮርመም መልክ በሚላክ የስርቆት እይታ፣ ቅልጥፍጥፍ ያለ ከሰው የመግባባት ችሎታ ወይንም ነፃነት የተሞላበት በራስ መተማመን ባህርይ አለበለዚያም ሌሎች ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ። እነዚህ ለጊዜው በመጀመሪያ ፍንዳታቸው ሊያስበረግጉ፣ በመሀል ያለውን አየር ሊበጠብጡ እሳት ሊጭሩ ይችሉ ይሆናል። አስበርጋጊነታቸው ግን ጊዜያዊ ሆኖ በአንዳንድ መካከሻ ሊከስሙም ይችላሉ። ካልሆነም ነገሩ ከገፋም ወደፊት ሊገፉበት ይችላሉ። ቁም ነገሩ እነኚህ ስሜት ለኩሶ

በሚያደርጉት ጉዳዮች ላይ ብቻ ሳይሆን ወንዶቻችንና ሴቶቻችን ወደፊት አብሮ ለመኖር በሚያደርጉት ጥረት ላይ ጠንከር ያለ መመዘኛ ማበጀቱና እንዴት ተጣጥመው እንከን የለሽ ኑሮ ይኖራሉ የሚለው ላይ ነው። ለዚህም ኋላ ቀር በሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ሶሻላዊ፣ ባህላዊና አጓጉል ልምዶችና ችግሮች እስከአንገቷ ባጠለቋት አገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ እየኖሩ ይህን ማሰብ ዘበት ነው ሊባል ይችላል። ግን አይደለም ሁሉም በየፊናው የበኩሉን ጥረት ቢያደርግ በመጠኑም ቢሆን የሚያረካ ነገር ሊታይ ይችላል።

ይህ እኛ በሰለጠነው ዓለም ወይም ህብረተሰብ በምንኖረው ላይ እኔ የምለው ችግር ብዙ አይታይምና በአገራችን ሁኔታ ስላለው ሁኔታ እንይ።

አገራችን ወንዱን አይዞህ በርታ ጉሽ ወንድ ልጅ ድሮስ ለምን ተፈለገ ሁሉም ቦታ ላይ እንዲሰለፍ እንጂ! እየተባለ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ሁሉ ነገር ለወንድ የተባለ የሚመስል ነገር እናስተውላለን። ይህ ዓይነቱ አመለካከት ሴቷን ትንሽም ቢሆን ዝቅ ያደርጋታል። ህብረተሰቡ በአዋጅ ባያውቀውም በድርጊት እንደሚታየው ወንዱን ከፍ ሴቷን ደግሞ ወረድ አድርጉ ይመለከታል። እንግዲህ የዚህ ውጤት የሆኑት ተቃራኒ ፆታዎች ሲፈላለጉ ይህ የኖረ አብሮ ያደገውን አስተሳሰብ በየግል ጭንቅላታቸው ይዘው ስለሚቀርቡ የሚፈጥሩትን ግንኙነት በእኩል ደረጃ ለማዳበር ሳይቸገሩ አይቀሩም።

እስኪ ለዘመናዊ ትምህርት፣ ለከተማ ኑሮና ለዘመናዊ ገጠመኞች የተጋለጠውን ክፍል እንይ። መቼም ከተሜ ከተሆነ ያለውም የሌለውም ተቸግሮም ይሁን አቅሙ ፈቅዶለት ሴት ልጁንም ወንድ ልጁንም እኩል ትምህርት ቤት ይልካል። ግን ትምህርት በሚሰጠው ጠቀሜታ ላይና በሚያስከትለው የህይወት ለውጥ ላይ ያለው እምነት ሁለቱ ፆታዎች በአንድ መልክ አያዩትም። ለወንዱ ገና ከጠዋቱ ጀምሮ እንዲገባው እንዲረዳው የሚደረገው ካልተማረ ካልጉበዘ የወደፊቱ እንጀራው እንደሚጠብበት ሲሆን ሴቷ ልጅ ግን ራሷ ጉበዝ ሆና በፍላጉቷ በርትታ ከሰራች እሰየው ካለበለዚያ ግን ትምህርት ሁለተኛ አማራጪ እንደሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ስትነገር ታድጋለች።

ታዲያ በእንደዚህ ዓይነቱ በተዘበራረቀ አመለካከት ታንፀው የወጡ ወጣቶች በየፊናቸው ህይወትን ግብ ግብ ሲገጥሙ ከችግር አያመልጡም። አንዳንዱ ወንድ የሚፈልገው ብትማርም በተቻለ መጠን የእሱን የበላይነት ተቀብላ እሱ በሚያደርገው ድርጊት ላይ የማታቀርብ፣ ያለ አንተ ሰማይ ይደፋብኛል ብላ ማማው ሥር የምትንጋለለዋን ይመርጣል። ግን አንድ ቀን ነገር ማስተዋል የጀመረች ቀን የሚከተለውን እግዜር ይወቀው። ይህ ዓይነቱ ወንድ ደግሞ የምታስበውን የምታደርገውን አውቃ ነፃነቷን ጠብቃ መኖር ከምትፈልገዋ ጋር በአጋጣሚ ቢጋተር በተቻለ ፍጥነት ማንነቷን ከተረዳ በአለበት ሰፈር እንዳትደርስ ሊያርቃት ይሞክራል። በሌላው በኩል ደግሞ ወንዱን ከፍቅሩ፣ ቁልምጫው ጀምሮ እስከ ጥፊና ካልቾው ድረስ የሚወዱ ሴቶች አይጠፉም። እኔ ካልመታኝ የወደደኝ አይመስለኝም የሚሉም አሉ። በእርግጥ ፍቅር በተለያየ መልክ ሲገለፅ ላይደብርም፣ ላይሰለችም ይችላል። ግን ጥፊ ለምን? ታዲያ እንዲህ ዓይነቶቹ ሴቶች ከላይ ለተገለፀው ወንድ ሊስማሙ ይችላሉ። ግን የግኑኝነታቸው ዘለቄታዊነት ያጠራጥራል። መዝለቅ ካልቻሉ ደግሞ በሚያፈሯቸው ፍሬዎች ላይ ጉዳቱ የከፋ ስለሚሆን ገና ከጅምሩ ቢያስቡ መልካም ነው። ሌሎቹ ሴቶች ደግሞ የግል ነፃነታቸው ተጠብቆ አስፈላጊው ከበሬታ ሳይነፈጋቸው እነሱም በምላሻቸው አፀፋውን ከበሬታና ፍቅር ሰጥተው አንተ ትብስ፣ አንቺ ትብሽ ተባብለው የሚኖሩበትን ህይወት ይመርጣሉ። ግን ለእነዚህ ሴቶች እንዲህ ዓይነት ክብርና አስተሳሰብ ያለውን ወንድ የማግኘት ዕድላቸው ጥቂት ስለሆነ ሳይቸገሩ አይቀሩም። ለወንዱም እንዲህ ዓይነቷን ሴት ሲፈልግ ላታጋጥመው ትችላለች። ስለዚህ በተስፋ መቁረጥ ያገኘውን ሲያግበሰብስ አልባሌ ቦታ ላይ ሊገኝ ይችላል። ሴቷም ምርጫ በማጣት ያልሆነ ሰው ላይ ልትወድቅ ትችላለች። ለእነኚህ ደግሞ ሰኔና ሰኞ ይሁንላቸው ማለት ብቻ ነው።

ከላይ የተጠቀሱት በአብዛኛው በወንዶችና በሴቶች የመምረጫ ሚዛን ላይ በባህሪና የሚኖሩበት ህብረተሰብ የአስተሳሰብ የዕድገት ደረጃ ባስከተለው ተፅዕና በአብዛኛው ሲከሰት የተስተዋለውን ነው። ከአገራችን ሁኔታ ብንመለከት፣ አገሪቱን የወረራት ድህነት ደግሞ ያመጣው ሌላ ጣጣ አለ። ይኸውም አንዳንዶቹ ወንዶችና ሴቶች ሁሉንም ነገር ከማቴሪያላዊ ነገር ጋር ማዛመዳቸው ነው። በተቻለ መጠን ሴቷ ማግኘት የምትፈልገው ወንድ ጥሩ ቤት፣ ጥሩ መኪና፣ ከየትኛውም ደረጃ እንደ ልብ ሊበትን የሚችል ካፒታል ያለው ሲሆን ለዚያ ደግሞ በጥሩ ሁኔታ በእኛ ሀገር የተመቻቸው በንግድ ዓለም ላይ የተሰማራው ስለሆነ ነጋዴው ለስንቱ ሴት እንደሚሆን እንጃ። ወንዱ ደግሞ ጥሩ ደመወዝ ያላት ቢቻል ከእሱ ከመገናኘቷ በፊት የቤት ማስሪቱን ነገር የተያያዘችው፣ ከተቻለም የአንዲት ቮልስዋገንም ቢሆን ባለቤት ብትሆን አይጠላም። ወይንም ደግሞ ከየትም ታምጣው ከየትም ቢፈልጉ አባቷ ያውርሷት ወፍራም ገንዘብ ያላት ጋ መጠጋቱን ይመርጣል። ይኸውም ወደፊት ለሚመሰረተው ትዳር ተብዬው ብዙ ሳይጨነቅና ሳይቸገር መኖር እንዲያስችለው ሲሆን የእሱ ብጤዋም ፍላጉቷ ይኸው ነው። ችግሩ ግን ሀብት ሰው ሠርቶ፣ ጥሮ ግሮ እንዳመጣው ሳይሆን ሲጠፋ ጊዜ የማይወስድበት መሆኑ ነው። ታዲያ ያኔ ይህ በንብረት ላይ ብቻ የተመሰረተ ትዳርም አብሮ ቡን ይላል። ፍዳው ለእነኚያ በንዋየ ፍቅር ከተጠመዱ እናትና አባት ለተፈጠሩ ልጆች ጭምር ይደርሳል። እንዲሁም አሁን ካለንበት የውጭው ኑሮ አንፃር ደግሞ ስንመለከተው ዛሬ ሴትና ወንዱ የሚፈላለጉት በአብዛኛው ከጥቅም አንፃር ነው። ሴቷ የምትሰራበት ቦታ መጀመሪያ ያጠናል፣ ፓርኪንግ ሎት ውስጥ የምትሰራ ከሆነ ወይንም ከሳምንት ቼክ ገቢዋ ሌላ በሆነ መንገድ የተለየ ገንዘብ የምታመጣ ዓይነት ከሆነ ፍቅሩ ይኑርም አይኑርም አይኑን ሳያሽ ማሻሸት ይጀምራል። ሴቷም ቢሆን የምታየው ገቢውን ነው ጥሩ ገቢ ካለው አጥምዳ የራሷ ታደርገዋለች። ሌላው ደግሞ ለወረቀት ሲባል የሚደረግ ግኑኝነት ነው። ከሁለት አንዳቸው የመኖሪያ ፈቃድ ወይም የስራ ፈቃድ ከሌላቸው አንዳቸው በአንደኛቸው ላይ ተንጠላጥለው ይህቺን ጊዜ ሊገኙት ይፈልጋሉና ይህቺን ነገር ከስር ጀምረው ያጠናሉ ይጠይቃሉ ወረቀት ይመረምራሉ። የሚያዋጣቸው መስሎ ከታያቸው በፍቅር የወደቁ መስለው ለመታየት ጥረት ያደርጋሉ። የማይሆኑት ነገር

ስለማይኖር ያንን ሰው ያሸንፋሉ። ከዛ እንፈራረም ነዋ! ታድያ ሁሉም ነገር ከተሳካላቸው በኋላ አብሮ መኖር ሲጀምሩ ሁሉም ነገር ይፋ ይወጣና "በሬ ሆይ ሞዱን አይተህ ገደሉን ሳታይ" ሆኖ በፀባይም በምኑም መጣጣሙ ይጠፋና መነጣነጥ ይጀምራሉ። እርስ በርስም በነገር መነቋቆር፤ ለጓደኛ ማማት፤ ድሮውንም እኔ አልፈለግኩም ነበር በግድ ተይገፔ ነው ... የመሳሰሉት ሮሮዎች ይከተላሉ። ወዲያው አንዱ የባሰበት ክፍል ሻንጣውን ይዞ ይወጣል። ደግነቱ እዚህ ልጅ ለመውለድ ሁኔታውም ስለማያመች አይቸኮልምና ልጆች ላይቸገሩ ይችላሉ። ነገር ግን ለሴቱም ሆነ ለወንዱ ህብረተሰቡ የሚሰጣቸው ግምት ጥሩ ስለማይሆን መጉዳታቸው አይቀርም።

እንግዲህ እነኚህ ሁሉ ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች መጀመሪያ ራስን ካለመመርመር የሚፈልጉትን ካለማወቅ፤ በንዋይ ፍቅር ከመጠመድ፤ ከግል ጥቅም ስሜት የመነጩ ስለሆኑ እነዚህን ለማስተካከል ወንዱም ሴቱም በየበኩሉ መጣር ይኖርበታል። የሚፈጠረው ትዳር የጋራ በመሆኑ ልጆችም የጋራ በመሆናቸው ለዚህ ትዳር መቃናት ሴቱም ወንዱም በጋራ ማሰብ ይኖርባቸዋል። የእነሱ ንዝህላልነት በእነሱ ቤት ብቻ አያከትምም። አልፎ ተርፎ ወደ አካባቢ ችግርነት ስለሚሸጋገር ለራስ ተረብሾ ሌላውንም ከመረበሽ ከጠዋቱ ምርጫን ማስተካከል ተገቢ ነው። ሴቷ ን አንቺ ምን ታውቂያለሽ አርፈሽ ቁጭ በይ! የሚለውን ኃይለ ቃል ከመናገር በፊት፤ ሴቷም እንደ ወንዱ ማሰብ፤ ሀሳቧን መግለፅ፤ ባልተስማማችበት ነገር ላይ መቃወም መቻሏን መገንዘብ ተገቢ ነው። ወንዱም ቢሆን ከእኔ በላይ ለአሳር፤ እኔ ለምን ተነከቼ ተደፍሬ የሚለውን የትዕቢት መንፈስ ትንሽ አስተንፍሶ በቅጡ ማሰብ ቢጀምር ላማረ፣ ቆንጆ ግንኙነት መሰረት ይሆናል። ለጊዜያዊ ጥቅማ ጥቅም የሚደረገውንም ሩጫ ወደ ጐን ትቶ ችግርን ግልፅ በግልፅ ተነጋግሮ በብልጥነት ሳይሆን በመተሳሰብ ሁኔታውን ለማስተካከል መሞከሩ ጥሩ ነው ባይ ነኝ። ለሁለቱም ብርታቱን ሰጥቶ በመግባባት፤ በመቻቻል፤ በመተሳሰብ የሞላ ፍቅር ላይ ግንኙነት ሲጀምር ውጤቱ ያምራል፤ ልጆችም ሳይሳቀቁ ያድጋሉ። ህብረተሰቡም ለሰላማዊ ህይወት መሠረት ይጥላል። ስለዚህ ይህ ትልቅ ኃላፊነት የሴቱም የወንዱም ስለሆነ ቢታሰብበት መልካም ነው።

## ቋንቋችን

# የሥነ ቃል ሀብታችን

(ከዝግጅት ክፍሉ የተጠናቀረ)

ሥነ ቃል በአፍ እየተነገረ ከትውልድ ትውልድ ሲወራረስ የቆየ ትውፊታዊ የቋንቋ ሀብት ነው። ስለሆነም ህዝብ ለቋንቋው አነጋገር ዘይቤና ስልት ባለቤት ነው። ስለዚህም በሚናገረው ልሳን በየዕለቱ የኑሮው እንቅስቃሴ ውስጥ በየአጋጣሚው ድርጊትና አፈጻጸም ላይ ተመስርቶ ልዩ ልዩ የሥነ ቃል ዘይቤዎችን ይፈጥራል። በዚህ ረገድ ሰዎች ቁጭ ብለው ሲያወጉ ሳሉ ከሚያውቋቸው ቃላትና ሐረጐች ቅንብር ማለፊያ ሥነ ቃልን በቀላሉ ሳይቸገሩበት ወርወር ያደርጋሉ። ያ ሥነ ቃል በአንክሮ የሚቀበሉት ምክር ወይም ፈገግ እያሰኘ ጥርስን ለሳቅ የሚጋብዝ ሊሆን ይችላል። እዚህ ላይ እንደ አለቃ ገብረሐና ያሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ። ፈረንጆች እንዲህ ያሉትን ሰዎች ዊቲ (WITTY) ይሏቸዋል። ማለትም ብሩህና ቀልጣፋ አዕምሮ ያላቸውና ወዲያው የፈለጉትን ጣል የሚያደርጉ፣ ምናልባትም በእኛ አነጋገር አያልቅበት እንደማለት ሊሆን ይችላል። ሽማግሌዎች ለእርቅ ለግልግል፤ ለምክር፤ ለምርቃት፤ ለሠርግና ለምላሽ ወይንም ለአፈርሳታ ሸንጐ በተቀመጡ ጊዜ አያሌ ሥነ ቃል ይሰነዝራሉ። አዳዲስ ምሳሌያዊ አነጋገሮችም ከዚህ ይገኛል። ነባሮችም ይዳብራሉ። በቀድሞ ጊዜ በባህሉ የችሎት አደባባይ ላይ ዳኛው ከፊት ለፊት ከወንበሩ ተሰይመው ከዛፍ ሥር ቁጭ ካሉ በኋላ ከሳሽና ተከሳሽ ዘንጋቸውን ይዘው ኩታቸውን አደግድገው እስጥ አገባ እያሉ ውረድ ሲያወርዱ፣ ለሥነ ቃል እድገት ሰፊ ድርሻ ሰጥቶታል። ለምሳሌም ያህል ከሳሽ ተከሳሽን በነገር ሲነካካው፤

በላ ልበልሃ
ያጤ ሥርዓቱን የመሠረቱን
አልናገርም ሐሰቱን
ሁሌ እውነት እውነቱን
ላምህ ብትወልድ ዛጐላ
ሚስትህ ብትለብስ ነጠላ
አንተ ብትውላ እጥላ ይለዋል። ተከሳሽም ፈጣን በሆነ ዘዴ መልሶ–

በላ ልበልሃ
ያጤ ሥርዓቱን የመሰረቱን
አልናገርም ሐሰቱን
ሁሌ እውነት እውነቱን
ላሜ ብትወልድ ዛጐላ
አውራውን አስመስል ብላ
ሚስቴ ብትለብስ ነጠላ
ቀን እስቲያልፍ ብላ
እኔ ብውል ጥላ
ያንተን ብጤ ነገረኛ ብጠላ! ይለዋል። አነጋገራቸው ችሎቱንም አድናቆት ላይ ይጥለዋል።

ከዚህም በስተቀር አውሬ አዳኝ ዝሆኑን፣ ቀጭኔ ውን፤ አውራሪሱን ወይም አንበሳ ገሎ ለመቀባትና ጀግና ለመባል መልካ ተሻግሮ፤ ቆንጥር ለቆንጥር ዞሮ ያገኘውን ገሎ ሲመለስ፣ እርሱ የሚያሰማው ቀረርቶና ሽለላ ሚስቱ በጐረቤት ሴቶች ታጅባ የሚዘፍኑት ዘፈን ሁሉ ሥነ ቃልን ያካተተ ነው። ጀግናው ጦር ሜዳ ሄዶ አነጣጥሮ ተኩሶ ጠላቱን ሲደፋው፣ ጉራዴውን መዞ በጨበጣ ገብቶ ሲያወራርደውና ፉከራ ሲያሰማ ሥነ ቃሉን ያጐርፈዋል።

አስለቃሽ ሴቱን ዙሪያዋ አስከብባ የሟቹን ታሪክ እያጣቀሰች የምትገጥመው ግጥም፣ የምታዜመው ዜማ እንኳን የሚያውቁትን የማያውቁትንም እንባ በእንባ

ታራጣለች። ገበሬው ማለዳ በሬዎቹን ጠምዶ ራሱንም በሬዎቹንም እያነሳሳና እያንጉራጉረ የሚያፈልቀው ሥነ ቃል ቀላል አይደለም። የቅኔ መምህሩ ከወንበራቸው ሆነው በመቶ የሚቆጠሩ ተማሪዎችን ከፊታቸው አስቀምጠው "ንሳ ተቀበል" እያሉ ተማሪውን የሚመሩበት ቅኔ እርሱም ተመሳጥሮ የሚሰጠው መልስ የሥነ ቃል ሀብት ነው።

ማለፊያ ጥምጥሙን ጉብ አድርጉ ሐር የመሰለ ካባውን ደርቦ፣ ባለ አሳር አውታር በገናውን በልቡ ላይ አንተርሶ ራሱን ወደ አርያም አቅንቶ በሚመስጥ መንፈሳዊ ዜማ፣

እኔ ሰው ነው ብዬ ስመለከተው
መድኃኒያለም ኑሯል የተሰቀለው
ምነው ዘመዴ ምነው! እያለ የሚያንቆረቁረው ዜማ ለሥነ ቃል ብልጽግና አንዱ መንገድ ሆኖ ቆይቷል።

ሥነ ቃል በተረትና በምሳሌ ይዘቱ ህፃናትን በትምህርት ለማበልፀግ ሰፊ ድርሻ አለው። ሥነ ቃል በሙዚቃም ሆነ በፊልም ሊቀነባበርና ጠቀሜታ ሊሰጥ ይችላል። እንዲያው ብቻ ከታሰበበት ሥነ ቃል ሁለገብ የሥነ ጸሁፍ ሀብት ነው ማለቱ ይበቃል። ይበቃል ብቻ ብለን ከማለፋችን በፊት ከየስነ ቃሉ ዘርፍ ጥቂት እናስነብባችሁ።

<u>ሰምና ወርቅ አማርኛ ቅኔ</u>
ላም ገዝቼ ጥገት
እጠጣ ብዬ ወተት
ቅሉ ተሰብሮ አዝናለሁ
በምን እልባታለሁ።
ራሴን አሞኝ እያያችሁ
ምነው ሰከረ ትላላችሁ
አሁን ማን ሰጠኝ ለእኔ ጠጅ
እንጀራ አዞረኝ እንጂ።

<u>ከሥራ ግጥሞች (ግብርና)</u>
የተሳካለት ሞፈር ቀንበሩ
ሰው የሚቀብር ይመስላል ፈሩ
አያ ምን ትወደድ በሬ ምን ትወደድ
የጉሽን መዋያ ስታደርገው መንገድ
በሰኔ ጣይ ፈራ በሐምሌ ዝናብ ፈራ
ልጄ እንጀራ ሲለው በጅብ አስፈራራ

<u>የብሶት ግጥም</u>
ልብሴንም ወሰደው ለበሰው እርዘኛ
በሬዬንም ነዳው አረደው ነፍጠኛ
እህሉንም ዘረፈው በላው ቀለብተኛ
ንጉሥ የቀረዎ ጥቂት አማርኛ
ምነው ሆድ አይዘርፉ አርፌ እንዳልተኛ

<u>የሞት እንጉርጉሮ</u>
በእንስራ በገንቦ ቀዳሁ ተጨንቄ
ባላፈር መሆኑን እኔ የት አውቄ (ሚስት)
ትላንትና ማታ ዕድሜ ብንቋጠር
ቀድሞም እናቴን ነው እግብቻት የነበር (ባል)

<u>የዘፈን ግጥሞች</u>
የጥርስዋ ንቅሳት ያንገትዋ ሙስና
ዓርብ ሮብ ያስኬዳል እንኳን ሐሙስና።

ሆዴን እንደራበኝ እንደሞረሞረኝ
ከጠገበው ጋራ ልሞት ነው መሰለኝ።

በሀብታም ተዝካር ቤት ውስጥ ታላቅና ታናሹ፣ ሽንጥና ፍርንባው በወሳንሳ እየተያዘ ለቁርጥ ሲቀርብ ስግብግብ የቆሎ ተማሪ ከያይነቱ ጉመድ ጉመድ እያደረገ ወደ አኩፋዳው ይከታል። ማዶ ለማዶ በትዝብት ዓይን የተመለከቱት ሽማግሌ፦

"ተሚ ሆዱን አሞታል፣
እየቆረጠ ያስቀምጠዋል
ልንገረው አንድ መላ፣
ትንሽ ቆርጦ እንዲበላ" በማለት ከአልጠግብ ባይነቱ መልሰውታል።

ፍቅሬ ብሬ የተባለ ሞገደኛ ባል ያገባችና ዱላ እራቷ የሆነችው ሴትዮ፦

"እድናለሁ ብዬ ለታቦት ተሳልሁ፣
ሞቴንም እስቤ ከፈንም አሠራሁ።
ዕድሌ ጠምሞ ላንዱም አልበቃሁ፣
በፍቅሩ ተይዤ እንዳለሁ አለሁ። ስትል ብሶቷን ገልጣለች።

ያለ አቻ ጋብቻ እየሆነበት ከትዳር ተራቁቶ ዕድሜውን በብቸኝነት የሚገፋ ቁም ጸሐፊ፦

"ከፊደል ሆሄያት እየተሟገትሁ፣
ጋብቻ ጠፍቶብኝ እባዝናለሁ።
እባካችሁ ሰዎች ፍጠሩልኝ መላ፣
የሰው ዘር መናቁ አይበጅም ለኋላ" ሲል ዛቻ ጭምር አስተጋብቷል፣ በኅብረ ቅኔ መልዕክቱ።

ውልታ የተባለች አመንዝራ ሴት፣ እግረ ሰላላ ከሆነ ወንድ ጋር ተዋዳ እየደገሰች ስታበላ በታየች ጊዜ፦

"ከቤተክሲያን በታች ቤቷን አስርታ፣
በግና ፍየሉን በአፍላል አስገንፍታ፣
ወዳጅ ጉረቤቷን ግብር አስገብታ፣
አንድ እግር ደረሳት እሜቴ ውልታ" ተብሎ ከታዛቢ ተገጥሞባታል።

በዋድላ ቅኔ በቅጽል ሐረጉች የተሳሰረ፣ በታሪክና በነባር ግሶች የተጣመረ ነው። በቆጠራው ላይ ላልቆየና ጠባዩን ላልለመደው ደቀ መዝሙር ምስጢሩን ፈትቶ ለማወቅ ይቅርና ንባቡን እንኳን ሙሉ በሙሉ ለማጤን ያዳግተዋል። ስለዚህም፦

"ዓመለኛ ሚስቱ ስታስቸግረው፣
እንደ ዋድላ ቅኔ መፍታት ተሳነው" ተብሏል።

ዜማ በእንጀራ፣ ቅኔ በወጥ ይመሰላል። እንጀራና ወጡን አዋህዶ ያልያዘ የቆሎ ተማሪ 'ግማሹን ተቀብታ' እንደሚባለው መሆኑ አይቀርም። በዚህም የተነሳ፦

"እንጀራ ዜማውን ቆጥበህ ያዘው፣
በደረቁ በልተህ እንዳትጨርሰው
ማጠፊጫው ቅኔ ሰከን ያለ ወጥ፣
ተጨልፎ አያልቅም በቅጡ ሰልቅጥ" የሚል ምክር መስጠቱ ይነገራል።

ሰውየው ውሽማ ወዶ በፍቅር ስለከነፈ ማታ ማታ

ራቱን ከበላ በኋላ የእህል ክምር እጠብቃለሁ እያለ ሚስቱን በማታተለል አዳሩ ውጭ ሆነ ታዲያ ሌሊት ከክምሩ ስር ውሽማውን ይዞ እንደተኛ ክምሩ ይናድባቸውና ሁለቱም ይሞታሉ። ሚስት ቀደም ሲልም የባልዋን መወስለት ጠርጥራ ኖሮ ስታለቅስለት በግጥም እንዲህ አለች፦

የሰራኸው ስራ፣ የሰራኸው በደል
የፈጸምከው ወንጀል፣ አለው እንጂ ነገር
እህል መድኃኒቱ መች ይገድልህ ነበር።

አያ ሱምቢ የሚባሉ ሀብታም ገበሬ ሸዋ ከደገማው ስፍራ ይኖሩ ነበር። ለማኙ ሁሉ በዝና ያውቃቸዋል። እጀ ሰፊ ናቸው። አንዱ አልጠግብ ባይ አሚና (ላሊበላ) በደረቅ ውድቅት ከቤታቸው በየቀኑ እየሄደ 'ወየው ዓለም' በማለት እንቅልፍና ጤና ሲያሳጣቸው ጊዜ ዳውላውን ባቄላ በጥጃ ስልቻ አስሞልተው ተሸክሞ እንዲወስድ ይፈቅዱለታል። ላሊበላው ሆዬ የአፍ ልፍለፋ እንጂ ጉልበት ስንኩል በመሆኑ ማንቃንቅ አቅቶት ከስልቻው ጋር መሬት ለመሬት እየተንከባለለ፦

"ሚካኤልም እርዳ፣ ጊዮርጊስም እርዳ፣
የባቄላ ሱምቢ እንደ እምቧይ ይፈንዳ"

ብሏቸው ነጎደ ይባላል።

# ታሪክና ምሣሌ

(ከመጋቢ አዕላፍ መክብብ አጥናው)

ታሪካዊ ትምህርት በምሳሌ እየጻፉ ብዙ መጻህፍትን ደርሰው በማሳተም የኢትዮጵያን ህዝብና ልጆቹን ሲያስተምሩ የኖሩ አንጋፋውና ስመ ጥሩው ኢትዮጵያዊ ደራሲ ከበደ ሚካኤል በ82 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት መለያታቸው ስለተሰማ በተከታታይ ይቀርብ የነበረውን ታሪክና ምሳሌ ትምህርታዊ ዝግጅት ለሌላ ጊዜ አስተላልፈን በርሱ ፋንታ ስለደራሲ ከበደ ሚካኤል ስራዎችና ለእሳቸው ታላቅ ሙያ የተነገረ አጭር ቅኔ ይቀርባል። በመጨረሻም ላይ ራሳቸው ደራሲ ከበደ ሚካኤል ከጻፉት መድበል ቅኔ የተጠቀሱና ጥልቅ ስሜትን የሚቀሰቅሱ ቅኔዎች ይከተላሉ።

የዚህ ቅኔ አዘጋጅ ከ40 ዓመት በፊት የደራሲ ከበደ ሚካኤልን መጻህፍት በማንበብ መጻህፍትን የማፍቀር ሱስ አሳድረውበት 40 ዓመት ሙሉ ያለማቋረጥ መጻህፍቶችን ማንበብ እንደቀጠለ የሚገኝ ሽማግሌ ነው።

## የደራሲ ከበደ ሚካኤል ሥራዎች

በኢትዮጵያ የስነ ፅሁፍ ታሪክ ውስጥ ታላቅ ስፍራ ያላቸውና ለወጣት ደራስያን አርአያ ከሆኑት ፋና ወጊ ደራሲዎቻችን መካከል ከበደ ሚካኤል አንዱ ናቸው። አቶ ከበደ ሚካኤል እንደተናገሩት "እኔ ከመጻፌ በፊት በጣም ብዙ አንብቤያለሁ። እንዲያውም ንባቤን የጀመርኩት ከጥንት የግሪክ ስልጣኔ ጀምሮ ተጽፈው የነበሩትን ሊትሬቸሮች ፈልጌ በማንበብ ነው"

በርግጥም የደራሲ ከበደ ሚካኤል ግጥሞች ቅንያዊና የማይሞት መልዕክት ያዘሉ ናቸው። በጋዜጣም ሆነ በመፅሐፍ ያወጧቸው በርካታ ግጥሞቻቸው በወል ግጥም ስርዓት የተዋቀሩና መሰረታዊ ቁም ነገር ያዘሉ ናቸው። ደራሲ ከበደ ሚካኤል ባበረከቱት ታላቅ አስተዋጽኦ ለመጀመሪያው 1957ቱ የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ሽልማት ድርጅት የአማርኛ ስነ-ፅሁፍ ተሸላሚነት አብቅቷቸዋል። ባለፈው ዓመት ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የክብር ዶክትሬት ድግሪያቸውን ከመቀበላቸው ባሻገር በስማቸው የልማት ድርጅት ተሰይሟል። ደራሲ ከበደ ሚካኤል ስለ ደራሲ ህይወት በአንድ ወቅት ሲናገሩ "የስነፅሁፍ ህይወትና የደራሲ ውሎ እንዴት ያረካል መሰለህ፣ የራስህን እውነተኛ ዓለም ፈጥሮ በሰላም መኖር እኮ ነው።" ብለዋል።

ደራሲ ከበደ ሚካኤል ካበረከቱልን ዋቢ መፅሐፍት መካከል ፦ ታላላቅ ሰዎች፣ የስልጣኔ አየር፣ የዓለም ታሪክ፣ ትልቁ እስክንድር፣ የኢትዮጵያ የጥንት ስዕሎች፣ የዕውቀት ብልጭታ፣ የቅኔ ውበት፣ አኒባል፣ ሮሜውና ዡልየት፣ ከይቅርታ በላይ፣ ብርሐነ ህሊና፣ የትንቢት ቀጠሮ፣ ሥልጣኔ ማለት ምንድነች?፣ ኢትዮጵያዊና ምዕራባዊ ሥልጣኔ፣ ካሌብ፣ የቅጣት ማዕበል፣ ጃፓን እንዴት ሰለጠነች? የሚሉት ይገኙበታል።

ከ3 ሺህ በላይ መፅሐፍት ያነበቡትና የ450 መፅሐፍት ደራሲና ተርጓሚ የጥበብ አባታችን ታላቁ ደራሲ ከበደ ሚካኤል ከአንድ ዓመት በፊት በጠና ታመው ጳውሎስ ሆስፒታል በህክምና ላይ ሳሉ "ለምን አንሶላ ለብሰው አይተኙም?" ብሎ አንድ ጋዜጠኛ ሲጠይቃቸው "ባለቤቴ ከሞተችበት ጊዜ አንስቶ ይህን ያህል ዓመት አንሶላ ለብሼ አላውቅም" በማለታቸው አግራሞትን ፈጥሮ ነበር።

ደራሲ ከበደ ሚካኤል በ82 ዓመታቸው በህይወት ቢለዩንም እንደነሶቅራጥስ፣ እንደነ ሼክስፒር፣ እንደነ በዓሉ ግርማ... ስራዎቻቸው ለዘላለም ከኢትዮጵያና ከኢትዮጵያውያን የሚለዩ አይደለም።

ስለደራሲ ከበደ ሚካኤል ዕረፍት
የተነገረ ቅኔ

የጨው ገደል ሲናድ ሞኝ ይስቃል አሉ
ብልሆች ግን አይተው በብርቱ ያዝናሉ
እንደ አንድ ሰው መርዶ አይደለም በውነት
ኅልፈተ ዓለም ነው የከበደ ሞት።

በብርዕ አንደበት እየተናገረ
ከቅኔ አማልክት አንዱ የነበረ
ወገኑን ያኮራ አገር ያስከበረ
የብረት ምሶሶው ከበደ ሚካኤል
እንዴት ተሰበረ?

ታሪክን በታሪክ እያነፃፀረ
ቅኔውን በቅኔ እያመሳጠረ
የሥነ ጽሑፍን ልደት ያበሰረ
ኢትዮጵያን ጠንቅቆ ያውቅ የነበረ
ከነባር ምስክር እንግዲህ ማን ቀረ?
ግን ስንመለከት የድርሳኑን መድበል
አልሞተም ህያው ነው ከበደ ሚካኤል።

ከበደ ሚካኤል ÷ ሚካኤል የሰው ዘር
የህይወትን መንገድ ታውቀው ስለነበር
ለኢትዮጵያ አለኝታ ሆነሃት ለመኖር
ምነው ከኤልያስ ዕድሜ ትንሽ ብትበደር?

የምሳሌን ትምህርት ጠንቅቆ የሚያውቀው
ከበደ ሚካኤል የጥበብ ቁልፍ ነው

ኧረ ለመሆኑ በሞት ስትለይ
ብዕርህም ከአንተ ጋር ተቀበረ ወይ?
ከበደ ሚካኤል ተጓዥ መንገደኛ
ላትመለስ ነወይ ከእንግዲህ ወደ እኛ?

እንግዲህ ደህና ሁን በላይኛው ቦታ
ለሚኖሩት ሁሉ የማክበር ሰላምታ
እንድታቀርብልን ለሁሉም ንገር
አደራ በሰማይ አደራ በምድር!!

ከደራሲ ከበደ ሚካኤል መድብል ቅኔ
የተጠቀሱ ኃይለ ቃላት

"በእጅ የተበተቡት ተንኩል ዞሮ ዞሮ
ማጋለጡ አይቀርም እጅና እግርን አስሮ
መጽሐፉም ይለናል ሲያስተምረን ጥበብ
ብልህ ሁን እንደ እባብ፥ የዋህ እንደ ዕርግብ።
* * * *

መሬት ሁሉን ነገር ተሸክማ ስትኖር
የሚከብዳት የለም ከሰነፍ ሰው በቀር
መታገል ያልቻለ ልቡ እየታከተ
በገዛ እጁ ወድቆ በቁሙ የሞተ
የሚያነሳው የለም በፍቅር በዕርዳታ
በዚህች በምድር ላይ ፍጡር ካልበረታ
ጥንቱን አልተሰራም ለሰነፎች ቦታ።
* * * *

መዶሻና ሞረድ ይፈልጋል ገና
ድንጋይ ነው ብረት ነው የሰዎች ልቡና
ሁልጊዜ ለክፋት መንፈሱ የሚያደላ
ተንኩልን የሚወድ ፍቅርን የሚጠላ
ደግ ለዋሉለት ክፋት የመለሰ
ይሙት በኅሊናው እየተወቀሰ።
* * * *

መስዋዕት እየሆነ ደካማ ለብርቱ
ያልታደለ ድኃ ይጠፋል በከንቱ
ለምን ትልቅ ዓሣ ትንሹን ይውጣል
ወርካ ከሰንበሌጥ በብዙ ይበልጣል
በወደቀ ጊዜ ሁሉን ያዳምጣል።
* * * *

ደግና ክፉውን እያደባለቀ
መንፈሱ ለይቶ ፍርድን ካላወቀ
ድካሙ ከሆነ እስኪሞላ ከርሱ
ልፋቱም ከሆነ ለጌጡ ለልብሱ
ካላቀረበለት ኅሊናው ወቀሳ
በምኑ ይበልጣል የሰው ልጅ ከእንስሳ?
* * * *

ደግና ክፉውን ጨርሶ ያላየ
ከኢምንት ያልወጣ ከዓለም የተለየ
በዚህች ክፉ ዓለም ላይ የሚሰራው ወንጀል
እንደምን ያለ ግፍ እንዴት ያለ በደል
እንዴት ያለ ውርደት ህዝብ እንደሚቀበል
ስንቱን መጥፎ ነገር የጥፋት ዋዜማ
በዓይኖቹ ያላየ በጆሮው ያልሰማ
የሰዎችን ሀዘን የሰዎችን ለቅሶ
ተካፋይ ያልሆነ በፍጹም ጨርሶ
የመፈጠር ዕጣ ጽዋ ያልደረሰው
ምንኛ ታደለ ያልተወለደ ሰው!!
* * * *

ሣይንስን የሚያህል መሣሪያ ጨብጦ
ካለፉት ትውልዶች ካልተገኘ በልጦ
በከንቱ ከቀረ ይኸ ታላቅ ተስፋ
ይገባል የአዳም ዘር ጨርሶ ሊጠፋ
ቦታውን በመልቀቅ እርሱ ተወግዶ
ብትሆን ይሻላል ይህች መሬት ባዶ
ጥበብም ያለ ሰው ሰውም ያለ ጥበብ
ለመኖር አይችሉም አንዱ በአንዱ ሰበብ
እየተረዳዱ ካልተደጋገፉ
ያሰጋል ሁለቱም አብረው እንዳይጠፉ።
* * * *

አማኑኤል ወርዶ የሰው ሥጋ ለብሶ
ወንጌልን ቢያስተምር ኦሪትን አድሶ
ያ ሁሉ መከራ ሆነና በከንቱ
በኃጢያቱም ሆነ በአመፅ በክፋቱ
ብሶበታል እንጂ ብትመለከቱ
ምንም አልተሻለው የሰው ዘር ክፋቱ።
* * * *

ሰይፍና ወረቀት ተጣልተው ቢማቱ
ተቀድዶ ወደቀ አሉኝ ወረቀቱ
ይኸው ታዲያ ምነው የወንጌል ብራና
ብዙ ሰይፍ ሰብሮ ይኖራል በደህና!!

## (ስለአኒባል የካርታጎ ጀግና ደራሲ ከበደ ሚካኤል የተናገሩት ቅኔ)

"አለመተባበር የሚያመጣው ዕዳ
መንግሥት እንደሚፈርስ ህዝብ እንደሚጐዳ
ለዓለም ሰዎች ሁሉ ዞራችሁ አስተምሩ
መስማት ለሚፈልግ ለቅን ሰው ንገሩ
ጠፊ ነው በኋቸው ህዝብ ካልተስማማ
ዓይን ያለው ያስተውል ጆሮ ያለው ይስማ
ኅብረት ስለጠፋ በብስጭት ነድዶ
በሰው አገር ሞተ አኒባል ተሰድዶ
አሳቡ ግን ሰፊ ነበረ በኋቸው
የካርታጎ ታሪክ ትምህርት ይሁናቸው
አለቀ ስለ እንቺ የሚኖረኝ በጎ
ደህና ሁኝ አገሬ ደህና ሁኝ ካርታጎ
* * * *

ጠንካራው ምሶሶ ዝግባው ተሰበረ
ቅጥራችን ፈረሰ ምሽግ የነበረ
አገሩን አድርጎ ሰው የሌላት ወና

ምትክ የሌለው ሰው ሞተ ዛሬ ገና
አወይ የእኛ ነገር በቃ ተፈጸመ
የካርታጎ ፀሀይ ጠለቀች ጨለመ።

* * * *

ለሁሉም ጊዜ አለው ብሏል ሰሎሞን
እጠይቀው ነበር በተገናኘን
ሞት የሚሞትበት ጊዜው መች ይሆን?
የበረዶ ፍሬ ናት የእኛ ህይወት
ደመና ከስማይ የወረወራት
ሥጋ ከለበሰ ሰው ዓለም ላይ መጥቶ
በረዶም ከሄደ ከደመና ወጥቶ
ወደ አፈር መግባቱ የማይቀር ነው ከቶ።
በላይኛው መዝገብ በእውነት ከተጻፈ
የምድሩ ቀሪ ነው እየተሸነፈ።

# የግጥም ጉባኤ

## ወቀሳ ለ"አያ ኩራቴ"

ከልሳኑ ሥምረት (ሴንት ሉዊስ)

ረብተህ ትረባናለህ
ሰባራ ቋንጃችንን ፥ ስንል ትጠግናለህ
በጉልበታችን መዳህ ፥ ስይላችን የተሰማህ
እያልንህ ደመላሻችን ፥ በቅንነት ስናምንህ
ለምን ለቀበሮች ሰጠኸን ፥
ለተኩላዎች አጋልጠህ።

ይሁንስ ብሎ ሀሊናህ ፥ ያ የምሁር ትንታኔህ
ከሌሎች ተዘነቀ ፥ የኋልዮሽ ተንቁቀቀ፣
ለምን ጉድጓድ ጠለቀ ፥ መብትን በንፍጥ ለነጠቀ
አንድነትን ለሰረቀ ፥ እንዴት ብላሽ አፈለቀ?

"አያ ኩራቴ" ብለንህ ፥ ረብተህ ታረባናለህ
በማለት ስንፎክርልህ ፥ ያ የምሁር ቋንቋህ
ኃይልን በኃይል ለነጠቀ ፥ ምልዐቱን ላማቀቀ
ጦርን ለነቀነቀ ፥ ተንደርድሮ ለሰበቀ
ምነው ወኔህ ደቀቀ ፥ እንዴት ብላሽ አፈለቀ!!

ሊቀድ ነው እኮ ጉህ ፥
"አያ ኩራቴ" እያልንህ ...
የነገርህ ሁሉ ትምተማ ፥ ፈራሽ ነገር ጠማማ
ለወገን የማይስማማ ፥ የማይላመጥ ጉማ።

እንዴት "አያ ኩራቴ" ፥ በዚህ የጣር ዐበቅቴ
እንደየዋህ ዐመቴ ፥ ደግሞ ልታሳውረኝ
ምነው እንዲህ ነካካኸኝ ፥ ብርኃኔን ልታስነሳኝ
እንደጉድፍ ወተቴ ፥ እንዴት "አያ ኩራቴ"!!

የልጆቼን ወተት መግዣ ፥ ገብሬ እንደመጋዣ!
እንዲሳካ ሐጃችን ፥ እንዲሰራ ቤታችን።
ባትጨነቅ ለህይወቴ ፥ ባትነደግጥ ለንብረቴ
ሳስተህ እንኳ ለህገሬ ፥ ለተቀበረባት እትብቴ
ለመከረኛዋ እናቴ ፥ እንዴት "አያ ኩራቴ"።

ልትፈነጥቅ ነው እያልንህ ፥
ኢጥቢያ ኮከብ ልታበራ
ያርበኛቹን ዕድሜ ይፍታህ ፥ ልናስወግድ በጋራ
ደረቅ ውድቅት ተገፎልህ ፥
የጉህ ውጋጋን ሲጠራ
ድቅድቅ ጭለማው ሲቀድ ፥ ደብዛዛውም ሲፈካ
የከፋው ተከፋፍቶ ፥ ግምባር በግምባር ሲለካ፣
እንዴት "አያ ኩራቴ" ፥ ላትከውነን ተነታረክ
ተው አይሆንም እያልንህ ፥ ወሰክ ነገር ተናገርክ!!

## በሉ እንደራረስ –

(ከማሩ ወልደነጉድጓድ)

መድረስም ያባት ነው
ባህል የፈጠረው ፥ መፋቀር ያነፀው
በሉ እንደራረስ፥ ሁሉንም ድረሱ
ካጠፋችሁ ካሱ
ግን እያደባችሁ ፥ ነገር አትከልሱ
ለእውነት አትሳሱ
ውሸት ቆንጥራችሁ ፥ መርዝን አታፍሱ
የሚደበቅ የለም ፥ ጣሪያ አትዳስሱ
ማን አስቀየማችሁ ፥ ምነው ትርምሱ።

ምነው ለኮሳችሁ ፥ እሳቱን ተፋችሁ
ጭሱ ሊያውራችሁ ፥ ሳሉ ሊያስላችሁ
ወበቅ ሊያፍናችሁ ፥ ከወጥ ቤት ሸሽታችሁ
የት ላይ መሸጋችሁ።

በሉ ቃል እንድረስ ፥ በሉ እንወቃቀስ፣
የቱ ላይ ነው ሐቁ ፥ ጳጳስ ላይ መሳቁ
ባባት መሳለቁ ፥ ማዕረግን መንጠቁ
በውኃ መድፈቁ
ሰድቦ ለሰዳቢ ፥ በአህዛብ "ማጣመቁ"
በዘረኛ ችሎት ፥ "ኃጢያት" መፈልቀቁ።

በሉ እንደራረስ ፥ በእኩልነት ምስ
በዴሞክራሲው ክስ ፥ እንዳው ሳንደጉስ
በቀንድ ሳንታመስ ፥ እንደልቅ አውራሪስ።

አውጡት ክሳችሁን ፥ በሉ እንደራረስ
የናንተን ስንከሳር ፥ የፋይላችሁን ክስ።

"ጠቢባኑንን" ንዱ ፥ ጫኑት ተነጂውን
ጦሩን ስበቁበት ፥ ገድግዱት ቆዳውን፣
ግን እንደራረስ ፥ መዳረስ ያለ ነው
ስድብ ወርውራችሁ ፥ መሸሽ ግን ቧልት ነው።

ማንስ ጀመራችሁ ፥ በሉ እንደራረስ
ማን ተናገራችሁ ፥ እናድርግ ግለ ሒስ፣
ማንስ ጉሸማችሁ ፥ ማንስ አሳጣችሁ
ማንስ ነካካችሁ ፥ እስቲ እንወቃቀስ
በያምም በፍስግ ፥ ሳንዝል ሳናሰልስ።

መድረስም ያባት ነው
ባህል የፈጠረው ፥ መፋቀር ያለ ነው፣
በሉ እንደራረስ ፥ ሁሉንም ድረሱ

ካጠፋችሁ ካሱ
ግን እያደባችሁ ፥ ነገር አትከልሉ
ለእውነት አትሳሱ
ውሸት ቆንጥራችሁ ፥ መርዝን አታፍሱ
የሚደበቅ የለም ፥ ጣሪያ አትዳስሱ
ማን አስቀየማችሁ ፥ ምነው ትርምሱ።

በካህናት ሥራ ፥ መቅደስ ከገባችሁ
በውነት ሳትካኑ ፥ ቡራኬ ካላችሁ
አሥርቱ ቃላትን ፥ በናንተ ፖለቲካ ከፈረከሳችሁ
እስቲ እንደራረስ ፥ መዳረስ ያባት ነው
እውነትን መረዳት ፥ ያው እኮ መርዶ ነው
ለውሸት በቁም መሞት ፥ እምባ ያነባል ሰው።

በሉ እንደራረስ ፥ መዳረስ ያባት ነው
መገዘዘን ይዞ ፥ ሸንኮራን ጨምሮ የሚያሰባስበው
በቅኔ ቤት ዘግቶ ፥
ይፍራታና ቡልጋን የሚያተራምሰው
በቀለም ዣንጥራር ፥ የሚያተራምሰው
በሉ እንደራረስ ፥ አውጡት እርሱ ማነው
የባላገሩ ጦር ፥ የፊደል ጉጠኛው።

የስደት ግፉዐን ፥ ኩሩ መንፈስ አበው
ግዞት ያጠቃቸው ፥ ውትርትር ነፍስ ሆነው
የመስቀል ቀንበሩ ፥ ሰያፍ የጋጣቸው
እንዴት ይሰደቡ ፥ ሳይመከቱ ቀርተው።

በሉ እንደራረስ ፥ እንድረስ ካላችሁ
በሙሴ ፅላት ስም ፥ የአዞ እንባችሁ
ከዕጢያችሁ ፈልቆ ፥ ከላይ ከጉንጫችሁ
የውኃ ቦይ ቀዶ ፥ ከፈሰሰላችሁ
በሉ እንደራረስ ፥ ጉጠኛውም ይውጣ
አፍርሳታ ይሁን ፥ አውጫጫኝ ይውጣ
ቢሻው ዓለም ይለፍ ፥ የምፅአት ቀን ይምጣ
ሥራችን ግልጥ ነው ፥ እንደ ጥጥ የነጣ።

በሉ እንደራረስ ፥ ሁሉንም ድረሱ
የቱ ላይ ነው ፍርዱ ፥ የቱ ላይ ነው ክሱ
ዳኛውስ ማን ይሆን ፥ የቱ ላይ ነው ነፍሱ
ያንድዩ ፍርድ ነው ፥
ወይስ የብዙኃን የሌጌዎን ማሱ።

በሉ እንደራረስ ፥ ማለቂያ ካለበት
ይኸ ቋንዣ መስበር ፥ ይኸ ሥጋ መብላት
በቡና ማመንዠግ ፥ ራት ላይ ሰው ማማት
በመፅሔት መክተብ ፥ በኢንተርኔት መብጣት
በስልክ መቀላመድ ፥ አጠላልፎ መቅላት።

ግን ይግባችሁ እንበል ፥ በሉ እንደራረስ
እግዜር የሚጠላው ፥ ስድስት ነቂስ
ሰባተኛውንም ፥ የአካይስት ምላስ
በወንድም መካከል ፥
ጠብን የሚዘራ ደምንም የሚልስ
የተጠየፈ ነው ፥ ምንም የማይካስ፤

በሉ እንደራረስ ፥ ከጀመራችሁት
መከራ መፍተልን ፥ ነፍስን መግደል መግዛት
ጠላት ሲያቅራራ ፥ ምንጣፍ ተነጥፎለት
ከሆነ ሥልጠና ፥ አባቶችን መግፋት።

አደባባይ ውጡ ፥ በሉ እንደራረስ
እናንተም ድረሱ የቀለም ጡር አለው ፥
በከንቱ አታፍሱ ለእውነት አትሳሱ
ውሸት ባኮፋዳ ፥ ሰቅላችሁ አታምሱ
ለነፍስ እዝኑላት፥ በሸር ያልታፈነ ሥጋ ካለባችሁ
ከተንኮል ርቃችሁ ፥ ኃጢአት ከሌላችሁ
ድንጋዩን ወርውሩት ፥ እውነት ይጠጋችሁ
በሉ እንደራረስ ፥ እንድረስባችሁ።

## የእናት ፍቅር

ከሊዲያ ተክሌ(መዓዛ)

በዓለም ከሚኖሩ ከሰው ዘሮች ሁሉ
የእናትን ውለታ ለመክፈል የቻሉ
ከሚሊዮን፥ ከሺህ፥ ከመቶስ ስንት አሉ?
ለእኔ ግን ብዙ ነው የእናቴ ውለታ
አሁን ነው ያወቅሁት የፍቅሩዋን ትዝታ።
ጤንነት ካላቸው ልጆችን ማሳደግ
ለእናቶች ብርቅ ነው እንደ ተፈጥሮ ህግ
የእናት ትዕግስትና ፍቅርዋ የሚለካው
ልጆችዋ ጤና አይተው ሲታመሙባት ነው።

ለዚህም የእኔ እናት በምሳሌነትዋ
የምታስደንቅ ናት ሰፊ ነው ትዕግስትዋ
ከአንድ ዓመት ለማያንስ ታምሜ ስቸገር
ሌት ተቀን ሳትለይ ታመመች ከእኔው ጋር
ምንም ሳትሰለች የምታሳየኝ ፍቅር
ለተመልካች ሁሉ የሚያስደንቅ ነበር።

እኔ ግን ለጊዜው ታምሜ ስነሳ
የእናቴ ውለታ ስቃይዋም ተረሳ
ስታዘኝ መታበይ መኩራት መዘባነን
መንቀባረር ሆነ መዝናናት መጀነን
አልታዘዝ ስላት አዝና ስትናገር
"ኋላ ይቆጭሻል" ከማለት በስተቀር
ልትቆጣኝ እንኳ አትደፍርም ነበር
ኧረ ምን ዓይነት ነው የእናትነት ፍቅር?

ግን ለምን ነበረ እንደዚያ መሆኔ
ባለውለታዬን እናት ማሳዘኔ
እርሷ ግን ረስታው በትንሽ ቅጽበት
ምን እንደበደልሁዋት ትዝም አይላት
አሁን የርስዋ አሳብ የልብዋ ምኞት
በቴሌፎን ጥሪ ድምጼን ለመስማት
ቢቻል ጊዜ ገጥሞአት ዓይኔን ለማየት
ሁልጊዜ ጸሎት ነው ሁልጊዜ ስለት
ከቶ ምን አንጀት ነው ለርስዋ የሰጣት?
ይቅርታ ሳልጠይቅ የበደልሁዋትን
ይኸው ዓመት ሞላ ከተለያየን
ማለቂያ የሌለው የውቅያኖስ ባህር
ኧረ ምን ዓይነት ነው የእናትነት ፍቅር?

አልታዘዝ ብዬ እኔ እየበደልኩሽ
ከሁሉ በማብልጥ አንቺ እኔን መውደድሽ
እያስደነቀኝ ነው ይህን የጻፍሁልሽ
ማሪኝ ይቅር በይኝ በእናትነት ፍቅርሽ!!

# ቢስቁም – ባይስቁም

(ከጥምቀተ አሮዲዮን)

እንዴት ናችሁ? እኔ አምላኬ ይመስገን በጣሙን ደህና ነኝ። ሰሞኑን ምን ሰማሁ መሰላችሁ? አገራችን የሰሜን አፕ መጠጥ በቅርቡ ነው የገባው አሉ። እና ታዲያ የሰሜን አፕን ትርጉም ሁሉም በራሱ ስሜት የየራሱን ትርጉም እየሰጠው ነው አሉ። አብዛኛው ህዝብ የልቤ ቢሞላልኝ ብሎ 'በቃ የወያኔ መንግስት 7 ዓመት ገዝቷ ልና አሁን እንደእንቧይ ወደ ሰማይ ወጥቶ ሊፈርጥ ነው' ብሎ ደምድሟል። ብልጡ የአገሬ ጉራጌ ደግሞ 'ይሄ ምን ጥርጥር አለው ሰሜን ህውስ (ሰባት ቤት ጉራጌ) ይደግ ይመንደግ ማለት ነው' ብሎም የራሱን ትርጉም ሰጥቷል። ከሁሉም ከሁሉም ቀልድ ግን ያሳቀኝ አንዱ የሴት ጓደኛውን ይዞ አንድ መዝናኛ ቦታ ይገባና የሚጠጣ ያዛሉ። እሱ ካስቴል ቢራ ያዛል (አገር ቤት እንደእናንተ ጊዜ እንደድሮው ሁለት አይነት ቢራ ብቻ ያለ እንዳመስላችሁ። አገሩ ሁላ ቢራ በቢራ ሆኗል አሉ።) እሷ ደግሞ ምን ያዘዘች ይመስላችኋል? ዙፕ። (7UP) አልነበብ ብሏት ነውና አትፍረዱባት። ግን መሳቅ ትችላላችሁ።

ለመሆኑ የዘንድሮው ክረምት እንዴት ይዟችኋል? እኔ መቼም ያን የአገሬን ቆማጣ እንኳ ባገኝ ሳላቅፍ እቀር ብላችሁ ነው? (በደህና ጊዜ ያላስቀመጥከውን ዛሬ ከየት ታመጣው እንዳትሉኝ እንጂ) ያለ ምክንያት አይደለም ስለ ብርዱ ያነሳሁት ዛሬ ወደ ክረምት ቀልድ አዘል ወሬ ልወስዳችሁ ነው፦ አንድ አሜሪካዊና የስኮትላንድ ተወላጅ በክረምቱ ወራት በእስኮትላንድ ውስጥ ስለነበረው ቅዝቃዜ ሲጫወቱ፣ የስኮትላድ ተወላጅ፦ "እኔ የነበርኩበት አካባቢ እጅግ በጣም ቀዝቃዛ ከመሆኑ የተነሳ ስናወራ ከአፋችን የሚወጡት ቃላት ወደ በረዶነት ስለሚቀየሩ ምን እንደተባባልን ለማወቅ እሳት ላይ መጥበስ ነበረብን" ይለዋል።

አሜሪካዊው፦ "አይ! ይቺ ምን አሳት! እዚህ ያለ ብርድ አሜሪካ ካለው ጋር ሲነፃፀር ምን ብርድ ይባላል? ትዝ ይለኛል አንድ ክረምት እጅግ ከመቀዝቀዙ የተነሳ አንዲት በግ ከኮረብታ ላይ ወደ ሜዳው ስትዘል በአየር እንዳለች ቀዝቃዛ የበረዶ ክምር ሆና ቀረች" ይለዋል።

የስኮትላንድ ተወላጅ፦ "ይኸማ እንዴት ይሆናል? ከስበት ህግ ውጭ እኮ ነው" ብሎ ቢቃወም

አሜሪካዊው፦ "እሱንማ አውቃለሁ። ግን የስበት ህግ ራሱ ቀዝቅዞ ነበር።" ብሎ መለሰለት።

✡ ✡ ✡

እናት – ልጆ አዋቂዎች ሲያወሩ ጣልቃ ገብተሽ አታውሪ። እስኪጨርሱ ጠብቂ ብዬ ከዚህ በፊት ነግሬሽ አልነበር?

ልጅ – ታዲያ እነሱ አውርተው አይጨርሱማ!

✡ ✡ ✡

ወላጆች ስለልጆቻቸው ትምህርት ሁኔታ መምህራንና ቤተሰቦች እንዲነጋገሩ ይጠሩና ይሄዳሉ። ከዚያም ስለተለያየ ነገር ሲወያዩ ከቆዩ በኋላ በመጨረሻ ልጆቻችሁ በትምህርት ቤት ውስጥ ስለ ወሲብ ትምህርት ቢሰጣቸው ምን ይመስላችኋል? ለተባለው ጥያቄ ወላጆች ሀሳብ ሲሰጡ ቆዩና የአንድ ወላጅ እናት ተነስተው "ነገሩስ ጥሩ ነበር። ግን ግን የቤት ሥራ ባይሰጣቸው ጥሩ ነው።" ብለው ሐሳብ እንዳቀረቡ ይነገራል።

✡ ✡ ✡

በአንድ የኃይማኖት ነክ ስብሰባ ላይ ቄሱ ከስብከተ ወንጌል ትምህርት ቀጥሎ ቤተክርስቲያኗን ለማሳደስ ስለገጠመው የገንዘብ ችግር በማስተዛዘን ለምዕመናኑ ሲገልጹ ከቆዩ በኋላ ምዕመናኑ የቤተክርስቲያኗን ችግር አይተው እንደየአቅማቸው እንዲረዱ በመማፀን የገንዘብ መሰብሰቢያ ሙዳይ ለምዕመናኑ እንዲዞር ትዕዛዝ አስተላለፉ። ምዕመናኑ ሙዳዩን ሲቀባበሉት ቆይተው በመጨረሻ ዞሮ ወደ ሰባኪው ቄስ ተመለሰ። ቄሱ ሙዳዩን ሲያዩት ጊዜ ባዶ ሆኖ አገኙት። ከዚያም ባዶ መሆኑን ለማሳየት ሙዳዩን ከፍ አድርገው ዘቀዘቁና እያራገፉ አይናቸውን ወደ ጣሪያው ሰቅለው "ሙዳዩ ራሱ ከእንዲህ ዓይነቱ ስብሰባ በደህና መመለሱ ለቸሩ እግዚአብሔር ምስጋና ይግባው" አሉ።

(እስቲ ለዛሬ ይብቃችሁ)

## . . .መቼ ይሆን እኛም ...

(ከገፅ 33 የዞረ)

ህዝቦች የሚገኙበት መሆኑንም አብሮ የሚያንፀባርቅ ቃል ነው። ታዲያ እኛ ከሀገራችን ወጥተን ከወዳጅ ዘመድ ከቤተሰብ ርቀን በባህር ማዶ ተበታትነን የምንገኝ ዜጎች በሙሉ ከዚህ ከሰለጠነው ህዝብ መካከል ተገኝተን የቀሰምነው ትምህርት አለን? እንደ እኔ አመለካከት ከምዕራቡ ሀገር ልንወስደው የሚገባን ትልቁ ትምህርት ወይም ቁም ነገር "መቻቻል"ን ነው።

ሁለት የተለያየ ሐሳብ የሚያመነጩ አንዳንዴም ጉሮሮ ለጉሮሮ ለመተናነቅ የሚደርሱ የፖለቲካ ፓርቲ አባሎች መሰረተ ዓላማቸው ግን የአንድ የተባበረና ጠንካራ አሜሪካ ህልውና ነው። አንዱ ክፍል የሌላውን ሐሳብ ስለነቀፈና ስላዋደቀ አንደኛው ሌላውን ከምድረ ገፅ ለማጥፋት አይፈላለጉም። ይህንንም የፀና አንድነት ያሳየን ፕሬዚዳንት ክሊንተን ኢራቅን ለመምታት የእንግሊዝና የአሜሪካን መንግሥት መወሰናቸውን በቴሌቪዥን ቀርበው ለህዝቡ ሲያሳውቁ ከተቃራኒው ፓርቲ አባላት ማጉረምረምና ጥርጣሬ የተሞላበት በርካታ አስተያየቶች ተሰንዝረው ነበር። ይሁን እንጂ ውሎ ሳያድር የሀገር ጉዳይ ከሽኩቻውና ከቃላት ጦርነት ይልቅ ቅድሚያ እንደሚሰጠው በመገንዘብ ልዩነታቸውን ለጊዜው ወደ ጎን በማድረግ ፕሬዚዳንቱ ያሳለፉትን ውሳኔ እንደሚደግፉ ገልፀዋል።

ዛሬ በተለያየ ስም በሚጠሩ የፖለቲካ ድርጅቶች ተሰባስበን የምንገኝ ሁሉ "ኢትዮጵያ" የሚለውን የአንድነት መጠሪያችን ጨርሶ እንዲጠፋ ሌት ተቀን ከሚደክሙ፣ "ሀገር" እንመራለን ብለው ከጭንቅላታችን ላይ የተቀመጡትን ፀረ አንድነቶች፣ ሀገራችን እንደጨርቅ ተበጣጥሳ ማየት የሚፈልጉትን የወያኔ ገዥዎችና አበሮቻቸውን በተባበረ ክንድ ለመዋጋት ልዩነታችን እንቅፋት አይሁንብን። ለጠላቶቻችን መደሰቻና ዕድሜያቸውን ማራዘሚያ አንሁን። ርስ በርሳችን ለመጠፋፋት ከመፈላለጋችን በፊት ተቀዳሚው ዓላ

ችን ሀገራችንን ማዳን ይሁን። ታዲያ እዚህ "ነፃ" ዓለም ውስጥ እያለን መቻቻልን ካልተማርን መቼ ልንማር ነው? እናስ በትምህርት መግፋት፣ ጥሩ ልብስ ለብሶ መታየት፣ በቆንጆ መኪና መንፈላሰስ አልፎ ተርፎም ባማረ ቤት ውስጥ መኖር ምን ፋይዳ ይኖረዋል?

የሰው ቤት የሰው ነውና ስለ ዘላቂውና ዕውነተኛው ቤታችን ሌላው ቀርቶ ስንሞት ሬሳችንን ለምንልክላት ሀገራችን ዘላቂ መፍትሄ እናስብ። "ባዶ ጭራሽ ባዶ'

እንደተባለው እንዳይሆን። ኢትዮጵያ የሚገኙ ዘመዶቻችን ከእኛ የገንዘብ ዕርዳታ ብቻ ሳይሆን የሚሹት ይህንን ሀገራችንን ወጥሮ የያዛትን ችግር ለማቃለል የድርሻችንን እንድናዋጣ ይጠብቁናል።

የዛሬውን ፅሁፌን "ተው ስማኝ ወገኔ! ተው ስማኝ ወገኔ" እያልኩ ጥሪዬን በማቅረብ እደመድማለሁ።

(ገነት ጉርሙ)

# ዜና ቤተክርስቲያናት

## በአትላንታ የቅዱስ ገብርኤል በዓል በደማቅ ሁኔታ ተከበረ





ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ መርቆሬዎስ ፓትርያርክ ዘኢትዮጵያ በተገኙበት ታህሣስ 18 ቀን 1991 ዓ.ም. የቅዱስ ገብርኤል ዓመታዊ በዓል አትላንታ በሚገኘው ደብረ ኃይል ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስትያን በደማቅ ሁኔታ ተከበረ። በበዓሉ ላይ እጅግ በጣም ብዙ ምዕመናን ተገኝተው በደስታ አክብረዋል።

የበዓሉ ገፅታ በከፊል





# በትልቅነቱ ምናልባትም በአሜሪካ ወደር የማይገኝለት
# በቺካጎ በቅርቡ የተገዛው
# መድኃኒያለም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን

**ዝርዝር ዜናውን ቤተ የክርስቲያኑ የመክፈቻ ክብረ በዓል በሚደረግበት በግንቦት ወር እትማችን እናቀርባለን።**



**በአትላንታ ሳህሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ቅዱስ ፓትሪያርኩ አቡነ መርቆሬዎስ፤ ብፁዕ አቡነ ዜና ማርቆስ፤ ብፁዕ አቡነ ይስሃቅና ብፁዕ አቡነ መልከፀዴቅ በተገኙበት የቅድስት ማርያም ዓመታዊ በዓል በታላቅ ድምቀት ሲከበር**



# ሰንጠረዥ

**በሰይፉ ኣዳነች ብሻው**

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፺ ዓመት
SAEFU © Copyright 1997

ይህን የሰንጠረዥ ጨዋታ ከግራ ወደ ቀኝ፣ ከቀኝ ወደ ግራ፣ ከላይ ወደ ታች፣ ከታች ወደ ላይና በሰያፍ በመከበብ የቀሩት ኖኄያት የሚያነቡትን በመፈለግ በጊዜዎት ይዝናኑ

| | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ያ | ሑ | ር | ወ | ል | ሰ | ሜ | ን | 2 | 7 | 2 | 7 | 2 | 6 |
| በ | ት | ቢ | ጋ | መ | ስ | ከ | ረ | ም | ደ | ቃ | ቅ | 6 | 2 |
| ባ | ም | ቢ | በ | ሐ | ዛ | ው | ጀ | ጋ | ተ | ራ | ላ | ወ | ለ |
| ና | ረ | ጄ | ጋ | ይ | ፀ | ይ | ደ | ፀ | ሥ | ጉ | ጌ | ት | ው |
| ት | ክ | ደ | ከ | መ | ስ | ከ | ረ | ም | ና | ች | ማ | ጥ | ለ |
| ቅ | ቦ | ይ | ነ | ው | ከ | ሥ | ሣ | ኅ | ታ | ክ | ሎ | ማ | ጥ |
| ወ | ል | ደ | ቀ | ኔ | ሰ | ል | ጋ | ና | ን | ኅ | ጥ | ቃ | ኅ |
| አ | አ | የ | ፍ | ሬ | ኔ | ሶ | ቆ | ቲ | ላ | ር | ሣ | ስ | ራ |
| ስ | ኛ | ተ | ል | ቧ | ባ | ብ | ባ | ነ | ደ | መ | ው | ሥ | ው |
| ቂ | ደ | ወ | አ | ግ | ዜ | ራ | ራ | ታ | ነ | የ | ር | ሳ | አ |
| ኝ | ል | ራ | ይ | አ | ዶ | ቅ | ወ | ዕ | ት | ለ | ማ | ን | ተ |
| ን | ቀ | ት | ሰ | ባ | ብ | ዐ | ረ | ታ | ም | ች | ደ | ቡ | ብ |
| ን | ን | ድ | ሚ | ዛ | ን | ን | ጣ | ር | ሸ | ለ | ሊ | ላ | ገ |
| ካ | ዋ | ቶ | አ | ደ | ር | ሮ | ዜ | ተ | ው | ር | ሀ | ባ | መ |

**ወቅት**

መፀው፡- ከመስከረም 27-
ታኅሣሥ 26
(ያበባና የፍሬ ወር ማለት ነው)

በጋ፡-፡- ከታኅሣሥ 27-
መጋቢት 26

ፀደይ፡- ከመጋቢት 27-

ሰኔ 26
ክረምት፡- ከሰኔ 27-
መስከረም 26

**መገብተ-አውራኅ**

ሚዛን Libra
ዐቅራብ Scorpio

ቀውስ Sagittarius

ጄደይ Capricorn
ደለው Aquarius

ሑት Pisces

ሐመል Aries
ተውር Taurus
ጀውዛ Gemini
ሸርጣን Cancer
አሰድ Leo
ሳንቡላ Virgo

**ብሶል**

ምሥራቅ
ሊባ

ደቡብ

አዜብ
ምዕራብ

ባህር

ሰሜን
መስዕ

**ቃላት (ቃሎች)**

ዋቶ አደር (ወታደር)
ካንት ይግባ (ከንቲባ)


ተጉማማ (ውስጥ ለውስጥ ተወራ)

ቧልተኛ (ቀልደኛ/ አስቂኝ)

አልቦ (ዜሮ፣ ባዶ፣ ጌጥ)

# መልሱን ባድራሻችን ላኩልን።

# ቃላት በሰንጠረዥ




## ወደ ጎን

1. ልጅ
2. ፊት መመልከቻ
9. ቄቅቄቅ
11. ንፁህ ማድረጊያ
12. ገብጋባ
14. ጀርም
16. ምጣድ (በትግርኛ)
18. በእግሩ ነካው
20. ሳትቀርብ
21. ማለያየት
23. አያያዘው
25. ቆንጆ ይሁን
28. ትልቅ እንሥራ
29. ክፍትፍት
31. በረታ
33. ዕቃ መያዣ
34. የድንጋይ ክምር
35. ምስክራችን
37. ፊት ሁን
39. መከደኛ

## ወደ ታች

1. የአባቴ ወንድ ልጅ
2. የእጅ ክፍል
5. አዳምጥ
6. ያለ ልክ ሞላ
7. ምስክር
8. ተውኔት
10. ጨካኝ
13. ምታው
15. በልጣ
17. ጠማማ
19. ዕጣን ማጨሻ
21. ስድ
22. ድብልቅ
23. አጠፋ
24. መከለያ
26. ደግ
27. ቅዝቃዜ ያለው
29. አለመረዳት
30. ከት ብዬ ______
32. ወሰነ
33. ስስ ጠፍጣፋ ትንሽ ብረት
36. ስልችት
38. ዳገታማ ቀዝቃዛ ቦታ

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

**የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።**

| | 12 ISSUES | | 6 ISSUES | |
|---|---|---|---|---|
| U.S | $30.00 | ☐ | $16.00 | ☐ |
| Canada | $40.00 | ☐ | $22.00 | ☐ |
| Europe | $56.00 | ☐ | $30.00 | ☐ |
| Asia | $70.00 | ☐ | $38.00 | ☐ |
| Institutions | $80.00 | ☐ | $40.00 | ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (     )* ______________

================================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (     )* ______________

================================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*

# MRA'G TRAVEL, Inc.

## ሚራዥ የጉዞ ወኪል

*International - Business - Leisure - Cruise*

92 Piedmont Ave. NE - Atlanta, GA 30303



ለዓለም አቀፍና
ለአገር ውስጥ ጉዞዎ አለንልዎ!!

XCELLENT SERVICE - SPECIAL FARE - GROUP FARE

**የኢትዮጵያ አየር መንገድ ቀጥታ በረራ**
**ከአዲስ አበባ — ዋሽንግተን ዲ.ሲ.**
**በJune 4, 1998 ቀን ጀምሮ**
**ዘወትር ሐሙስና ቅዳሜ**
**በረራውን ለማስተዋወቅ**
**ልዩ ታላቅ ቅናሽ**

SPECIAL INTRODUCTORY FARE

ገነት ፈቀደ – ፕሬዚዳንት
GENET FEKEDE
PRESIDENT

**Please, call** (404) 577-4404
(404) 577-4682
(404) 577-4889
**Fax:** (404) 222-9305

Cerified Agent for:
ARC - IATA - CLIA

**Also Call:**
**San Fransisco Area**
**Aderaw Yeshiwas**
**Selam Fekede**
**Phone: (510)829-0529**
**Fax: (510)829-0529**

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
***ETHIOPIAN AIRLINES***

*Fly ETHIOPIAN*

የኢትዮጵያ አየር መንገድ
ልዩ ወኪል
CONSOLIDATOR FOR
*ETHIOPIAN AIRLINES*



# Allstate®

**You are in good hands.**

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978 - Fax: (404)299-6266

- ⇨ **AUTO**
- ⇨ **HOME OWNER'S**
- ⇨ **RENTERS**
- ⇨ **LIFE**
- ⇨ **BUSINESS**
- ⇨ **COMMERCIAL AUTO**



Theodros
Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, IL
Allstate Indemnity Company, Northbrook, IL
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**

# DO YOU HAVE




## We Have The Solutions

**Services we provide**

- Marketing
- Promotions
- Advertisement
- Distributions
- Publishing
  - Books
  - Magazines
  - News Papers
  - News Letters
  - Brochures
  - Stationary
  - Menus
  - Fliers
- Artist Development
- Recording and producing music
- Commission Agent

ደውለው ያነጋግሩን:: በአገልግሎታችንም ይደሰታሉ::

OPIA

Marketing & Promotions

MAKING YOUR IDEAS PRACTICAL

Specializing in the Ethiopian Market

Tel: 703 567 8127 Fax: 703 567 5932 E-Mail: OPIA1@aol.com
PO Box 70909, Washington, DC 20024